# ከሚሽግዳ እስከ ዓለም ዳርቻ

(ሕይወቴ ትምህርት ቤቴ)

ለአክብሮት ምስጋና ጋር
ተስፋ ጽዮን ደለለው

በ

ተስፋጽዮን ደለለው (ዶ/ር)

# አበርክቶት

ወንጌልን በደማቸዉ ዘርተዉ ላለፉት

ቀዳማይ የወንጌል አማኞች

ለአጎቴ አቶ ፈታሞ ዋቤቶ፣

ለአጎቴ መንታሞ ዋቤቶ፣

ለአቶ ፉዕኑሮ አናሞ፣

ለአቶ ፎቼ አናሞ

እና

ለአቶ ቦቄ አንጄ።

ፅናትን፣

ትጋትን፣

አይበገሬነትን

በሕይወታቸዉ ኖረዉ ላሳዩኝ

ለእናቴ እማማ አንሸቤ።

እንዲሁም

ከዕድሜዬ ኢጋማሽ በላይ አብራኝ ለዘለቀችዉ ባለቤቴ

አምሣለ ገብረ ማርያምና ለልጆቻችን ዋቤቶ፣ መና እና ማኀሌት

መታሰቢያ ትሁንልኝ።





# ከሚሽግዳ እስከ ዓለም ዳርቻ

(ሕይወቴ ትምህርት ቤቴ)

ግለታሪክ

ደራሲ:- ተስፋጽዮን ደለለዉ

ኤዲተር:- ወንድዬ ዓሊ

የሽፋን ስዕል:- ሳሙኤል ወርቁ

አንደኛ እትም 2007

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነዉ

Kemishgeda Eske Alem Darech

(Hiywote Temehret Bete)

Author: Tesfatsion Dalellew

Editor Wondiye Ali

First Edition: 2015

Copyright©2015 Tefsation Dalellew

All rights reserved no portion of this book may be reproduced in any form what so ever, expect for brief quotations, in reviews, without the written permission of the publisher.

አሳታሚው የጸሐፍ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማባዛት፣ በኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች መቅረጽና ማራባት የተከለከለ ነው።

ኢሜል:tesfatsion@gmail.com

ስልክ ቁጥር:0911 92 58 77

ፖስታ ሣጥን ቁጥር:102055

# ከሚሽግዳ እስከ ዓለም ዳርቻ
# (ሕይወቴ ትምህርት ቤቴ)

በ

ተስፋጽዮን ደለለዉ

ኤዲተር

ወንድዬ ዓሊ

Email: wondiyealihamza@gmail.com

Mobile፡ 0911 689941





## ማውጫ

አመሰግናለሁ ........ 8
መቅድም ........ 12
መግቢያ ........ 13
የኤዲተሩ ማስታወሻ ........ 17
ምዕራፍ አንድ ........ 19
መሠረቴ - ዙሪያ ገባዉ ........ 19
1. ትውልዴና የሕይወቴ ሀሁ ........ 19
መልከዓ ምድሩ ........ 21
2. ልጅነቴ - በተንገጫገጨ ቤተሰብ ውስጥ ........ 22
ምዕራፍ ሁለት ........ 29
የቤተሰባችን ሃይማኖታዊ ዳራ ........ 29
3. ቅድመ ወንጌል ሃይማኖት በከምባታ ........ 29
የአባቴ ሃይማኖቶች ........ 30
ፎጠ ፊዱ ........ 33
የመሳላ በዓል ........ 34
4. ወንጌል ቤታችንን ሲያንኳኳ ........ 37
"አየሱስ! . . . እሱ ደግሞ ምንድ ነው?" ........ 37
አባታችን ........ 40
አባባ በልጆቻቸው ሚዛን ........ 41
5. እናታችን ........ 43
የቋንቋ ልዩነት አስኮበለለኝ ........ 46
6. ጋብቻ በከምባታ ባህል ........ 53
ማባበል፣ ማግባባት - ሔረንቻ ወይም ሔረሚ ........ 53
ጠለፋ- ምዱ (ምዷ) ........ 54
"ልጃችሁን ለልጃችን" ........ 55
ምዕራፍ ሦስት ........ 58
ወንጌል፣ ወንጌላውያንና ማሕበራዊ ለውጥ ........ 58
7. የመጀመሪያዎቹ የወንጌል መልእክተኞች ........ 62
በመጀመሪያ:- ወንጌልን ለቅርቦቻቸዉ አደረሱ ........ 62
ሁለተኛም:- በየገበያው ወንጌልን ዐወጁ ........ 62
ሦስተኛ:- ፊደል ማስቆጠርን እንደ ወንጌል ስርጭት ስልት ተጠቀሙበት ........ 63
8. ወንጌል ያስከተለዉ ማኅበራዊ ለውጥ ........ 65
መማር ........ 66

በሥራ መትጋት ..... 67
ፍርሃት ቀረ ..... 68
ባሕላዊ እሴቶች ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ፡- ..... 69
ትኩስ ድንች ..... 70
መነቃቂያ ኮንፍራንስ፡- ..... 73
ሁለቱ ባሪያ ፈንጋዮች ያሳደሩት ተፅዕኖ ..... 74
9. ስደቱና የፈጠረው ትርምስ ..... 77
**ምዕራፍ አራት** ..... 82
የመደበኛ ትምህርት ጉዞዬ ..... 82
ጥቂት ስለ ተሰማ አሩሲ ..... 85
እንደገና አሰላ ..... 91
ይርጋ ዓለም ..... 93
10. አሁንም ትምሕርት ..... 94
ጃንሆይ በድንገተኛ ጉብኝት ..... 96
የማትሪክ ፈተና ..... 99
11. ባይብል አካዳሚ - ከትምሕርቱ ሌላ ..... 101
**ምዕራፍ አምስት** ..... 104
ትምህርትና ቤተ ክርስቲያን ..... 104
12. ቀጣይ ትምህርቴና ሜኖ-ናይትነቴ ..... 104
13. በአባልነት ስለ መጠቃለሌ ..... 108
14. ከካሸርነት ወደ ባሕር ዳር ፖሲ ..... 111
በየት ልውጣ!? ..... 114
ዋሸሁ! ..... 115
ተናዘዝኩ ..... 117
15. ለኰሌጅ ትምህርት መመረጥ ..... 117
16. የ"አንዲት ልጅ" ነገር ..... 119
**ምዕራፍ ስድስት** ..... 124
አዲስ የሕይወት ምዕራፍ ..... 124
17. ትምህርት በአሜሪካ ..... 124
የኮሌጅ ዕዳዬ ..... 129
18. ወደ አገሬ ..... 131
አዲስ አበባ ..... 135
የኰሌጅ ጓደኞቼ በአገር ቤት ..... 136





እዚህም እዚያም ..... 136
19. እማማና 17ቱ ዓመታት ..... 138
20. አዲሱ የሥራ ዓለም ..... 146
አስተማሪና የተማሪዎች ዲን ..... 146
ባይብል አካዳሚ ..... 147
**ምዕራፍ ሰባት** ..... 150
ትዳር ..... 150
21. የአርባ ዓመት ትዳር ..... 159
**ምዕራፍ ስምንት** ..... 169
አገልግሎት በብሔራዊ ደረጃ ..... 169
22. የመሠረተ ክርስቶስ ዋና ጸሐፊ ..... 169
23. እዚያ ነበርኩ፡- ሲ.አር.ዲ.ኤ (CRDA) ሰቋቋም ..... 175
24. እዚያ ነበርኩ፡- የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ሲመሠረት ..... 176
25. ወርልድ ቭዥን ..... 184
26. የኖኅ መርከብ ወደ ፍርድቤት ..... 195
27. በአብዮቱ ያልጠበቅሁት ገጽታ ..... 198
**ምዕራፍ ዘጠኝ** ..... 205
አገልግሎት በውጭ አገራት ..... 205
28. ኒውዚላንድ -በዝውውር (Newzealand) ..... 209
29. ድንገት ወደ ኢትዮጵያ ..... 211
30. ወደ ድኅረ-ምረቃ ትምህርት ቤት ..... 213
እንደገና ተማሪ ..... 215
በአሜሪካ ከኢትዮጵያ ወንጌላውያን ጋር ..... 217
"በቦሌም በባሌም" ..... 222
ሲአትል ..... 222
ፔንስልቫኒያ ..... 224
31. 19918 - ኤምሲሲ (MCC) ..... 227
ኤምሲሲ (MCC) ምንድንነው? ..... 231
**ምዕራፍ አስር** ..... 237
የማታ ማታ ..... 237
32. ወደ አገሬ ..... 237
ጥቂት የከምባትኛ ቃላት ..... 251
የከምባትኛ አባባሎች ..... 262

# አመሰግናለሁ

እግዚአብሔር ሰውን እንደ ደሴት ብቸኛ አድርጐ ያልፈጠረው ሁለንተናዊነቱን ከወላጆቹ ጀምሮ ከጐረቤቱ ጓደኛው ከአለቃውና ከጭፍራው ሁሉ እንዲያገኝ እንደሆነ ይህቺ መጽሐፍ ምስክር ናት ብዬ አምናለሁ። ሰው ከተወለደበት ዕለት አንስቶ  እስከ ግባዓተ መሬቱ ድረስ ለሰው - ሰው ያስፈልገዋል። በሕፃንነቱ የሚያቅፈው፣ በጉልምስናው የሚመክረው፣ የሚገስጸውና መልካም ሲሠራም የሚያመሰግነው፣ በሽምግልናው ደግሞ የሚደግፈው፣ ያው ሰው ነው።

ይህም ጸሐፊ ሰው በመሆኑ በሕይወት ጉዞው፣ ውጣ ውረዱ፣  ያለፈባቸዉና ያለፉበት፣ እንዲሁም ያሳለፉቸዉ ዱካዎች ምናልባት ለቀጣዩ ትውልድ ጠቃሚ ነገር ከተገኘበት በማለት ለማቀናበር ያደረገው ሙከራ ከፈጣሪው በታች ያሳካለት ሰው ነው። ለዚህ ያበቁኝን ሰዎቼን በሙሉ በዚህ የምስጋና ገጽ ለመዘርዘር አይቻለኝም - እጅግ ብዙ ናቸውና። ከእናቴ አነሼቤ ልነሳ፡-

- እናቴ አንሼቤ! ዕድሜ ብቻ ሳይሆን የነቃ አእምሮ ከጤና ጋር የሰጠዎትን እግዚአብሔርን  አመሰግናለሁ:: እማማ፡- የትጋት፣ የፅናት፣ የታታሪነት ምሳሌዬ ነዎት:: መጽሐፉን ለመጻፍ ከጀመርኩበት ቀን አንስቶ በተለያዩ ጊዜያት ላቀረብኩልዎት ጥያቄዎች በአንዳንዶቹ ሞኝነት እየመሰሎዎት ከት ብለው ቢስቁም፣ የሰጡኝ መረጃ መተኪያ አልነበረውም::

- ገና ከማለዳዉ ወደ መደበኛ የትምህርት ገበታ እንድወጣ ያነሳሳኝ፣ የመከረኝ፣ የገሠጸኝ፣ ኋላም የተመኘልኝን ሆኜ ስገኝ የአመሰገነኝ - ያ የበቀልኩበት ማኅበረሰብ ነዉ። ከጥቂት መፍጨርጨሮች በተቀር የሚገባውን ውለታ ስለ መክፈሌ ገና እርግጠኛ አይደለሁም:: ሆኖም ያሳደገኝን ማኅበረሰብ ውለታ እስከ መቃብር በር ድረስ ሳስታውዉ እኖራለሁ:: እነሆ ክቡር ምስጋናዬ!





- ጋሼ ተሰማ መደበኛ ትምሕርት በአሰላ ከተማ ባስጀመረኝ ዓመት አንድ ማለዳ የሆነ ዕቃ ከሱቅ እንድገዛ ተልኬ ስሄድ መኪና ብርቁ በነበረበት በዚያ ዘመን ከኋላዬ አንድ መኪና እየመጣ መሆኑን አየሁ:: ለሚሽግዳ ልጅ መኪና ብቻ ሳይሆን የመኪናም ጥሩምባ (ክላክስ) ብርቁ ነበር:: መኪናዉ አንዴ ጥሩምባ እንዲያሰማኝ ጓጓሁ:: ስለሆነም መሐል መንገዱን ይዤ መራመዴን ቀጠልሁ። መኪናው ፍጥነቱን እጅግ ቀንሶ (እየተንከባለለ ማለት ይቻላል) በጐኔ በኩል መጣ፤ ሹፌሩ ሳይሆን አንዱ ተሳፋሪው እጃቸውን በመስኮት አውጥተዉ ጆሮ ግንዴን አጮሉኝ:: ዘልዬ በዩን ተሻገርኩ፤ ዞር ብዬ ሳያቸው የፖሊስ አዛዡ ነበሩ:: “ሁለተኛ በመኪና መንገድ ብትሄድ . . .!” ብለው የእድሜ ልክ ዛቻ ዛቱብኝ:: እንደዚያ ዓይነት ስህተት ዳግም አላደርግሁም፤ ሰውዬውንም ለዘላለም አልረሳቸውም። እነሆ ከባለ ውለታዎቼ የኀሊና መዝገብ እንደ ሰፈሩ ቀሩ::

- የሁለተኛ ክፍል አስተማሪዬ አቶ ወልደ ሐና ይባሉ ነበር። በትምሕረት ውጤት መግለጫዬ (ካርዴ) ላይ “ዐመል” በሚለው መስመር ላይ አስተያየተቻውን ሲጽፉ “ግብረ ገብነት የተፈጥሮ ስጦታው ስለሆነ ችግር የለበትም” ያሉት በዘመኔ ሁሉ የሕይወት መመሪያ ሆኖኛል።

እነዚህ አራቱ በሕይወቴ ያሳረፏቸዉ ማኅተሞች ቢተነተኑ እጅግ ብዙ ናቸው። ለእኔነቴ መገለጫ እንደ መላእክት መልካም መልእክተኞች ድምር ውጤታችሁ ነኝና ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸዉ።

ባለቤቴ ወ/ሮ አምሳለ ገ/ማርያም፤ ልጆቻችን ዋቤቶ፣ መና እና ማህሌት ከለገሡኝ ፍቅራቸው ሌላ ተሞክሮዬን በመጽሐፍ መልክ እንዳደራጀዉ ከጐተጐቱኝ መካከል ቀዳሚዎቹ ናቸው።

የመጻፉ ነገር በውስጤ እየጋለ በመ፟ጣበት ወቅት ነበር መጋቢ በቀለ ወልደ ኪዳን

"ጣልቃ እየገባ" በሚል ርዕስ ስለ ጻፈዉ መጽሐፍ የሰማሁት፡፡ የቀደሞ የሥራ ባልደረባዬና ወዳጄም ስለነበረ ደወልሁለትና መጽሐፉን ባለማግኘቴ የተሰማኝን ቅሬታ በስሱ ገለጽኩለት፡፡ "አሁን ፈልጌ ይዤልህ እመጣለሁ" አለኝና መጽሐፉን ይዞ ከተፍ አለ። ማኪያቶ ፉት እያልን ስንጨዋወት እንደ ስብከቱ ሁሉ ፅኑ በሆነዉ ንግግሩ "ጋሽ ተስፉ አንተስ ለምን አትጽፍም?" ብሎ እሳቴ ላይ ቤንዙኑን አፍስሶበት ተለያየን። በቁ እንግዲህ ያንተ ምስጋና የምመልሰዉ ይህች መጽሐፍ ታትማ እኔም "በአክብሮት" ብዬ ሳበረክትልህ ነው።

የመጽሐፉን አዘገጃጀት በአማካሪነት እንዲያግዘኝ የመረጥኩትኩት ወንድዬ ዓሊን ነዉ፡፡ በስልክ ተነጋግረን፤ "ለውሎዬ ቡና" ግብዣ ጭምር ቢሮዬ ድረስ መጣ፡፡ ለተለኮሰው እሳት ማገዶ የሚሆነውን ነገር ሊሰጠኝ እንደሚችል ነግሮኝ ሄደ። በአጭር ቀናት የልቤን አሳብ የማፈስባትን የይዘትና የቅርፅ ካርታ በአጭር ገጾች በተቀነባበረች ሙዳይ ቀምሮ ሰጠኝ፡፡ ወንድዬ በቃል ብቻ ሳይሆን በአርትዖት ሥራህም ታማኝ ሆነህ እስከ ኅትመቱ ቀን አብረኸኝ ስለቆምክ ባለውለታዬ ነህ።

መጋቢ አማኑኤል ሄራሞ በዱራሜ የተሰበሰቡልኝን አስራ ሁለት የቤተ ክርስቲያንና የአገር ሽማግሌዎች አስተባብሮ በዱራሜ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ቁ. 2 ጽ/ ቤት ሁለት ጊዜ አከታትሎ ስለ ሰበሰበልኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

አቶ ጌታቸው ሞሎሮ የታሪካ ማጠናከሪያ መረጃዎችን ለማጠናቀር ስል ከአካባቢዉ የአገር ሽማግሌዎች ጋር ያደረግሁትን ሁለት ዙር ውይይት ቃል በቃል በመጻፍ ረድቶኛልና በእጅጉ ላመሰግነው እወዳለሁ።

እየተወደደ በመጣው የማታ ጉልበታቸው ጥሪዬን ቁም ነገር ብለው ከመቀመጫቸው ብቻ ሳይሆን አንዳንዶቹ ከመኝታቸው ተነሥተው መጥተው የተሰበሰቡልኝንና እውቀታቸውን ያካፈሉኝን ስማቸውና ምስላቸዉ በመጽሐፉ በስተመጨረሻ የተዘረዘረውን አባቶች ለማመስገን ቃላት ስለማይበቃኝ የልቤ ይድረሳችሁ እላለሁ።





ሁለቱንም የሽማግሌዎች ስብሰባ በዱራሜ ቃለ ሕይወት ጽሕፈት ቤት በቪዲዮ የቀረጸልኝን ወንድም ፍቅሩ አራሮን፤ በጣም አመሰግናለሁ።

የመጀመሪያውን ንድፍ በኰምፒውተር የተየበሽልኝን ወይኒቱ ገብረ ማርያምን፤ እንዲሁም ሁለተኛውን ዙር ትየባ በመተየብ ብቻ ሳይሆን ተደጋግሞ የተከሰተውን እርማትም ሆነ ማስተካከያ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትይ የሠራሽልኝ እውቢት ኑራሞን አመሰግናለሁ፡፡

ቡተሬ ፈታሞ፣ ገብሬ ፈታሞ እና ዶዕለሶ ደልበቶ፤ በተለይም የቤተሰብን ሐረግ በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃ በመሰብሰብና በቅንበሩም ቀና ኃሳባቸውን በመስጠት ያደረጉልኝ እርዳታ ከፍተኛ ነው። በተለይም ቡተሬና ገብሬ ወደ ተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር የመረጃውን ትክክለኝነት በማረጋገጥ ረገድ ላደረጉልኝ አገዛ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

ወንድሜ ወልዴ እና እህቴ ዘነበች፤ በእናታችን አጠገብ ሆነው ለእናቴ ያቀረብሁላቸውንም ጥያቄዎች መረጃውን በመስጠትም ሆነ በማስተካከል ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ ያደረጋችሁልኝ እርዳታ ሳይመሰገን የሚታለፍ አይደለም።

እህቴ ወ/ሮ ሰናይት እነዚያን አሥራ ሁለት አባቶች በቤትሽ ጋብዘሽ ያበላሻቸው ምሣ ምን ያህል ምስጋና ከአንደበታቸው እንዳሰሙሽ ባውቅም በመጽሐፉ ምንነት የተጫወትሺውን ጉልህ ሚና ከልብ ከመነጨ ምስጋና ጋር አቀርባለሁ።

ሢሣይ ንጉሤ የሽማግሌዎቹን ቃለ ምልልስ በኮምፒውተር ስለተየበሽልኝ በጣም አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም፡- የግሎባል ዲሳይፕል የኢትዮጵያ ባልደረቦቼ የእያንዳንዳችሁ ፍቅር፣ አክብሮትና ትብብር ልዘርዝር ብል ቦታ ስለማይበቃኝ እንዲያዉ ጌታ ይባርካችሁ እላለሁ፡፡

# መቅድም

ይህ መጽሐፍ የዶክተር ተስፋጽዮን ደለለው (እኔ ከቀድሞም ጀምሮ "ጋሽ ተስፉ" ነው የምለው) ግለ-ታሪክ ነው፡፡ ግለ-ታሪኩ ከብዙ ጉዳዮች ጋር የተጋመደ ነው፡፡ ለምሳሌ ጋሽ ተስፉ ከተገኘበት ብሄረሰብ ታሪክና ባህል ጋር፤ ብሄረሰቡ ይጨቆንበት ከነበረው "የገባር ሥርዓት" ጋር፤ የክርስቶስ ወንጌል በዚያ አካባቢ ከመሰበኩ በፊት ገባሪ እና አስገባሪ ይደናበሩበት ከነበረው ድቅድቅ ጨለማ ጋር፤ ወንጌሉ በእምነት በተቀበሉት ዘንድ ካስከተለው የአእምሮ መታደስ (TRANSFORMATION) ጋር፤ ወዘተርፈ፡፡

"የአእምሮው መታደስ" - እንደ ቋያ እሳት - በእጅጉ ተቀጣጣይ ነበረ፡፡ ማገዶው፣ ወቅቱ፣ ሁኔታው፣ ሁሉም ሆነ ተብለው ተዘጋጅተውለት የነበረ ነው የሚመስለው፡፡ እና ከዛፍ ወደ ዛፍ፣ ወደ ቁጥቋጦ፣ ወደ ሰንበሌጥ፣ በፍጥነት ዘለለ፡፡ ግንዶች ጋዩ፤ ቁጥቋጦች ተቀጣጠሉ፤ ሰንበሌጦች ተንበለበሉ፡፡ አራዊቱም (ተቃዋሚዎች) ከየጎሬአቸው ወጡ፤ ብርሃን እና ጨለማም ለአጭር ጊዜ ተፋጠጡ፡፡ ድል የማን እንደ ሆነ መናገር አያስፈልገኝም፡፡ መቼም የእነዚያ የመጀመሪያዎቹ አባቶች (የዛፎቹ) ምስክርነት ተሰምቶ አይጠገብም፡፡

ቁጥቋጦቹና ሰንበሌጦቹም (ወጣቶቹ እና ልጆቹ) እነዚያን ዛፎች በእግር በእግራቸው ተከተሏቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል አንዱ ጋሽ ተስፉ ነው፡፡ ጋሽ ተስፉ የእነዚያ ዛፎች፣ የዚያም ተሓድሦ፣ ተከታይ ብቻ ሆኖ ግን አልቀረም፡፡ ከፀሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያዋ ድረስ ያሉ ሌሎች ብዙዎችን ወደ ተሓድሦው ጎራ ያስከተተ ጭምር ሆነ እንጂ፡፡ እግዚአብሔር በጨለማ ለሄደ ሕዝብ ብርሃን ሲያሳይ፣ በሞት ጥላ አገር ይኖሩ ለነበሩም ብርሃን ሲያወጣላቸው (ኢሳ. 9፡2)፣ የሚሆነው ነገር ሁልጊዜም ይኸው ነው፡፡

በቀለ ወልደ ኪዳን (መጋቢ)





# መግቢያ

ከሚሸግዳ ወጥቼ ሕይወት በመራኝ መንገድ ስጓዝ ከአየሁት ሁሉ የሚያስገርመኝ ዓለም በማያቋርጥ የቴክኖሎጂ ምጥቀት ላይ መሆኗ ነው፡፡ (የተወለድኩበት አዜ-ዶቦአ ቀበሌ ያለው የእናቴ ቤት ግን ዛሬም መብራት አልገባም)፡፡ "ሕይወት" የተባለው ባቡር ከተነሳበት እስከ ደረሰበት ድረስ የሚወርደው ቁልቁለት፣ የሚወጣው ዳገት፣ የሚያቆራርጠው ሜዳ የሚሻገረው ድልድይ የሚያልፍበት ከተማና መንደር እንዲሁም የሚያሳፍረው ሰውና የሚጭነው ዕቃ እጅግ ብዙ ነው፡፡

የሰው ልጅ አእምሮም ያንን ሁሉ ወጪና ወራጅ ሃሳብና ጉዳይ በየመልኩና እንደየዓይነቱ፣ እንደክብደቱም እየፈረጀ ሰድሮ ይዞ በተፈለገ ጊዜ ያወጣዋል፤ ይዘረግፈዋል፤ (Download እንዲሉ)፡፡ ይህም መጽሐፍ ከሰባት አሥርታት በፊት የተጀመረው የሕይወት ባቡሬን ጉዞ መለስ ብዬ ስቃኝ አእምሮዬ ካቀበለኝና ያከማቸኋቸዉ ልዩ ልዩ ሰነዶቼ ከመሰከሩልኝ የተውጣጣና ለናንተ ለውድ አንባቢያን እንዲመች ሆኖ የተቀናበረ ነዉ፡፡ የረዳኝን ጌታ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡

በዚህ የሕይወት ባቡር ጉዞዬ ከአገር መሪዎች፡- ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን፣ የኬንያ የመጀመሪያዉ ፕሪዚደንት የነበሩትን ጆሞ ኬንያታን፣ የታናዛኒያውን ጁለየስ ኔሬሬን ፊት ለፊት ለማናገር ዕድል አግኝቻለሁ፡፡ ከሃይማኖት መሪዎች ደግሞ፡- ቢሊ ግራሃምን፣ ጆን ስቶትን፣ ቢሾፕ ፌስቶ ኬቬንጀሬን፣ ቢሾፕ ዴዝሞንድ ቱቱን፣ ክቡር አቶ አማኑኤል አብርሃምን፣ ቄስ ጉዲና ቱምሳን አቡነ ጳውሎስንና አቡነ ማቴያስን ተዋውቄአለሁ፡፡ ከአንደበታቸዉ ተምሬአለሁ፣ በበርካታ የጋራ ጉዳዮች ላይ ተወያይቻለሁ፡፡

ይህ ጉዞ በተጨማሪም እጅግ ብዙ ስፖርተኞችን፣ ተዋንያንን፣ ደራስያንን፣ ኢኮኖሚስቶችን፣ ፖለቲከኞችን፣ ገበሬዎችን፣ ነጋዴዎችን፣ አስተማሪዎችን፣ መሐንዲሶችን፣ ሐኪሞችን፣ አስተሟሪዎችን፣ ተመራማሪዎችን፣ ዳኞችን፣ ጠበቆችን፣

ወዘተ አስተዋወቆኛል፣ በአንድ ወይ በሌላ መንገድ አብረን ተጉዘናል፤ ከከፊሎቹ ጋርም አብረን ዘልቀናል፡፡ ከእነዚህም ሌላ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ኮንፈራንሶች ላይ ታዳሚም አቅራቢም ሆኜ ተሳትፌአለሁ፡፡

በእነዚህ አጋጣሚዎች ሁሉ ለሰው ልጅ ሁሉ መልካም የሚያስቡ፣ ለወገናቸው ብሎም ለአገራቸዉ የሚቆረቆሩ ጠቃሚና ሰላማዊ ሰዎች ጋር አብሬአቸው ኖሬአለሁ፤ ሠርቻለሁ፡፡ እንደዚሁም የገዛ ኑሮአቸውን ለመግፋት ከመታገል በቀር የተለየ ሙያ የሌላቸው ነገር ግን ቅን ሰዎችን በሰላምታቸውና በፈገግታቸው፣ በእሺታቸውና በደራሽነታቸው የሌላ ሰው ሕይወት የሚጠግኑ፣ ይህንን ከፈሉኝ ወይም ውለታ መልሱልኝ ሳይሉ ልምዳቸውንና ሃሳባቸውን ጉልበታቸውንም የሚለግሡትን አግኝቻለሁ፡፡

ሌሎች ደግሞ ነበሩ፣ አሉም፡- ሲጠጉአቸው እንደ ቅንቅን የሚኮሰኩሱ፣ እንደ ጨኪት የሚናከሱ፣ እና እንደ ሳማ የሚለበልቡ፣ እንደ ቆንጥር ከሚዋጉ አሚታዎች፡፡ ከጥቂቶቹ ጋር የሕይወት ባቡር አገናኝቶኝ አብሬአቸዉ ኖሬአለሁ፣ ሠርቻለሁም፡፡ ሕይወቴ የተቀረፀው በደጋጎቹ አጋጣሚዎች ብቻ ሳይሆን መልካም ባልሆኑትም ተሞክሮዎች ጭምር እንደ ሆነ እገነዘባለሁ፡፡ ያ በማለዳ አብሮኝ መጓዝ የጀመረው ገና በውል ሳልረዳው «እኔም ጌታን እቀበላለሁ» ብዬ በወላጅ አባቴ እግሮች መሐል ተቀምጬ የተናገርኩትን ቃል ከቁም ነገር ቆጥሮ ገደብ በሌለው ታማኝነቱ እየመራኝ፣ በአቀበቱ፣ በቁልቁለቱ፣ በወጀቡ ሁሉ በምህረት እጁ ደግፎ እነሆ እዚህ እንዳደረሰኝ ለውድ አንባቢዎቼ እመሰክራለሁ፡፡ ከእርሱም የተነሳ ነዉ ሕይወቴን ለሌሎች ለማካፈል የደፈርኩት፤ ያለ እርሱ በጎነት የለኝምና፡፡

በቅርቡ ዓመታት ዶ/ር በየነ ጭጭ አይበሉ የሚባል ወዳጄን አግኝቼ "ጋሼ በየነ ለምን መጽሐፍ አትጽፍም?" በማለት ጠየቅሁት፡፡ ከት ብሎ ሳቀና "በቁሜ ስናገር ያልሰማኝ ሕዝብ መጽሐፍ ብጽፍ ያነብልኛል ብለህ ነውን?" ሲለኝ ውስጤ





በረዬ፡፡ ጫጩት ፊት ፈንግል አይወራም እንደሚባለዉ ለመጻፍ የሰነቅኋቸዉ አላባዎች መፈነጋገሉ ጀመሩ፡፡ ዶ/ር በየነ ይቺ አገር ካፈራቻቸዉ እውቅ ምሁራን መካከል አንዱ ነዉ፤ አብዛኛውንም ዕድሜውን በማስተማርና በምርምር ያሳለፈ ሰው እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ "ታዲያ ጋሼ በየነ እንዲህ ካለማ፣ እኔስ ብጽፍ ይነበብልኝ ይሆን"? የሚለዉ ጥያቄ ወረረኝ፡፡ እውነት ለመናገር እንዳልጽፍ ወደ ኋላ ከጎተቱኝና እንደገናም ጥያቄ ከቀሰቀሱብኝ ምክንያቶች አንዱ ይህ የጋሼ በየነ ዓይነት ስጋት ነበር።

ከመጋረጃ በስተኋላ ሜዳ እንዳለ የሚታወቀው እንደ አጥር የተጋረጠውን የአመለካከትም ሆነ የእውን መሰናክል ዘልሎም ይሁን ሾልኮ ሲታለፍ ብቻ ነው። ደግሞም ካለመሞከር ይልቅ ሞክሮ መውደቅ ይሻላል፤ ከወንዙ ወዲያ ማዶ ያለውን ማን ያውቃል?! በማለት መንደፋደፍ ጀመርኩ፡፡ ግርድፍ ሃሳቦቼን ወደ ወረቀት መለወጥ ጀመሩ፤ አንደኛ ረቂቅ፣ ሁለተኛ ረቂቅ፣ ሦስተኛውን መስለቅ ጀመርኩ፡፡ ለካ አሳብ አያልቅም - ይገታል እንጂ፡፡ ቀጠልኩ . . .

ህዳር 10 ቀን 2007 ዓ.ም ረቡዕ ዕለት ከዚህ መጽሐፍ ኤዲተር ጋር ሆኜ ወደ ቤቴ እየነዳሁ ነበር፡፡ ቤቴ ስደርስ የባለቤቴ መኪና ግቢ ውስጥ አልነበረችም፤ በውቅቱ ትከሻዋ አካባቢ ሕመም ይሰማት ስለነበር መኪና መንዳት እንደማይገባት በማሰብ ልቤ ቢከፈልም "አስቸኳ ጉዳይ ቢያጋጥማት ይሆናል" ብዬ የዕለቱን ሥራዬን ማመቻቸት ቀጠልኩ፡፡ ኤዲተሬ ቡናውን ከደጋገመ በኋላ ዓይኑ ሲገለጥለት ወደ ሥራችን ገባን፡፡ የዚህን መጽሐፍ ሦስተኛ ዙር ረቂቅ ገጾች እንደ ስጥ ዘርግተን፡- አሳብ በመከመር - በመናድ፣ ነገር በማሳጠር - በማስረዘም፣ በመለወጥ፣ በመቀነስ፣ በመከለስ፣ በመጉረድ፣ በመጨመርና በወዘተርፈዉ የፊደላት ማሣ ውስጥ ሰመጥን፡፡

ባለቤቴ አምሳል የማዕድ ቤቱን በር ከፍታ ወደ ሳሎን ገባች፤ ነገሬም አላልናትም ነበር፡፡ እንደ ሕፃን ልጅ ወደ ደረቷ አስጠግታ ያቀፈችውን ውብ የአበባ እቅፍ ከፍ አደረገችና ዜማ በተላበሰ ድምፅ "መልካም ልደት!" አለች፤ እንግሊዝኛውን ከአማርኛ እያቀላቀለች፡፡ "ውይ ዛሬ ነው እንዴ የልደት ቀኔ? . . . አመሰግናለሁ አምሳል" ብዬ ወደ ፊደላቱ ጫካ ተመለስኩ፡፡

73ኛ ዓመቴን በአምሳል ምክንያት አሰብኩት፡፡ እግዚአብሔር ከከምባታ እምብርት ሚሽግዳ አንስቶ እስከ ዓለሙ የምዕራብ ጫፍ ኒውዝላንድ ድረስ ድንኳን ሲተክል ሲነቅል ሰባ ሦስት ዓመት የቆጠረለት እንደ እኔ ዓይነቱ አዛውንት፡- አረረም - መረረም፣ ከረታም - ደቀቀም፤ ለሚመጣው ትውልድ የማታ ቃሉን መተዉ የተገባዉ ነዉ፡፡ እያመነታሁ ብተወዉ ኖሮ ምንኛ የህሊና ባለ ዕዳ በሆንኩ ነበር!? በተለያዩ መንገዶች ጅምሬን ለመጀመር ድፍረት የሆነኝን ጌታ አምላኬን አመሰግናለሁ፡፡ ማንኛውም ግለ ታሪክ ጸሐፊ የሚጽፈው አንባቢዎቹን በሰልፍ ለማስደሰት ሳይሆን የሚያካፍለው ቁምነገር ሲኖረዉ ብቻ ነዉ፡፡ ደግሞም አንድ ሰው በግለ ታሪኩ የሚያነሳቸዉ የተቀነጣጠቡ ትዝታዎቹ የሁሉንም ታዳሚዎቹን ልብ እንደማይሞላ እረዳለሁ፡፡ እንዲያውም የመጽሐፉ አካል ሳይሆኑ በእግረ መንገድ የተነሱቱ አንዳንድ ትረካዎች ሙሉዕ ሐተታ ስለማይሰጣቸዉ ጥያቄ ሊያስነሱ እንደሚችሉ ከቀደምቶቼ ግለ-ታሪከኞች ተለምዶ እገነዘባለሁ፡፡ ሆኖም የያዘውን የወረወረ ፈሪ አይባልምና ጥረቴን እነሆ!

**ተስፋ ጽዮን ደሰሰው መልካ ንባብ**





# የኤዲተሩ ማስታወሻ

«ከሚሽግዳ እስከ ዓለም ዳርቻ» እግዚአብሔር ብቻውን ጉልበትና ብልሃት የሆነለት ሰው ግለ ታሪክ ነው፡፡ ሚሽግዳ፡- ለእማማ አሼንቦ «ወንድ ልጅ ተወለደልሽ» የተባለበት፣ የባለ ታሪኩ (የደራሲው) እትብት የተቀበረባት ቦታ ነች፡፡

ሚሽግዳ ከ73 ዓመታት በፊት የጋሽ ተስፋ የሕይወት ሩጫ የተለኮሰባት ሁሌም አረንጓዴና ሽሙንሙን የሆነች መንደር ነች፡፡ ነፍስ ሲያዉቅ በእረኝነት ከዚያች መንደር ተነሳ፣ ልምጩን ሰቅሎ (ጫማውን ... እንዲሉ) ለትምህርትና በሥራ አጋጣሚም ኢትዮጵያንም ዓለምንም ዞራት፡፡

«ዓለም ዳርቻ» ሲለን በሃያ ስምንት ዓመታት የውጭ አገር አገልግሎትና የሥራ ቆይታ፣ ከዚያም በፊት፣ ከረገጣቸዉ አገሮች ሁሉ ምሥራቅ ንፍቀ ክበብ ጠርዝ ላይ የምትገኘዉ ኒዉዝላንድን በልቡ ይዞ ይመስለኛል፡፡ ጉዞ ሕይወት ነዉና - ሕይወትም ጉዞ ነዉና ሩጫዉ እንደቀጠለ አለ፡፡ አሁንም በሙሉ ጤናዉ፣ በሙሉ ጉልበቱና ማስተዋሉ ላይ ስለሚገኝ ከመቃብር ወዲህ መድረሻውን የሚያውቁት እግዚአብሔርና እሱ ብቻ ናቸዉ፡፡

ከሚሽግዳ እስከ ዓለም ዳርቻ ጉዞዉ መካከል ያለፋባትና ያለፈባቸዉ ሰርጦችና ጉድባዎች ተራራና ሜዳዎች እንደ ሐምበርቾ ግዝፈት እንደ ሚሽግዳ መስከ አርጋታን አጎናጸፉት፡፡ መጣልና መሰብሰብ፣ መራብና መጥገብ፣ እንባና ሳቅ እየተፈራረቁ ለውሰዉ፣ ለውሰዉ አሁን የተላበሰውን ሰብዕና አስታጠቁት፡፡ ይህንን በይበልጥ አንባቢ የሚረዳዉ ቁጥብነቱ እየተገዳደረዉ በዝርዝር ያልነገረንን ብዙ ጉዳዮች በየመስመሩ መካከል ቆም እያልን ስናብላላዉ ነዉ፡፡

ጋሽ ተስፋ የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ በሚያምር የቁም እጅ ጽሑፉ በብዕር ሲዘረግፋዉ ሲሻ አጠገቡ ነበርኩ፡፡ በስክን ስሜት ሐምሌ 2005 ዓ.ም ጀምሮ 2006 ዓ.ም ነሐሴ

ፈጠመዉ:: አእምሮዉ ውስጥ ተሰድሮ ከርሞ ነበር - ማለት ነዉ:: እፍታዉን እንደ ወረደ ለመቅመስ የታደለዉ ይህ ኤዲተር፣ ቁጥብ ሳለ ግልጽ፣ ትሁት ሳለ ደፋር፣ በትንሽ ጥራዝ ትልቅ ሐተታ ያዘለ እንዲህ ያለ ረቂቅ በእጁ ገብቶ አንደማያውቅ ይመሰክራል::

አተራረኩ ሲበዛ ተፈጥሯዊ ከመሆኑ የተነሳ የጋሽ ተስፋን ረቂቅ ኩል መኳኳል፣ እንሰስላ ማሞቅ አላስፈለገውም፤ በርኖስ ላይ ካቦርታ መደረብ ነዉና:: እንዲያም ሆኖ የመጽሐፉ ቅንብር ለቅድመ ኅትመት አንባቢዎች በቀረበበት ወቅት የተሰነዘሩትን አስተያየቶች ለማካተት ጋሽ ተስፋ ልበ ሰፊ ነበር::

አስተያየት በመስጠት ረገድ ከእረኝነት ጓደኞቹ እስከ መሥሪያ ቤት ባልደረቦቹ፣ ከሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች እስከ መጽሐፍ ቀበኞች (የንባብ ጥመኞች)፣ ከባለቤቱ እትዬ አምሳል እስከ ጉምቱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ድረስ ተሳትፈውበታል:: ስለሆነም በእርጋታዉ ላይ እርጋታ፣ በጥንካሬዉ ላይ ሌላ አቅም ጨምረውለታል::

የጋሽ ተስፋን ትዕግሥት የተፈታተነዉና የዚህ ኤዲተር ዋነኛዉ ኃላፊነት እኒህን ማንጓለልና ተገቢዎቹን በተገቢዉ ቦታ መሰካካት ነበር::

ጋሽ ተስፋ በዚህ ሥራ ከጀርባህ እንድቆም ስለ ሰጠኸኝ ዕድል አመሰግናለሁ::

**ወንድዬ ዓሊ**





# ምዕራፍ አንድ

# መሠረቴ - ዙሪያ ገባዉ

## 1. ትውልዴና የሕይወቴ ሀ ሁ

አያቴ ዋቤቶ ሳካሎ ድላባ ለአቅመ አዳም ሲደርሱ ካገቡአቸው ከመጀመሪያ ሚስታቸው ሁለት ወንዶችና አምስት ሴቶች ልጆች ወልደዋል። ወንዶቹ ልጆች በሻና ዶፌ ሲባሉ ሴቶቹ ደግሞ ደንቶ፣ ሌሌቤ "ለጅቤ" ሎምባያና ሳደሜ ይባላሉ። ወንዶቹ በሻና ዶፌ በጣም የታወቁ ፈረሰኞች ነበሩ፤ "የአላባ ጦርነት" ተብሎ በሚታወቀው የጎሣ ግጭት ሲገደሉ ሴቶቹ አግብተው ወልደው ልጆችና የልጅ ልጆች ሁሉ አቅፈውና ስመው አሳድገው የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ነፍስ ባወቀበት ዕድሜ ተራ በተራ ወደማይቀሩበት አለም አልፈዋል::

የአቶ ዋቤቶ ሁለተኛ ሚስታቸውና የእኔ አያት በቤት ስማቸዉ እዳዬ በመባል የሚታወቁት ወ/ሮ ዋኖሬ ሐረቼ ይባላሉ። መቼ እንደተጋቡ በውል የሚያስታውስ ሰው አላገኘሁም እንጂ እዳዬ የአባቴን እባት ዋቤቶን አግብተው አራት ወንዶች ልጆችና ሦስት ሴቶች ልጆች ወልደዋል። የዋቤቶ አራተኛው ልጅና የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ እባት የስድስት ወይም የሰባት ዓመት ልጅ ሳሉ አቶ ዋቤቶ ባደረባቸው ሕመም ምክያት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

እንደማንኛውም የገጠር ኑሮ ማታ ማታ ምድጃ ከቦ እሳት እየሞቁ ተረትም ታሪክም መስማት የተለመደ ነዉ:: በእግረ መንገድም ማሕበራዊ ግንኙነቶች ሁሉ በከፋም ሆነ በደግ መነሳታቸው አይቀርም:: ታዲያ አባቴ በተደጋጋሚ ከሚነሱት የምድጃ ዳር ወሬዎች መካከል አንዱን ወደ ጎረቤቶች እንዴት እንዳሻገሩት የልጅነት ትዝታቸውን ሲናገሩ ከሰማሁት እኔም አንዱን ልጥቀስ::

በእሳት ዳር ተቀምጠው እናታቸው ገንዘብም ሆነ ሌላ ንብረት የተበደሩአቸውን

የጐረቤት ሰዎች ስም እልፎ አልፎም ቢሆን ያነሱ ነበር፡፡ "እከሌና እከሊት ተበድረው አልመለሱልኝም" ሲሉ የአባባ ጆሮ ከወትሮው ይልቅ ይቆማል፤ በልባቸው መዝግበው አድረው ሲነጋ በማለዳ ተነሥተው ወደ ተባሉት ተበዳሪዎች ቤት ሄዳው "የወሰድከውን የወሰድሽውን ውለህ/ውለሽ ሳታድሪ ወይም ሳታድር እንድትልኩልኝ ብለዋል" በአማልክቱ ስም ገዝተው ባለዕዳዎቹን ያስከፍሉ እንደነበረ በሰፊው ይነገር ነበር። እናታቸው ታዲያ "ምነው ልጄ አሳፈርከኝ?" በማለት ይቆጧቸው እንደነበረ እኔም ከአባባ አንደበት አድምጫለሁ።

ይህንኑ የሚመስል ሌላው የአባባ ነገር ከፍ ብሎ አባታቸው በልጅነታቸው እንደሞቱባቸው የተጠቀሰ ሲሆን "ቱማቴ" የሚባል በአካባቢው ፍርሃት እየዘራ የኖረ ጠንቋይ "እኔ ነኝ የገደልሁት፤ አሁንም ፈረሱን፣ በሬውን እና ይህንን ያህል ጥሬ ብር ካልከፈልሽ ልጆቹንም እፈጃለሁ" በማለት አስፈራርቶ የወሰደውን ንብረት በሕጋዊ ፍርድ ቤት ከሰው እንዳስከፈሉትም አውቃለሁ።

አያታችን አቶ ዋቤቶ ከአባታችንና ከሌሎችም ከደረሱባቸው ሰዎች ሲወራ እንደነበረው ለመናገር የማይቸኩሉ ብዙ ካጤኑና ከአስተዋሉ በኋላ በአውጫጭኝም ሆነ በሌላ ሽምግልና "ምነው ዝም አሉ?" ሲባሉ ብቻ አሳብ በመስጠት ወደሚያስማማ ውሳኔ አሳብ የሚመሩና በዚህም የታወቁ ተወዳጅና ተከባሪ ሰው እንደነበሩ ይነገራል። በተጨማሪም የተመሰከረላቸው ወጌሻም ነበሩ፡፡ ሰውም ሆነ እንስሳ በወሊድ ጊዜ ምጡ ሲጠናበት በቅድሚያ የሚጠሩት እሳቸዉ ነበሩ፡፡ ስብራትን በመጠገን ውልቃትን በመመለስ የታወቁና ለመርዳትም ወደ ኋላ የማይሉ ሰው እንደነበሩ ይነገርላቸው ነበር። በባሕርያቸው ደግሞ ገራም፣ ርህሩህና ተወዳጅ ሰው ነበሩ ይባላል።

የእርሳቸው ልጅና የዚህ የጸሐፊ ወላጅ አባት ግን የአባታቸው ነው ከተባሉት የሙያና የመልካም ተግባር ጥቂቱን ቢወርሱም በተለይም የእጁ ሙያ ግን ሲያልፍም





አልነካቸው። አንድ ጊዜ ከፈረስ ወድቄ የቀኝ ትከሻዬ ወለቀና በቦታው ሳይመለስ እየቆየ ሲሄድ ሕመሙ እየባሰ እንቅልፍ እስካጣ ድረስ አሰቃየኝ፡፡ ቆይቶም ቢሆን በአማማ ግፊት ወደ አንድ ጐረቤታችን ሽማግሌ ዘንድ ተወሰድሁ። ሰውዬው የወለቀ ትከሻ መልሶ በቦታው ማስገባት ቀርቶ ምኑንም ከምን መለየት የማይችሉ በመሆናቸው የጨመሩብኝ ስቃይ እየታወሰኝ እስከዛሬ በጥሩ የማላስባቸው ሰው ሆነው በአእምሮዬ ተስገው ቀሩ፡፡ ታዲያ ለዚያ ስቃይና እንቅልፍ ማጣት የዳረገኝ አባቴ የአባቱን ሙያ ወርሶ ባለማቆየቱ ምክንያት መሆኑን አምናለሁ። በዚህ ረገድ የኔም ትውልድ ሆነ ከኔ በኋላ የመጡት ሦስት ወይም ከዚያ በላይ ትውልዶች ከባህላዊዉ እውቀት፣ ጥበብና ብልሃት እያደር መነቀላችን በግል የአኗኗር ዘይቤአችንንም ሆነ በጠቅላላውን የአገራችን ሁለንተና ላይ እንዳች ያጎደለ ወይም እንደገና የማንሞላው ሽለቆ የከፈተ ይመስለኛል፡፡

## መልከዓ ምድሩ

ዞሪያ-ገባዉ ሚሽጊዳ ይባል እንጂ ብዙ መንደሮችንና ቀበሌዎችን ያጠቃልላል። ሚሽጊዳ በምሥራቅ እስከ ዱራሜ ከተማ ሲዘረጋ ሾደራን፣ ጦጠንቄን፣ ቤናራን፣ ጠቆራን፣ ዊጤን፣ ዶቦአንና አዜን ጨምሮ በስተ ደቡብ ሕልፈታን ያዋስናል፤ አዜ ደቦአ ደግሞ የሐምበሪቾን ተራራ በስተሰሜን አድርጐ የጨጫ ተራራ ደግሞ ከሐምበርቾ ጋራ ተያይዞ ሆን ብሎ ለመከላከያ የተገነባ ታላቅ ግንብ ይመስል የቆመ ነው። ከሐምበርቾ በስተደቡብ ከጨጫ በስተምዕራብ ደግሞ እኔ ነኝ ያለ ሰንጋ ፈረስ በአንዴ ሽምጥጦ የማያቋርጠው ለጥ ያለ ሜዳ ይገኛል፡፡ ደቀያ ሜዳ ይሉታል፤ በየቀኑ በሺህ የሚቆጠሩ ቀንድ ከብቶች የጋማ ከብቶች እና በጐች የሚሰማሩበት ሁልጊዜ አረንጓዴነቱ የማይከስምበት መስክ ነዉ።

ከዚያው ከሐምበሪቾ ተራራ ሥር የሚፈልቁ ሁለት ወንዞች አሉ፡፡ ተከቡሌና ኮሮዋ ይባላሉ፡፡ ከሁለት ምንጮቻቸው ፈልቀው ከሰማይ ጠል በታች ሰውንም ሆነ

እንስሳውን እያጠጡ በመሬታችን ተገናኝተዉ ወደ ታች ይፈሳሉ፡፡ ኮሮዋ የተባለው ወንዝ  በክረምቱ ወራቶች የሚገኝና በበጋዎቹ ወራቶች ደግሞ የሚመነምን ጠባይ አለዉ፡፡ ተከቡሌ ግን በክረምትም በበጋም የማይደርቅ እንደ ክረምቱ ወራት በሙላት አካባቢውን ባያጥለቀልቅም የሚሰጠውን ግልጋሎት የማያቋርጥ ታማኝ ወንዝ ነው። በቅርቡ ግን  የ"ልማት" ሰለባ ሆነ፤ ቡና ማጠቢያ መኪና ተተክሎበት በሰውም ሆነ በእንስሳቱ ላይ ፍዳ እያስከተለ ሲሆን ለራሱም ቢሆን አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል። ማንኛውም የልማት ሥራ የባለሐብቱን አትራፊነት ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ስነምህዳርና በነዋሪው ሕዝብ ላይ ምን ያስከትላል ተብሎ በጊዜው በወጉ ጥናት አስፈላጊው ቢሆንም በውሃው ላይ የተደረገበት ልማት አልነበረም፤ ወደ ወንዙ የሚገባዉ እጣቢ ውሃ ለሰውም ለእንስሳም የጤና ጠንቅ ከመፍጠሩም በላይ በበጋው ወራት ለከፍተኛ የውሃ እጥረት ሕዝቡን ዳርጎታል።

ወደ አዜ-ዶቦአ ልመለስና ቅዳሜ ዕለት ዱራሜ ሰኞ ደግሞ ሺንሸቾ ትላልቅ ገበያዎች ይውላሉ። ደቀያ ሜዳ ላይ ከብት ስናግድ ቅዳሜ ዕለት ጧት ወደ ሦስት ሰዓት ጀምሮ ገበያተኛው ሸህሙን ተሸክሞ ከብቱን እየሳበና እየነዳ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ የሚተምመውን ሕዝብ ማየት አንዱ ትርዒት ነበር። ገበያተኛው ሲሄድም ሆነ ሲመለስ አንዳንዱ ሸንኮራውን እያኘከ ሲሄድ ተለቅ ያሉት እረኞች ራሳቸው ካልሆነም ትንንሾቹን "ሸንኮራ ስጡኝ"።  ብለው ይለምናሉ ወይም ያስለምናሉ። ሁል ጊዜ ውጤታማ ልመና ባይሆንም ሁሌ ከንቱ ስለማይሆን ልመናው ይቀጥላል። አንዳንዱ ሰው የጐረሰውን ብቻ እያኘከ የቀረውን ለልጆቹ ሰጥቶ ያልፋል።

## 2. ልጅነቴ - በተንገጫገጨ ቤተሰብ ውስጥ

አያቴ አቶ ዋቤቶ ሳከሎ ከሁለቱ ሚስቶቻቸዉ የተወለዱት አጎቶቼና አክስቶቼ አሥራ አራት ናቸዉ። ከመጀመሪያዋ አያት (ከአያቴ ዋቤቶ ሚስት) አምስት ሴቶችና ሁለት ወንዶች፣ ከባቴ እናት ደግሞ አራት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ተወለዱ፤ የኔ





አባት አራተኛው ልጅና ሦስተኛው ወንድ ልጅ ነበሩ። ከአባቴ ከዳለሎ ጋር ከአንድ ማሕፀን የተገኙ አጐቶቼ ፈታሞ፣ ዳልበቶና መንታሞ ሲባሉ  አክስቶቼ ደግሞ ኬሻሜ፣ ሎዳሜና ምልከሴ ይባላሉ። ከሁለተኛዋ አያቴ የተወለዱት ሁለት ወንዶች ልጆች  በሻ እና ዶፊ የሚባሉ ሲሆን ሴቶቹ አክስቶቼ ደግሞ ደንቶ፣ ለጅቤ፣ ሌሌቤ፣ ሎምባያና ሣደሜ ይባላሉ። ለእናቱ ብቸኛ የማሕፀን ፍሬ የነበረ ደግሞ ኤደሞነበር፡፡

ከሁለት እናቶች ከተወለድነው የደለፌ አስራ አምስት ልጆች መካከል ሁለት ወንዶች በአምስትና ስድስት ወር ዕድሜያቸው ሲሞቱ የቀረነው አስራ ሦስት ዛሬም ድረስ በሕይወት አለን። እኔ እስከወለድ ድረስ ለዋቤቶ ልጆች በተለይም ለአጎቶቼ ሌላ ወንድ ልጅ አልተወለደም ነበር። በሕፃንነታቸው ከሞቱት የአባቴ ልጆች አንዱ ከኔ አስቀድሞ የተወለደ ነበር። እናቴ ግን ከኔ በኋላ ሰናይትን፣ ዘውዴን፣ ወልዴን፣ ዘነበችን፣ ዜናን እና ታደሰን ወልደዋል፡፡ ወ/ሮ ሠናይትና ወ/ሮ ዘውዴ እያንዳንዳቸው የሰባትና የስምንት ልጆች እናቶች ሆነው የልጅ ልጆችም አፍርተዋል፡፡ አቶ ወልዴ የወ/ሮ አልማዝ ባለቤት በኢትዮጵያ አየር መንገድ የአውሮፕላን ሞተር መካኒክ ሆኖ ሲሠራ ቆይቶ በጡረታ ሲሰናበት ለረጅም ዘመን በምሥራቅ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አመራር እያገለገለ የአራት ልጆችና የልጅ ልጆችን ከብር ለማየትም ታድሏል። ወ/ሮ ዘነበች ደግሞ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ (ወንጌላዊት) ስትሆን ባለቤቷ አቶ ሣህለማርያ መናሞ ይባላል፡፡ ወ/ሮ ዜና በአንድ ክርስቲያናዊ ድርጅት ትሠራለች፤ በተጨማሪም በቦረቻ (ሲዳማ) መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በሸምግልና ታገለግላለች። አቶ ታደሰ የወ/ሮ ወርቃአበባ ባለቤት፣ የሁለት ወንዶችና የሁለት ሴቶች አባት ሲሆን፣ በሙያዉ መሐንዲስ፣ ሥራውም ተቋራጭ ነው። በኮተቤ መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን  በተለያዩ ኃላፊነቶች በማገልገል ላይ ይገኛል።



**እናቴ**

እግዚአብሔርከአንድ ማሕፀን ፈጥሮ ወደዚህች ዓለም ያመጣን ከእናታችን ጀምሮ ሁላችንም ያለነው በጌታ ቤት አገልጋዮች እንድንሆን ስለሰጠን ዕድል ፈንታ ክብርና ሞገስ ለእርሱ ይሁን። ነፍስ ካወቅሁ ጀምሮ የወላጆቻችን ትዳር እንደ ተንቃነቀ ጥርስ ስለነበረ የተወለድነው ሁላችንም ከመቼ መቼ እንበታተናለን በሚል የስጋት ዓለም እንኖር እንደነበር አስታውሳለሁ። "የፈሩት ይደርሳል፣ የጠሉት ይወርሳል" እንደተባለው የአበው አባባል የፈራነውም የጠላነውም አይቀሬ ሆነና በ1947 ዓ.ም እውን ሆነ። ታሪኩ እንዲህ ነው፤ አንዳንድ ፎቶግራፍ ከታየ በኋላም እንኳ ቢሆን ምስሉ በሰው አእምሮ ተስሎ እንደሚቀር እናቴ የመጨረሻ ልጃቸውንና ወንድሜን ታደሰን የአንድ ዓመት ተኩል ልጅ ሳለ አዝለውና እህቴን ዘነበችን አስከትለው ከቤት ወጡ። ፈጠን ፈጠን እያሉ ከቤታችን ፊት ለፊት ያለውን የደቀያን ሜዳ በማቋረጥ ከሜዳው ቀጥሎ ያለውን የጨጫን ተራራ ለመውጣት ሲያያዙት በመንገዱ ግራና ቀኝ ያሉት ዛፎች እስኪከልላቸው ድረስ ዓይኖቼ ተተክለውባቸው ተስፋው ሁሉ ጨልሞብኝ የት እንዳለሁ እስኪጠፋኝ ድረስ የቆምሁበት እግሮቼ ሲከዱኝ ይታወቁኛል። ድንጋጤው ለቀቅ ሲያደርገኝ ከእንቅልፍ እንደነቃ ሰው ብንን ብዬ ጎረቤታችንና





ጓደኛዬ ወደሆነው ወደ ዮሐንስ ምርከኖ ቤት ሄድኩ።

ዮሐንስ አባቱም እናቱም በልጅነት ሞተውበት ራሱ አባወራ ሆኖ ያደገ የትንሽ ትልቅ ነበር። የቤታቸውን አጥር እያጠባበቀ ነበር። እንዳየኝም "ምነው ፊትህን አኮሳተርከው?" አለኝ፡፡ እንደ ኮሶ መራራ የሆነውን ታሪኬን ልተርክለት ስጀምር በዓይኖቼ እንዲፈስ ያልጋበዝኩት እምባ እየወረደ መናገር እንዳቃተኝ አስታውሳለሁ። የሚገርመው ነገር በአንድ ካፌ ውስጥ ቁጭ ብዬ ይህንን ታሪክ እያስታወስኩ ስጽፍ በነበረበት ሰዓት ከቁጥጥሬ ውጭ እምባዬ ረገፈ፡፡ ሰዎች እንዳያዩኝ በመሐረቤ ጠራርጌ፣ ጥቂትም ቆም ብዬ ስሜቴን ማረጋጋት ነበረብኝ። አባቴ የኔን እናት አግብተዉ ሦስት ልጆች ከወለዱላቸዉ በኋላ የአንድ ወንድም እና የአምስት እህቶች እናት የሆኑትን ሁለተኛዋን ሚስታቸውን ሴጎን አገቡ፡፡ ከሁለተኛዋ እናታችን ሁለት ወንድና (አንዱ ሞቷል) አምስት ሴቶች (የመጨረሻዎቹ መንትያዎች) ከአፈሩ በኋላ እሳቸውንም እንደገና ፈቱ፡፡ የእኔን እናት ከመፍታታቸው ከአንድ ዓመት አስቀድሞ ደግሞ ወ/ሮ ማርታ የሚባሉትን ሦስተኛዋን ሚስታቸውን ሲያገቡ የቤተሰባችን ምስቅልቅል እኔ ነኝ ካለ ማጥ የጠለቀ ነበር። የመጀመሪያዎቹ አስራ ሰባት ዓመታት በተለይ እማማ ከባድ ቀምበር የተሸከሙበት አስቸጋሪ ዓመታት ነበሩ፡፡ የመከራ ዓመታቸዉ እንዴት እንዳለፈና በመከራ የዘሩትን በደስታ እንዴት እንዳጨዱ ኋላ እመለስበታለሁ፡፡

***

አሁን ሰባ ሦስት ዓመቴ ነዉ፡፡ የልጅ ልጆችን ከአፈራሁና የማታ እንጀራዬን እያጣጣምኩ፣ ላለውና ለሚመጣው ትውልድ አወርሰዉ ዘንድ የሚገባኝን እያሰላሰልኩ ሳላሁ አንዳንዴ ልቡናዬ ወደ ኋላ ያምዘገዝገኛል፡፡ የልጅነት ወራቴን እንደ ፎቶ ማጎደር ያሳየኛል፡፡ እናም በክንፎቹ ተሸክሞ አሁን የሆንኩትን ለመሆን ያስቻለኝን ጌታ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ እንደ ሳይንሱማ ቢሆን ኖሮ በኋላ



እናቴ

ቀር ልማድና ማሕበራዊ መስተጋብር ውስጥ እንዲሁም እኔ በግሌ በወላጆቼ እንግጭግጭ ትዳር አልፎ እዚህ መድረስ ሳይሆን ለሚሸግዳም ሕይወት ዕድል ፈንታ ባልኖረኝም ነበር፡፡

ምክንያቱም የወላጆች ትዳር መፍረስ በልጅ ላይ የሚያመጣው ያለመመቸት ልኩ በውል የሚታወቀው የፍቺዉ እውነተኛ ሰለባ በሆኑት በልጆች ዘንድ ብቻ ነው፡፡ በተለይም በገጠር ማሕበረሰብ ሁሉም ንብረት በወንድ ቁጥጥር ስለሚተዳደር ትዳር ፈርሶ ቤትና ከቤቱ ጋራ ያለ ንብረት ሁሉ እዚያው ወንዱ ቤት ሲቀር ሴቷ ግን የሚጠባ ልጇን መንታም ቢሆን አንጠልጥላ ነው የምትሄደው።

ምንም ዓይነት የተተለመ የገቢ ምንጭ ሳይኖር የሚቀመስ የሚላስ ከጐተራ የሚዛቅ ወይም ከጓሮ የሚበጠስ ሚሣይ በሌለበት ሁናቴ አንድ ወንድ የትዳር አጋሩን፣ የልጆቹን እናት ማባረር ማለት ጭካኔ እንጂ ሌላ ምን ቋንቋ ይገልጠዋል? በአብዛኛዉ በወንዱ ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሠረተዉ ፍቺ ትዳሯን ብቻ እንደ ሕይወት ዋስትና ለቆጠረች የቤት እመቤት  ቅስሟን የሚያንካክት፣ ቀሪ ዘመኗን የሚያሸመደምድ፣ ሜዳውን ገደል የሚያስመስል ተስፋ ገዳይ ክስተት ነዉ።

በሽማግሌ ወይም በፍርድ ቤት ዳኝነት ንብረት ለመካፈል ቢችሉ እንኳን የትዳር መፍረስ በልጆች ላይ ምቾትን፣ በራስ መተማመንን (Self confidence) ይነሳል፡፡ አብሮ አደግ ጓደኛ ያሳጣል፤ የጨዋታ ስልቱ እንኳን ሳይቀር ይለወጥበታል። ቀዬው አካባቢው ሁሉ አዲስ ነው የሚሆንበት። እስከ ዛሬም ድረስ በማሕበረሰባችን እንደ ዘበት የሚታየዉ ፍቺ በልጆች ላይ የሚያስከትለዉ አካላዊ፣ ስነ ልቡናዊ፣ መንፈሳዊና አእምሯዊ ጉዳቶች ልክና ዳርቻ የለውም፤ በውል ተጠንቶ ኪሣራዉን ስለማናስበዉና የተፅዕኖ መጠኑ ይለያል እንጂ ጫናዉን እንደተሸከምን አለን፡፡

አንዳንዴ እላለሁ፡- ሚስትን የሚፈታ ባል አባትነትንም ጭምር ይሆን የሚፈታው? ካላሳሰበለት፣ ካልተጠነቀቀለት ልጄ የሚያሰኘው ያ አንድ ቀን የሆነው በፍቅርም





ይሁን በሌላው ግንኙነት የተዘራው ዘር ብቻውን አባት ያሰኛል ቢባል በቂ አይደለም። ከተጠያቂነት የወጣ አባት ስሙ (ማዕረጉም) አብሮ ቢቀነስ ይሻላል። ፈረንጆች ‹የታጣ አባት (Missing father)› ይሉታል።

የወላጆቼ ትዳር ከፈረሰ በኋላ በአእምሮዬና በስሜቴ የደረሰብኝ መዋለል ቀላል አልነበረም፤ ለናሙና ያህል ጥቂቶቹን እንደሚከተለው እገልጻለሁ፡፡ ከመስከረም እስከ ሰኔ አሥር ወር ተቆጥሮ ትምህርት ቤት የዓመቱን ሥራ ጨርሶ ይዘጋል። ተማሪዎች ሁሉ ለቀሩት ሁለት ወራት ወደ የመጡበት ይሄዳሉ። ሁሉም ተማሪ ወዳለው ወላጅና ዘመድ ይሄዳል ምክንያቱም ከአሥሩ ወራት ጋራ የዓመቱ ትምህርት ሲያልቅ አስተማሪም የለም። ቢሮውም ዝግ ነው፤ የሚቀር ተማሪ እንኳን ቢኖር በተለየ ያላለቀና የሚያስረክበው ሥራ ከሌለ ዘበኞቹም ያስወጡታል።

ከወላጆቼ መለያየት በኋላ የትምህርት ቤት መዘጊያ ሲደርስ ጉጉቴ እየከሣብኝ የተለየ አሳብ  ይገባብኝ ጀመር፡፡ ቀድሞ ወደ ወላጆቼ ለመሄድ የትምህርት ቤት መዘጋት የሚያጓጓኝን ያህል አሁን እንደ ወንዝ ሙላት የሚያስፈራኝ ሆነ። የወሊጆቼ መለያየት ሳላውቀው ውስጣዊ ደስታዬን በእጅጉ ሠረቀዉ፡፡ ማንኛቸው ዘንድ ምን ያህል ጊዜ ልቆይ? ማንኛቸውስ ጋ ቀድሜ ልሂድ? የሚሉ ያልተለመዱ ጥያቄዎች ውስጤን ያስጨንቁኝ ጀመር። ይሁን እንጂ መሄዴ አይቀሬ ነውና መጀመሪያ ወደ አባቴ ቤት ከዚያም ጥቂት ቀን አሳልፌ ወደ እናቴ መሄድ ማቀድ ግድ ሆነብኝ። አንድ ላይ ሆነው ቤት ስደርስ ማንኛቸውን አስቀድሜ ልሳም እል የነበረው ቀረ። አሁን ያለኝ እድል አንዳቸውን (አባቴን) ስሜ  ውዬ አድሬ ርቀቱን ተጉዤ እናቴን ማግኘት ሆነ። አንዱም ያልተመቸኝ ይኸ ነበር።

በፊት ወላጆቼ ቤት ስደርስ የሁለቱ ወር እረፍት ተጀመረ ማለት ነበር። ከተለያዩ በ፡ኋላ ግን በሁለቱ መኻል መመላለስ ምቾቴን ቀንሶ ዕረፍቴን ተሻምቶብኝ ወደ ትምህርት ቤት መመለሱ ቶሎ አልደርስ ይለኝ ጀመር። እያደርም ሁለቱን ወራት

ማስለፊያ አማራጮች አስቀድሞ መፈላለግ ጀመርኩ። በዚህ ምክንያት የ1952 ክረምት ከአሰላ ዘጠነኛ ክፍል ጨርሼ ሻሸመኔ (ኩየራ) ከነበረችው የአክስቴ ልጅ ዓለሜ ጋር ቆየሁ። ባለቤቷ አቶ ሙላቱ (አሁን ዶ/ር) ለትምህርት አሜሪካን ሄዶ ነበር። በዚያው ክረምት ወደ ይርጋዓለም አቤላ፣ ዲላ ወዳሉት ዘመዶቼ ዘንድ ጥቂት ቀናትና ሳምንት እየቆየሁ የዕረፍቱን ጊዜ ጨረስሁት።

ከዚህ በኋላ በየክረምቱ ወደ ወላጆቼ ያለመሄዱንና ሁለቱን የክረምት ወራት ትንንሽ ሥራ ፈልጎ በመሥራትና በተለያዩ ከተማዎች ያሉትን ዘመዶች/ጓደኞች በመጠየቅ ማሳለፍን ተለማመድሁት። ይህ ሲሆን ደግሞ የተሻለ ዕረፍትና ደስታ የሚሰጠኝ እንደሆነም ተረዳሁ። በተለይም በ1950 ዓ.ም. ከሰባተኛ ክፍል ወጥቼ በሻሸመኔ የSIM ግቢ ይሰጥ የነበረውን የአንድ ዓመት የጤና ረዳትነት (Dresser) ትምህርት መማሬ በእጅጉ ረዳኝ። ዓላማዬም ግቡን ጥሩ አድርጐ መታልኝ። ከመጀመሪያም አስቤበት የገባሁት ይህ የጤና ረዳትነት ትምህርት ያኖረኛል ብዬ ሳይሆን ለመሸጋገሪያ ይረዳኛል በሚል ነበር የታቀደው። ይህ ትምህርት ለክረምት ሥራ ነበር የታቀደው። ነገር ግን ለገናና ለፋሲካ ዕረፍት ትምህርት ቤት ሲዘጋ እኔ በቀላሉ የአጭር ጊዜ ሥራ እያገኘሁ በተለይም በናዝሬት (አዳማ) በሚገኘው ኃይለማርያም ማሞ መታሰቢያ ሆስፒታል መሥራቱ የዕረፍቴን ጊዜያት ማሳለፊያ ከመሆኑም በላይ ለኪሴ በጣም ያስፈልገኝ የነበረውን ገቢ ያስገኝልኝ ጀመር:: ያችን ሣንቲም እያቃጨሉ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ በጣም ደስ የሚል ከመሆኑም ሌላ ለማንኛውም ትንንሽ ወጪዎች የሰው እጅ መከጀሉ አበቃ። አቤት ያ ሁኔታ ይሰጥ የነበረው ደስታና ነፃነት!

መቼ ይህ ብቻ ለተናናሾቼም መደጎሚያ ትንሽ ትንሽ የሚያስፈልጋቸውን ለማድረግ መቻል እንዴት ያለ ደስታና ኩራት ነው:: ከእነዚያ አንዱን ክረምት ወንድሜ ወልዴ ባልታወቀ ህመም ተምሞ ከስቶ መጣ:: ያኔ የምኖረው ናዝሬት ነበር:: የመረመረልኝ ሐኪም ርሁማቲክ አርትራይተስ ነው ብሎ መድኃኒት አዘዘለት:: ያንን መግዛት መቻል ሌላዉ ደስታዬ ነበር::





# ምዕራፍ ሁለት
# የቤተሰባችን ሃይማኖታዊ ዳራ

## 3. ቅድመ ወንጌል ሃይማኖት በከምባታ

ከግራኝ መሐመድ ወረራ በኋላ ፈንዳኖ/ፈንዳነኖ የሚባል የቀጣጠነ እስልምና የሚመስል ሃይማኖት በሃዲያ ደቡብ ከምባታ በኩል ከባደዋቾ ወደ ሰሜኑ ክፍል እንደመጣ ሽማግሌዎች አስረግጠው ይናገራሉ። የቀጣጠነ እስልምና ለተባለው አለባቸው ኬዕሚሶና ሳሙኤል ሀንዳሞ በ2002 ዓ.ም. "የሀዲያ ሕዝብ ታሪክና ባህል" በተባለው መጽሐፋቸው ሲያስረዱ "ፈንዳኖ ሃይማኖታዊ ሥርዓታቸውን የሚመሩበት መጻሕፍት የሌላቸው ከመሆኑም በላይ ውስን የአምልኮ ማዕከል የላቸውም" ብለዋል።[1] ፈንዳኖ በዚህ አይገደዱም። በጥቅምት 25ቱ የሽማግሌዎች ስብሰባችን ሽማግሌዎች ሲያስረዱ "ከ10 ቀን ጀምሮ 15/17 ድረስ ይጾማሉ" ብለዋል። ይህንንም የሚጾሙት በባሕሉ ደንብ የተገረዙት ወንዶች እንደሆኑም አስረድተዋል።

የሽማግሌዎቹም አገላለጽ የአለባቸውና ሳሙኤል "ፈንዳኖ ስለመሆናቸው የሚገልጹት ጸጉራቸው ላይ ማበጠሪያ በመሰካት መፋቂያ ጆሮ ግንዳቸው ላይ በማኖር እንደሚገልጹ አጽንተዋል/ አረጋግጠዋል። በዛር፣ በወንዝ፣ በተራራ ማምለኩ እንደቀጠለ ነበር። ይህም የውክልና አምልኮ ይመስላል። ለምሳሌ ሁሉ የሚያውቀውና የሚቻለው አምላክ መገኖ/ዋአ ነው (ከምባትኛና ሐዲይኛ) የሚጾመው ጾም ሦመና ይባላል። አቶ ሻሜቤ መኪሶ ሲናገሩ ሰው ለማያውቀው አምላክ (ለሰይጣን) እየሰገደ ጥንቆላና ጠንቋይ የገነነ ስለነበረ ሰው ሲሞት ቃልቻው እኔ ነኝ የገደልሁት እያለ መፎከር ብቻ ሳይሆን (ባተነታ) ከከፍያ ይጠይቃል፤ ፈረሱን፣ ጋሻውን፣ ጦሩንና ልብሱን ሳይቀር ይወስድ ነበር "ብለዋል" (ጥቅምት 23 ቃለ ምልልስ)

[1] አለባቸው ኬዕሚሶና ሳሙኤል ሀንዳሞ፤ የሀዲያ ሕዝብ ታሪክና ባህል 2002ዓ.ም. ገጽ 224

## የአባቴ ሃይማኖቶች

አባቴ ወደ ፈንዳኖነት ሁለት ጊዜ ተለውጠዋል።[2] የመለወጡ ሥርዓት ያለ ምንም ካህን ወይም መሪ ተለዋጮቹ ራሳቸው አስቀድመው ጢማቸውን ተላጭተው ጥፍራቸውን ቆርጠው ሲነጋጋ ወደ ወንዝ ሄደው ይነከራሉ፣ ይታጠባሉ፣ ይፀዳዳሉ። ከዚያ ወደ ቤት ሲመለሱ ከየጫካው አበባ ቀጥፈው በራሳቸውና በጆሮአቸው ሰክተው ወደ ቤት ሲገቡ ሥርዓቱ ተጀመረ ማለት ነው። ይህ ሥርዓት ሐይባና ሲባል ጾሙ አሥራ ሰባት ቀን ሲፈጅ ሦመና ይባላል። ይህ ፆም ወንዶቹን እንጂ ሴቶችን አይጨምርም። ከወንዝ ወደ ቤት ሲመለሱ በተለይ ለዚህ የሚሠራ "ቡሎ" የሚባል ምግብ ይዘጋጃል። ቡሎ ከገብስ እንደ በሶ የሚዘጋጅ ሲሆን በቅቤ የረሰረሰና እንኳን የበላ አፍ ቀርቶ የያዘው እጅ በቅቤው ይነከራል። ቡሎ ከመበላቱ አስቀድሞ ግን የምግቡ እፍታ ከአናቱ ተቆንጥሮለት ውጭ ተወስዶ በዛፍ ሥር ወይም በእንስት ሥር በኮባ ተደርጎ ይቀመጣል። መስዋእት መሆኑ ነዉ:: አንዳንዴ ግን ጮሌ ልጆች ተሸሽገዉ ይበሉታል::

በቅርቡ ይህንን ርዕስ አንስተን ከቤተሰብ ጋር ስንጨዋወት አንድ ቀን ወንድሜ ታደሰ ልጅ ሆኖ ከሌሎች ልጆች ጋራ ሆነው ወደ ውጭ የሚወስደውን ምግብ አምላኪው ሰው አድርሶ ወደ ቤት ሲመለስ ጠብቀው ቦታውን አጣርተው ከአዩ በኋላ ፈጥነው ከቦታው ሄደው ተሻምተው በልተው የቤቱም እንዳያመልጣቸው ቶሎ ብለው እንደሚመለሱ አጫውቶኛል። ታዲያ ያ ውቃቢ ጋባዡ ሰው ጧት ማልዶ ይነሣና እንግዶቹ ያስቀመጠላቸውን ተጋብዘውለት እንደሆነ ቀስ ብሎ ያይና እንደተበላለት ሲያውቅ ደስታውን በመጠነኛ ፈግግታ አረጋግጦ ወደ ቤቱ ይመለሳል። ነገር ግን ማን እንደበላለት አያውቅም እነ ታደሰም ሊሆኑ ይችላሉ።

እማማ ስለዚህ ሲያጫውቱኝ አበከረው የነገሩኝ የተለያዩ የአባብ ዓይነቶች አጀብ

[2] ፈንዳኖ - አማኙ ነዉ፤ ፈንዳናኖ - እምነቱ ነዉ::በመሠረቱ እስልምናን ይመስላል ቢባልም የራሱ የሆኑ ሥርዓቶች ይዞ የሚመራ የጥንቱ የከምባታና ሐዲያ ሕዝብ እምነት ነው።





ያሰኛል። በየት እንደገባ ባይታወቅም አሊጋው ሥር፣ መቀመጫ ዙሪያ በማገር ውስጥ እየተሸሎከለኩ እባቦች ብቅ ይላሉ። ሁሉ ጎብኚ እባብ አንድ ዓይነት አይደለም። ባለ ቁንጮ፣ ዥንጉርጉር በጣም ትልቅና መጠነኛ የሆኑት ይርመሰመሱ ነበር። ብዙዎቹ ለአባባ በተኙበትም ይሁን በተቀመጡበት በሚታይ አቅጣጫ ነበር የሚመጡትና አሳቸውም በፍጥነት "ቅቤ ቅቤ" ብለው በጦር ጫፍ ላይ የተድበለበለ ጥሬ ቅቤ ከፊታቸው ሲያቀርቡላቸው ቅቤውን ላስ ላስ አድርገው መንገዳቸውን ሲጀምሩ በሉ በሰላም ሂዱ ብለው ያሰናብቷቸዋል።

ወላጆቼ "ሀ" ብለው ትዳር ሲጀምሩ የሁለቱም ሃይማኖት ፈንዳኖ ሲሆን አባባ በዕድሜአቸው ዘመን በሦስት ሃይማኖቶች ውስጥ ተንሸራሽረዋል። ወደ ፈንዳኖነት ሁለት ጊዜ፣ ወደ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሁለት ጊዜና ወደ ፕሮቴስታንት ሁለት ጊዜ በጠቅላላ ስድስት ጊዜ እምነታቸውን ቀያይረዋል። ከፈንዳኖነት ወደ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት መጀመሪያ የተለወጡ ጊዜ ያመልኩዋቸው የነበሩት አጋንንት በተለያየ ደዌና ድህነት አባባንም ቤታችንንም መታ" በማለት እማማ በመተከዝ አስታውሰውታል። "ወደ ሢቄ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሄደን ተጠምቀን የተመለስን ዕለት ይታለቡ የነበሩ ላሞች አራት ነበሩ፤ ሁሉም ነጥፈው ለማለብ ሲሞከር ጠብታ ወተት እንኳን አልነበራቸውም። በዚህ ላይ የአባቴ ሕመም ዝም ብሎ የሚያደክም፣ ምግብ የማያስበላ፣ ትኩሳት የሚለቅ፣ እንደ ወባ የሚያንቀጠቅጥ ግራ የሚያጋባ እንደነበረና ይህም ለሁለት ዓመታት ያህል ቀጥሎ እንደነበረ እማማ ያስታውሳሉ። "አገረኝነትን የተላበሰው እስልምና ከአምልኮተ ጣዖት ሥርዓት ጋር ተቀይጦ እስከ ወንጌል ኃይል መገለጥ ድረስ ሰፊ ተቀባይነት የነበረው ፈንዳኖ[3] ብሎታል

Statfan Grenstedt የተባለው ስዊዲናዊ "Ambaricho and Shonkolla በተሰኘው መጽሐፉ በገጽ 54"....Especially for the Hadiya under the influence of the

[3] ወንድዬ አሊ፤ የእኩለ ሌሊት ወገግታ፤ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ 1992 ዓ.ም ቅጽ 2 ገጽ 99

Fendano syncretism" በማለት የፈንዳኖን መቀየጥ ገልፆታል[4]። የአባታችንን ጤና መታወክ ከተመለከቱት ዘመዶችና ወዳጆቻችን መካከል "ያ ቀድሞ የምትገብርለት አምላክ (ውቃቢ) ተቆጥቶብሃል፤ እሱን በመተውህ እርም አድርገሃል፤ የገባው እርም ካልወጣ አንተንም ልጆችህን ያጠፋል ስለሆነም ተመልሰህ ከእርሱ ጋር ብትታረቀዉ ይሻላል" የሚሉቱ በዙ።

በምክራቸዉ መሠረት እርሙን የሚያወጣ አዋቂ ማፈላለግ ነበረባቸዉ:: በዚያን ዘመን እርም ማስወጣት ይችላሉ የሚባሉት "አንኮትመና" በመባል የሚታወቁት የሕብረተሰብ ክፍሎች ብቻ ናቸው ተብሎ ይታመን ነበር:: እሩቅም ሳይኬድ የጎረቤት ሰው ተጠቁሞ ቀነ ቀጠሮ ተበጀለትና የተባለው ሰው ጉዳዩ ተነግሮት ያለማንገራገር መሣሪያውን ይዞ በተባለው ቀን መጣ። ያመጣው መሣሪያ ሌላ ነገር ሣይሆን የጉማሬ አለንጋ ነበር። በአለንጋው ሁለት ነገሮች አደረገ፣ አንደኛ እንደ መግረፍ እያደረገ ማስፈራራትና ውጣ "ልቀቅ" እያለ የሰውየውን ዙሪያ መምታት፣ ሁለተኛ የጉማሬውን አለንጋ እጀታውን በሰውየው አፍ ውስጥ እየከተተ "በል ትፋ አውጣ" እያለ ማጣደፍ ነበር።

አለባቸውና ሳሙኤል በመጽሐፋቸው እንደሚገልጹት ይህ ድርጊት የማንጻት ስርዓት አካል ነዉ:: ሰመናን ወይም ጾሙን በታህሳሰ ወር የሚይዙ ፈንዳኖ በሕዳር ወር በየአካባቢያቸው ወዳለው ትልቅ ወንዝ በመውረድ ለጾም ዝግጅት የመንጻት ሥርዓት ያደርጋሉ። ወንዝ ውስጥ ከገቡ በኋላ የጉማሬ አለንጋ በመያዝ ልክ እንደ ጉማሬ ዋና ዓይነት አስመስለው ይዋኛሉ።. . . በአፋቸውና በሆዳቸው ውሀ በማስገባት ከዚያም በማስመለስ ውስጣቸው ሊኖር ይችላል ተብሎ የሚታመነውን ቆሻሻና አሮጌውን ምግብ (እርም) በማስወገድ ማንፃትንም ያካትታል[5]።

ታዲያ ይህ ሥርዓት ማለቂያው ምንድነው? ብዬ እማማን ስጠይቅ "ሌላ የተከሰተና

[4]Staffan Greenstedt, Ambaricho and Shonkola 2000

[5]አለባቸው ኬዕሚሶ እና ሳሙኤል ሀንዳሞ፤ የሀዲያ ሕዝብ ታሪክና ባሕል፤ 2002ዓ.ም. ገጽ 15





ለሌሎች የታየ ነገር የለም። ተጠርቶ የመጣው ሰው የፈጠረውን ግርግር ራሱ በፈለገው ጊዜ ያበቃና "በል አሁን ይህንን የተዘጋጀውን ምግብ ብላ ብሎ ያዘዋል። ታዞ ምግቡን ከበላ ያጀቡት ቤተዘመድና ወዳጅ ሁሉ ደስ ብሎአቸው እነርሱም በምግቡ በመደሰት ሁሉ ነገር በመልካም እንደተከናወነ አምነው "አስወጪውንም" አመስግነው በሌላ እምነት ተለይቶ የነበረውንና አሁን የተመለሰላቸውን ሰው ተቀብለውት ወደ እየመጡበት ይመለሳሉ፤" በማለት እናቴ የአባቴን የሃይማኖት አቋም ተርከውልኛል።

እንግዲህ እስከአሁን ከፍ ብሎ በተገለፀው መሠረት አባባ በመጀመሪያው ፈንዳኖ ከዚያ ኦርቶክክስ ቀጥሎም እንደገና ፈንዳኖ በመሆን ዕድሜአቸውን አጋምሰውታል፤ በፈንዳኖነታቸውም እስከ 1930ዎቹ መጨረሻ ዘልቀዋል:: የወንጌል ብርሃን የፈነጠቀላቸዉ በ1930ዎቹ መጀመሪያ ነበር። እኔ የተወለድሁት በ1932 ዓ.ም ሲሆን ፈንዳኖነትን አብቅተው ወላጆቼ የወንጌልን ብርሃን ሲያዩ ስድስት ዓመቴ ደርሶ ነበር። በዚህ ወቅት ሦስተኛ ታናሽ እህቴ ዘውዴ ተወልዳ ጡት ትጠባ እንደነበር የእማማ አእምሮ አሁንም ፍንትው አድርጎ ያስታውሣል።

በወቅቱ እንደ ሃይማኖት ከሚቆጠሩት ልማዳዊ እምነቶች በተጨማሪ በአብዛኛዉ ከባዕድ አምልኮ ጋር የተለወሱ በዓላት በየወቅቱ ይደረጉ ነበር:: ሰፊ ተፅዕኖ ከነበራቸዉ እስከአሁንም ካለቸዉ በዓላት ሁለቱን እንደሚከተለዉ በአጭሩ አስዳስሳችኋለሁ::

## ፎጠ ፈዱ

ፎጠ ፈዱ ማለት ትርጉሙ "የፎጣ ደጅ" ማለት ነው። ("ፎጣ" ጠብቆ ይነበብ:: ላልቶ ሲነበብ የፊት ወይም የእጅ መጥረጊያ እንዳይሆን!) ፎጣ የተባለ የኑርቶ ጉሣ ቃልቻ ነው። የመስቀል በዓል የክረምቱን ወራት አስናብቶ የጥቅምት ብራ ሲጀምር የሚታሰበው ፎጠፈዶ ነው። ከበዓሉ ዕለት አስቀድሞ "ቤተ ዘመድ" የሆን ሁሉ

እንጨቱን ማገሩንና ገመዱን ይዞ ወደ ቃልቻው ቤት ይሄድና ተረባርቦ የአምልኮውን አዳራሽ አረቾ ይሠራል። ይህ የሚከናወነው ከጥቅምት 1-5 ባለ ጊዜ ሲሆን ማሳረጊያ በዓሉ ጥቅምት 6 ቀን ይውላል፡፡

መስከረም 30/2006 ዓ.ም ሴቶች በቡድን እየሆኑና እያዜሙ ወደ ቃልቻው ቤትና "አረቾ" ወደተባለው ማምለኪያ አዳራሽ ይደርሳሉ። የቃልቻውም መልእክተኞች (ሞሮታ) በሆታ ከውስጥ ወጥተው ይቀበላሉ። ሕዝቡ በዘፈንና በጭፈራ ሲያስተጋባ ቃልቻው ይወጣና የተዘጋጀውን የጥድ ቅርንጫፍ ያድላል። ጭፈራው ሲቀልጥ ከዋሉ በኋላ ማለዳ የወጣችው ጸሐይ ልትጠልቅ ስታቆለቁል ያ ሁሉ ሕዝብ ወደ ቤቱ ለመመለስ ሲተምም አቧራውን እያስነሣ የመልስ ጉዞውን ይጀምራል። በልጅ አእምሮ ተሰግስጐ የቀረው ይህ የዘፈንና የጭፈራ ድግስ የሚታወሰው በየዛፉ ጥላ ሥር ይጨፈር የነበረው ሁሉ ለዚህ ጸሐፊ የማይረሳ ትውስታ ነው። በዚህ በዓል ሲጨፍሩ የዋሉ ሴቶች ሲመለሱ ቤት ቀርተው ወደ በዓሉ ሳይወጡ ለቀሩት ሴቶች የሚሉት ሲድብ አዘል ግጥም፣እማማና ወልዴ እንዳስታወሱት :-

"አሳዕል አሳዕል ዬማ
አኑ ዳኖል ሆሶ ሆጐፌ
ሆማ አቶት ዬማ"፡፡

ሲተረጐም

ደጅ ጥኚ፣ ደጅ ጥኚ አሉ
አባ ዳኖሌ(ትልቁ ዳኛ)
ቤቷ ለዋለችም ገለባ
ጥዱን አትስጪአት አሉ፡፡

**የመሳላ በዓል**

መሳላ ማለት በከምባትኛ መስቀል ማለት ነው። ነገር ግን መሳላ ክርስቶስ ለሰው





ልጅ ኃጢአት የተሰቀለበትን የእንጨቱን መስቀል ማለት አይደለም። ይህማ በከምባትኛ መስቀላ ነዉ የሚባለዉ፤ ከአማርኛው መስቀል የተወሰደ ይመስላል። መሳላ መስከረም 17 ቀን እንደ አዲስ ዓመት የሚከበር ታላቅ በዓል ነው። ከአዋሽ በስተደቡብ ያለ ሕዝብ በሙሉ የሚያከብረው በዓል ነው። በዓሉ በመስከረም ስለሆነ ከግንቦት ወር ጀምሮ ድባቡ መለወጥ ይጀምራል። ከነዚያ ምልክቶች አንዱ የእርዱ ከብት ተገዝቶ የሚቀለብ፣ በቤትም ያለው ዋጋውን ተምኖ የተቀራጮቹ መጠን ዋጋው ይከፈልና ለቅልብ ይገባል። በአብዛኛው ሠንጋው የሚቀለበው ለሁለት ወር ሲሆን ስሙን ማስጠራት የሚፈልግ ቀደም ብሎ እንደየሁኔታው ይጀምራል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ወሬው ስለመሳላ ይሆንና ከልጅ እስከ አዋቂ የሚያስበውና የሚያወራው ስለመሳለ እየሆነ ጠቅላላ መንፈሱ ሁሉ በዓሉን የሚስብ እየሆነ ይሄዳል። የአዜ/ ደቦአ ቀበሌና በጠቅላላው ሚሽግዳ ማለት ይቻላል በአካባቢው ያለውን ሜዳ ሁሉ መሳላ በዓል ይከለላል። በዚያ በተከለለው ሜዳ እስከ መሳላ በዓል ድረስ አንዳችም ከብት እንዳይገባ ተጠብቆ ለበዓሉ አንድ ወይም ሁለት ቀን ሲቀረው በስምምነቱ መሠረት የአካባቢው ከብት ሁሉ ተለቅቆ የበዓሉ መከፈቻ ይሆናል።

ሠንጋም ይቀልብ፣ ቅርጫም ይግባ ለበዓሉ ሥጋ የሚያዘጋጀው ወንዱ ይሆናል። ሴቱ ደግሞ በበኩሉ አተካኖ የሚባል ከቆጮ የሚሠራ አብዛኛውን ጊዜ ከበዓሉ አስቀድሞ አስራ አምስት ቀን በፊት ሸፌ የሚዘጋጅ ራሱን የቻለ ሥርዓት ያለው ሴቶች የሚሠሩት ነው። ለዚያ የሚሆን ቆጮ በደንብ በከፍተኛ ጥንቃቄ ተዘጋጅቶ አንድ ሰው የሚያስቀምጥ ያህል ከብ ተድበልብሎ እንደ ትልቅ ኳስ በአፍቾ ተደራርቦ ይጠቀለልና ጠብቆ ይታሠራል፤ ሸፌ ተብሎም ይጠራል፡፡ ሸፌ ከታሠረበት ሊሠራ እስከተፈታበት ቀን ድረስ ለሴቶች እና ለልጆች እንደመቀመጫ ያገለግላል። ዓላማው ያ ቆጮ በደንብ እንዲጠፍና ምንም ዓይነት ፈሣሽ እንዳይኖረው ለማድረግ ነው።

ከመሳላ በዓል አስቀድመው ሴቶች በአተካኖ ቀን ረዥም ጊዜ ፈጅተው ያዘጋጁታል።

ያ የሚበላው አብዛኛውን ጊዜ ማታ ይጀመርና እንደ ቤተሰቡ ብዛት እስከ አለቀ ድረስ እንግዳውም ቤተኛውም ይመገበዋል። በዚህን ጊዜ ምራት/ቶች አማታቸውን የሚያከብሩበት ይሆናል። ያም ማለት የራሳቸውን አተካና ሳያዘጋጁ አስቀድመው እንደቁጥራቸው ተሰብስበውም ይሁን ለብቻ የአማታቸውን ዝግጅት ከአጠናቀቁ በኋላ ነው ተመልሰው የቤታቸውን ዝግጅት የሚጀምሩት። በዚያን ሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ወንዱ ለበዓሉ ማገዶ የሚሆን ግንድ ከአለው መርጦ ከሌለው ገዝቶ በኅብረት ፈልጠው እንደሚደርቅ አድርገው ይቆልሉታል። ለበዓል የተባለ ነገር ሁሉ ቢያስፈልግም እንኳን አይነካም። በዚህ ሁሉ ዝግጅትና ግርግር ድግሱ ሌላ ሆኖ በጣም ያስደስታል። የልጆችንም ደስታ ለመጨመር አዲስ ልብስ ይገዛላቸዋል። ከብቱም በዚያ በተከለለው መስክ ላይ ይለቀቅና መመገብ ብቻ ሳይሆን ይፈነጫሉ። ወዲያ ወዲህ ይሮጣሉ ይጮሃሉ፣ ይቦርቃሉ።

የዚያ ሁሉ ዝግጅት የሚፈጥረው ግርግር መስከረም 17 ቀን ለእርድ ከየቤቱ ተገዝቶም ይሁን ተቀልቦ የሚወጣው ሠንጋ ሲታረድና ሥጋው ተከፍሎ ወደእየቤቱ ሲገባ ጾጥታው እየሰፈነ ይሄዳል። ከተበላማ በኋላ ወሬው ሁሉ በሰከነ መንፈስ ስለሥጋው ነው እንጂ የሚሆነው ሌላው ሁሉ ተራራ ያከለው ስሜት (emotion) በእርካታ ይወርድና እረጭ ይላል። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የዘራሮ ጊዜ ነው። ትርጉሙ አበባ ማለት ሲሆን አግብታ የሄደች ሴት ልጅ አበባ ይዛ ጥሩ ምግብ ሠርታ ወላጆችዋን "እንኳን አደረሳችሁ" ብላ ታመጣለች። አብልታ እና በልታ ወደ ቤቷ ትመለሳለች። የሠፈሩም ልጆች አደይ አበባ እየቀጠፉ በየቤቱ አዞረው ይሰጣሉ። በመልሱ ምግብ ይሰጣቸዋል እንጂ ገንዘብ አይሰጥም። ጎረምሶች የተለያዩ ባህላዊ ጭፈራዎችን ከቤት ወደ ቤት እየዞሩ ይጫወታሉ፤ ይሸለማሉ፣ ይጋበዙማል። በበዓሉ ድምዳሜ ልጆችም አዋቂዎችም ችቦ ለኩሰው ይዘው እየዞሩ የመሰላን በዓል "በሳላም ሂድ በሰላም ተመለስ" እያሉ ይሸኙታል፤ ይህም የሚሆነዉ ጥቅምት ሲገባ ነዉ። ከዚያ በኋላ ለሚቀጥለው መስቀል ማሰብ ይጀመራል።





እንደሚታወቀው ሁሉ የወንጂን፣ የወንጂ ሸዋንና የመተሐራን የስኳር ፋብሪካዎችና የሸንኮራውን እርሻ ከመጀመሪያ ጀምሮ ሲያንቀሳቅስ የኖረው የሰው ኃይል የመጣው ከደቡብ ብሔርና ብሔር ብሔረሰቦች ነው። ፋብሪካዎቹ ከረምት ከረምት ሁል ጊዜ ስለሚጸዱና ስለሚጠጋገኑ የመስላንም በዓል ምክንያት በማድረግ ለዚያ ሁሉ ከአዋሽ ማዶ ለመጣው የደቡብ ሠራተኛ ፈቃድ ይሰጥና ወደየመጣበት ሲመለስ ቴፕ ማጫወቻውን፣ ሬድዮውን እና ለራሱም ሆነ ለዘመድ የገዛውን አዳዲስ አልባሳት በሻንጣና በካርቶን ተሸክሞ ሲመለስ ለመስቀሉ በዓል የተለየ ድምቀት ይጨምራል።

## 4. ወንጌል ቤታችንን ሲያንኳኳ

**"እየሱስ! . . . እሱ ደግሞ ምንድ ነው?"**

ጥቂት ወደ ኋላ ልመልሳችሁ:: የስድስት አመት ልጅ እንደነበርኩ አስታውሳለሁ፤ ከብቶች ከግጦሻቸው ገብተው ውጪው ጨልሞ የቤታችን በር ከተዘጋ በኋላ አባባ ወደ ቤት እያዘገሙ ነበር:: እንደልማዳቸው መምጣታቸውን ለማወጅ ከውጭ ሆነው ጎሮሮአቸውን እእእ በማለት ካጣሩ በኋላ (የታወቀ ድምጽ ስለሆነ) ማነው ተብለው ሳይጠየቁ በሩ ተከፈተላቸው፤ ዘው ብለው ገቡ። መቀመጫቸውም የተለየ ስለሆነ ማንም አይዝባቸውም፣ ሰተት ብለው መጥተው አረፍ አሉ። ለሙቀትም ለመብራትም ምግብ ለማብሰልም የሚያገለግለው እሳት ሦስተኛውንም ግልጋሎት እየሰጠ ነበር። እማማ እራት በማዘጋጀት ላይ ነበሩ። የእሳቱ ቦግ ብሎ መንደድ፣ ይሰጠን የነበረው ሙቀት የእራቱ ዝግጅትና የአባባ መምጣት ቤታችንን የተሟላና የተመቻቸ አድርጎታል፤ ፈረንጆች (Cozy) እንደሚሉ ማለት ነው።

አባባ መቀመጫቸው ላይ (ሦስት እግር በርጩማ) ሲቀመጡ የኔ ቦታ ይለወጥና በሁለት እግራቸው መሀል መሬት ቁጢጥ ብዬ በሁለት እጆቼ የእግራቸውን ፀጉር ማሻሸት ደስ ይለኝ ስለነበረ ማንም ተሻምቶኝ አያውቅም። እርሳቸውም ጸጉሬን

ያሻሹልኛል። አባባ ቅንሽ አረፍ እንዳሉ "የሱስን ተቀብዬ መጥቻለሁና እናንተም ተቀበሉ"፤ በማለት አዲስና እንግዳ ነገር ማወጅ ጀመሩ። ነገሩ ምን እንደሆነ ሳይገባኝ ለወሬ ቸኩዬ ነው መሰለኝ "እኔም እቀበላለሁ!" በማለት በእግሮቻቸው መሀል እንደተቀመጥሁ ከስር አንገቴን ወደ ላይ ሳቀና ፈገግ ብለው ወደታች ይመለከቱኝ ነበር።



እናትና ልጅ

"የሱስ? እሱ ደግሞ ምንድ ነው?" ያሉት ደግሞ እማማ ነበሩ? ከዚያ በኋላ የነበረው ጭውውት እንዴት እንዳለቀ አላስታውስም። እናቴ ግን ዝርዝሩን አስታውሰው አጫውተውኛል። የሱስን እንዴትና መቼ ተቀበሉ ብዬ ሐምሌ 12 ቀን 2005 ዓ.ም በአሥራ ሁለት ሰዓት ገደማ ላቀረብሁላቸው ጥያቄ ሲመልሱ?

"እኔ ወዲያውኑ አልተቀበልሁም ከአንድ ወደ ሌላው ሃይማኖት መንሸራሸር አልወድም ነበር። አንትህ መንታሞና እኔ ቢሉን ቢሰሩን እምቢ ብለን ቆየን። በኋላ ግን አባዮ ኤደሞ የተባሉ ወንጌላዊ መጥተው ወንጌልን ሲሰብኩልን ጌታን ተቀበልን" ብለውኛል።





እኚህ አባዮ ኤደሞ የተባሉ ሰው ለረዥም ዘመን ቤታችን ይመላለሱም ነበር። የቤተ ክርስቲያንም መሪ ሆነው እስከ ህልፈተ ሕይወታቸው ከቦታ ወደ ቦታ በእግር እየኳተኑ ወንጌልን ያስተማሩ አባት ነበሩ። ሁለት እናቶች እንደነበሩን ከፍ ብሎ ተገልጿል። አባቴ ጌታን ከተቀበሉ በኋላ ለቤተ ክርስቲያን መሪ የሚሆን ሰው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መሠረት . . . "የአንዲት ሚስት ባል. ." የሚለው ከተዘረዘሩት መስፈርቶች አንዱ ስለሆነና ትምህርቱ የማይዘለል ቢሆንም በገዛ ውሳኔያቸው ከሁለቱም ሚስቶቻቸው ጋር ቆይተዋል። እኩያቸው የነበሩትና የአጎታቸው ልጅ ቄስ ሽሜቦ ቀልቦሮም ባለ ሁለት ሚስት ቢሆኑም ስመቅጼል ትምህርትና ለትዕዛዙ ቦታ ሰጥተው[6] አንዷን ሚስታቸውን በክብር አሰናብተዉ ከሌላይቱ ጋር በትዳር ጸንተዉ ኖረዋል፡፡

አባባ ግን እምቢተኝነታቸውን እንደተሸከሙ ቆይተው እስከ ዕለተ ህልፈታቸው ድረስ እንደዚያው ቀጥለው ኖረዋል። በሞት አፋፍ አልጋ ላይ እንዳሉ ግን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ቤት ድረስ መጥተውም ጸልየውላቸው ንስሐ ገብተዋል። ያ "እሱ ደግሞ ማን ነው?" ብለው የጠየቁት እናታችን ግን በአምልኮአቸው፣ በአሰራት፣ በመስዋዕታቸው ጽኑ ሆነው በየጊዜው በቤታቸው አገልጋዮችንና መዘምራንን እየጋበዙ የምሲጋና ፕሮግራም በማዘጋጀትና ሕይወታቸውን በሰላም እየመሩ እስከዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ድረስ በሕይወት አሉ፡፡ ከእርሳቸዉ ትረካ በመነሳት ዕድሜአቸው ዘጠና ስድስት አመት ይሆናል፡፡

በሊጋው ሕይወቴ ወደ ቤታችን የመጣው ኢየሱስ ለመላዉ ቤተሰባችን ጥላ ከለላ ሆኖ በአንድም በሌላም መንገድ ስንላላና ስንደከም ችላ ሳይለን፣ ከመስመሩ ወጣ


[6] ዶ/ር ሚልኪያስና ወ/ሮ ዜናን [illegible] ሁለተኛ ሚስታቸውን ወ/ሮ ሸዎን በሰላም አሰናብተው ብቻ ሳይሆን ለጓደኛቸው ድረስ [illegible] እንዳገኙ ነግረዉኛል (ገጽ 48)



እናትና ልጅ

ስንልበት ደግሞ እየጠበቀን፣ በመስመሩ ስንገባለት ደግሞ በአብሮነቱና በመልካም እረኝነቱ ወደ ለመለመው መስክ እየመራን፣ በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብንሄድ ክፉውን ሳንፈራ (መዝ. 23) ቸርነቱና ምህረቱ በሕይወታችን ዘመን ሁሉ እየተከተለን እዚህ አድርሶናል።

## አባታችን



አባቴ

አባባ በማኅበረሰቡ ዘንድ ደፋርና ጎበዝ የሚባሉ አክብሮት ያተረፉ ሰው ነበሩ። ጥሩ መልበስና ከባለሥልጣናት ጋር መዋልም ይወዱ ነበር። መደበኛ ትምህርት ለመከታተል ዕድል ባይኖራቸውም በተፈጥሮ ልበለውና በአንፃራዊነት ጥበብና ብልሃት የታደሉ ነበሩ:: የነገሮችን ምንጭ፣ ሂደትና ውጤት አጢነው ምን መሆንና መባል እንደሚገባው ማዕከላዊ እማካኙን የውሳኔ አሳብ ስለሚያቀርቡ በማኅበረሰቡ ዘንድ ከበሬታ ያገኙ ነበሩ::

በእሳቸዉ ዘመን ከባለሥልጣናት ጋር በአደባባይ በድፍረት ለመዋል ማንበብና መጻፍ መቻል ትልቅ መለኪያ ነበር:: ስለሆነም ኃይለማርያም ከሚባል ፊደል አስተማሪ ከሆነ የአማራ ተወላጅ ጋር ተወዳጁ:: በቤታቸዉ ተቀምጦ ማንበብ፣ መጻፍና በአጭር ጊዜ ዳዊትም አስደገማቸው። እንዲሁም በግላቸዉ ጥረት የዘመኑን ወንጀለኛ መቅጫና የፍትሐብሔር ሕግ አንብበው መረዳት መቻል ብቻ ሳይሆን በወረዳና አውራጃ ፍርድ ቤቶች ለባለጉዳዮች ዋቢ በመሆንም ይረዱ ነበር።

በማኅበረሰቡም መካከል ችግር ሲፈጠር በግምባር ቀደምነት የሚጠሩና ለማንም






ሳያዳሉ ሁነኛ ምክር የሚለግሡ ነበሩ:: ያለአግባብ በተበደለው ወገንም በኩል ቆመዉ በምክርና ባስፈላጊው ሁሉ ይረዱና ያበረታቱ ነበር። ማንም ሰው በጉልበቱ ተመክቶ ሌላውን ሲያጠቃ ካዩ ደግሞ ጣልቃ ገብተው ይገላግላሉ፣ እምቢ የሚልና የማይተው ከሆነም በመጣበት አኳኋን በድብድብም ቢሆን ለማስተናገድ አይመለሱም ነበር። ከዚህም የተነሣ የጎረቤትና የአካባቢው ሰው በፈቃዳቸዉ እርሻቸውን በማረስ፣ ቤት ሲሠሩ በማገዝ ያገለግሏቸው ነበር።

መስከረም 13ና 14 ቀን 2007 ዓ.ም የዱራሜ ዞን ባዘጋጀዉ ልማት ነክ ስብሰባ ላይ እንድሳተፍ በተደረገልኝ ጥሪ መሠረት በአካባቢዉ ስገኝ አንድ አዛውንት ስለ አባቴ የነገሩኝ ነገር ባህርያቸውን በከፊል ይገልጻል:: ነገሩ እንዲህ ነዉ:- ሴት አያታችን ሞተዉ አስከሬናቸውን በቤተሰብ መቃብር ለማሳረፍ ሲቆፈር ወቅቱ ክረምት ስለነበረ ምንጭ ወጣበት:: የእድሩ አባላት ለአባቴ ሲነግሯቸዉ ከቤታችን ሰሜን ምሥራቅ ጉብታ ላይ ባለዉ የአቦ ቤተ ክርስቲያን ለማስቀበር የካኅኑን ፈቃድ ቢያስጠይቁ ቤተ ዘመድ ቢሆንም መልሱ አይቻልም ሆነ:: አባባ ይህንን ሲሰሙ በቁጣ ጠብመንጃቸውን አንስተዉ ጥቂት ሰዎችም አስከትለዉ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አመሩ፤ የእናታቸውንም መቃብር ማስቆፈር ጀመሩ:: ያ የዘመድ ቄስ ለወዲያው ደርሶ ቁፋሮውን ለማስቆም ሲሞክር "እዚህ አትቀብርም" ካልከኝ አንተዉ ትገባበታለህ በማለት ጠብመንጃቸውን አዞሩበት:: "እግዚአብሔር ይይልህ!" ብሎ ሄደ፤ የእናታቸውንም አስከሬን በዚያ መቃብር አረፈ::

### አባባ በልጆቻቸው ሚዛን

አባታችን እንደማንም ወላጅ ልጆቻቸውን የሚወዱና መልካሙን ሁሉ የሚመኙልን ነበሩ። በማንም ጥቃት እንዲደርስብን አይፈቅዱም። ሁላችንም እንድንማርና እንድንሻሻል ይገፋፉ ነበር። ባይገፋፉን እንኳን "አትማሩ" የሚል ተቃውሞ አይሰነዝሩም ነበር። ይሁን እንጂ ትምህርት መማር የገንዘብ ወጪ እንዳለበት



አባቴ

አ
ኀ
ነ
ጋ
ት
ባ
በ
ነ
ወ
መ
አ
በ
ነ

ተረድተው ለመዳዳሻ፣ ለስንቅ፣ ለልብስ. . . ወዘተ አስፈላጊውን መስጠት ቀርቶ ሽራፊ ሳንቲም መደጎም የመከራ ያህል ይከብዳቸዉ ነበር። ከደጎሙም ብዙ ደጅ ከአስጠኑን በኋላ ነበር። የሚያሳዝነው ሁላችንም ልጆቻቸው አንዳችን ከሌላችን ሳይለይ ስለንፉግነታቸዉ እንጂ ስለ ቸርነታቸዉ የተሻለ ትውስታ የለንም።

ለዚህ ዋና ምክንያት ብዬ የማስበዉ ያኔ ገንዘብ በካሽ ለማግኘት የግድ የቤት እንስሳ ወይም እህል ገበያ ወስዶ በመሸጥ ነበር፤ በዚያው ልክ የተገኘችውን ፈረንካ ለማውጣት ነፍስና ሥጋቸዉ ስለሚሟገትባቸዉ ይመስለኛል። ለምሣሌ፡- አንድ ጊዜ ሻሸመኔ እኖርበት ከነበረው ዘመድ ቤት ለትምህርት ቤት መከፈቻና ለጥምቀትም በዓል ቤት ውስጥ የነበርን ሁለት ልጆች ታፈሰ ሸዋን ግዛው የወ/ሮ ሙሉወርቅ እህት ልጅና እኔ (የባል ዘመድ) ተፈቀደልንና ልብሳችንን እንድናጥብ ሳሙና ተሰጠን። ሁለታችንም ያለችንን ልብስ አጥበን ተኩሰን ሰቀልንና በነጋታው ወደ ጥምቀተ ባሕር ልንሄድ ወሰንን። ጧት ስንነቃ የኔ ልብስ አንዳች ሳይቀር ሌሊቱን ምስጢራዊ በሆነ መንገድ ተለይቶ ተሰርቆና ለቤት ሥራ የለበስሁትና መጨቅጨቂት መሰሎ የቆሸሸ ብቻ ቀርቶልኝ ባንድ ጊዜ ባዶዬን ቀረሁ። ይህንን ችግሬን ገልጬ ለአባቴ ደብዳቤ ጻፍኩና በእጅ ለሚሰጥ ሰው ልኬ ብጠብቅ ብጠብቅ ብቅ የሚል ሰዉ፣ ጠብ የሚልም ነገር ጠፋ። እኖርበት ከነበረው ዘመዴ ቤት ስለወጣሁ ሁኔታዬ ፈረንጆቹ እንደሚሉት "ከመጥበሻ ወደ እሳቱ (በእንግሊዝኛቸዉ from the frying pan into the fire)" የመውደቅ ያህል እየሆነብኝ ሄደ።

ይህ ጊዜ የሕይወቴ ጨለማ ትዝታዎች አንዱ ነበር፡፡ የማድርበት ማጣት አንድ ነው፣ የምበላው ነገር እየራቀኝ መሄዱ ሌላ ነገር ነው። ትምህርቴን ልሰናበተው ጥቂት ሲቀረኝ ከሁለት ወር በላይ ጠብቄ አባቴ ከአዲሷ "እንጀራ እናቴ" ጋር መጡና ልብስ አሰቀደዱልኝ። አንድ ቁምጣና አንድ ዣሪያን ኮት ተሰፋልኝ። የማደሪያዬን ችግር የትምህርት ቤት ጓደኛዬ የነበረው ተመስገን ማዴቦ (በደርግ ጊዜ የኢትዮጵያ





ሠራተኞች ማኅበር መሪ የነበረውና የተገደለው) ሻሸመኔ Sudan Interior Mission (SIM) ግቢ ማደሪያ ሰጥተውት ይኖር ነበር፡፡ በክፍሉ ውስጥ በዘረጋት ሰሌኑ ላይ አብረን እንድንተኛ ፈቀደልኝ፡፡

የዕለት ምግባችን የበቆሎ ቆሎ ነበር፤ ለዚያውም የበቆሎው ‹ስፖንሰሬ› ሙሉ ለሙሉ ተመስገን ነበር። በዚህ ሁሉ አባታችን ትምህርት የሚያስከፍለውን ዋጋ እንዲሁም ከቤተሰብ ርቆ መማር የሚያስከትለውን ችግር በውሉ አይረዱትም ነበር ማለቱ ይቀለኛል፤ ለኅሊናዬም ሰላም ይሰጠኛል፤ አላለፉበትምና፡፡ እየተራቡም ሆነ እየተራቆቱ መማር በኔ ተጀመረ እንጂ ተናናሾቼም በየተራ ፅዋውን ተጎንጭተዋል። ልዩነቱ አቅሜ እየፈቀደልኝ በሄደ ቁጥር ሸክማቸውን የመጋራት (የማቃለል) ዕድል ማግኘቴ ነበር።

## 5. እናታችን

እናታችን ወ/ሮ አንሼቤ ከአባታቸው ከአቶ ሳንቂቆ ኮሮቼና ከእናታቸው ከወ/ሮ አርፍጬ ሐንዶሬ ቃጨቢራ ወረዳ በግምት በ1911 ዓ.ም. ገደማ ተወለዱ። ቃጨቢራንና የእኔን ትውልድ መንደር ሚሽጊዳ አዜ ደቦአን ቀበሌ የሚለየው የጨሜ ተራራ (በእግር ከ30 - 40 ደቂቃ መንገድ) ሲሆን ተራራ ባይኖር ኖሮ ሁለቱም ቦታዎች የተያያዙ በሆኑ ነበር። በሁለቱም አካባቢ የከብት እርባታና እርሻ የኢኮኖሚው ዋና ግብዓቶች ሲሆኑ የቃጫቢራ ነዋሪዎች ወደ ከብት እርባታዉ ሲያደሉ የሚሽጊዳ ነዋሪዎች ደግሞ ወደ እርሻው ያደሉ ነበር። የሚሽጊዳ ነዋሪዎች ለውጥን ፈጥኖ የማስተናገድ ዝንባሌ ሲኖራቸው ቃጨቢራዎች ደግሞ ዝግ ያሉ ነበር። ለምሳሌ ሃይማኖትን ትምህርትንና እርሻም ቢሆን ቃጫቢራዎች ዘግይተው ነበር የተቀበሉት።

አያታችን እዳቼ ተድረው የመጡት ከደጋው መጠሪያ ስሙ ጎጃሜ ከሚባል ለሐንገጫ

ከተማ ከሚቀርብ ቦታ ሲሆን ጕሣቸው አየታ ይባላል። የቃጫቢራ ነዋሪዎች ደግሞ ሃዲያ ሲሆኑ በከምባታና በሃዲያ መኻከል የጋብቻ ጥምረት የጀመረው በእኛ ዕድሜና ትውልድ ሳይሆን ጥንት ነበር ለማለት ይቻላል። የሁለቱን ጕሣዎች አዎንታዊ ግንኙነት ለማወቅ ልዩ ጥናት ቢደረግ መልካም ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

አያቴ አዳቼ ያገቡት ከሃዲያ ወገን ሲሆን ልጃቸው የኔ እናት ደግሞ ያገቡት ከከምባታ ነው፤ (እኔ ከዬቱ ነኝ ማለት ይሆን?)፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ አያቴ አዳቼ ከዕለታት አንድ ቀን የአንድ ዓመት ሴት ልጃቸውን (እናቴን) አዝለው ወላጆቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ጐጃሜ ሄዱና ከርመው ወደ ቤታቸው ለመመለስ ሲነሱ አባባ ሐንዶሬ የልጅ ልጃቸውንና በኋላ የዚህ ጸሐፊ እናት የሆኑትን ጫና በማሳደር "አትወስጂም እዚሁ ቀርታ ጡት ማስጣል አለብን" ብለው በግድ አስቀሯቸዉ፡፡ አያቴ ልባቸው እንደከበደ ልጅ ማዘሉ ግን ቀልሎአቸው ወደ ትዳራቸው ብቻቸውን እንደተመለሱና በዚህ ምክንያት የእናቴ አፍ መፍቻ ቋንቋ ከምባትኛ ሆኖ ወደ አሥር ዓመት ገደማ ከአያቶቻቸው ጋር ኖረው ወደ ወላጆቻቸው እንደተመለሱ እማማ መስከረም 28 ቀን 2006 ዓ.ም እያስታወሱ አጫውተውኛል።

ከአሥር ልጆች መካከል ሁለተኛ የሆኑት እማማ ስለ ወላጆቻቸው ኑሮ ሲያስታውሱ "የተወለደው ወንድ ሁሉ ዋና ሥራዉ ግጦሽ ባለበት ሁሉ ከብቶች ተከትሎ መዞር ነው፤ . . . እየተንዳኙ እስከ ሆሣዕና፣ ወንጀላ ሜዳ ድረስ ለወራት ከከብቱ ጋራ ይዞሩ ነበር" ይላሉ። ይህ ኑሮ እስከመቼ ቀጠለ ብዬ ለጠየቅሁአቸው ለመመለስ ሲያስታውሱ ስድስተኛው ወንድማቸው ሱጌቦ የተባለው አጐታችን ተወልዶ በእግሩ ለመሄድ ድክ ድክ በሚልበት ጊዜ ነው መሬታቸውን ሌሎች ሰዎች ባለቤት የሌለው ነው በማለት ለመውሰድ መነሣሣታቸውን ያወቁ ዘመዶች መልእክተኛ ልከው ሲነግሩአቸው አባታቸው አቶ ሣንቂቆ ያለ የሌለ ከብታቸውን ነድተው ወደ ቃጫቢራ ተመለሱ። ከዚህ በኋላ ትኩረቱ ወደ መሬት ማረስና የተለያዩ ሰብሎችን





እየዘሩና እንስት እየተከሉ ከብትም እያረቡ ከከብቱም ጨርሰው ሳይላቀቁ ኖሩ። በእንዲህ ያለ ኑሮ ያደጉት እናቴ እንደሚገምቱት ከ18-20 ዓመት ሲሆናቸው ነበር ከአባታችን ጋራ ትዳር የመሠረቱት።

እናታችን ግን ከነበራቸው ጥቂት ለሁላችንም በየተራችን እየተበደሩም እየተለቁም ይደርሱልን ነበር። በኔ ዘመን ትምህርት ቤት ስላልተስፋፋ መኖሪያ ቤት እየኖሩ ለመማር ዕድሉ የማይታሰብ ቢሆንም ለታናናሾቼ በሩ ተከፍቶላቸው ነበር። ከነዚህ አንዱ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ የሱስ በ1955 ዓ.ም በቤናራ ቀበሌ የከፈተችው ትምህርት ቤት ነው። ይህ ትምህርት ቤት ከቤታችን በእግር የግማሽ ሰዓት መንገድ ብቻ ሲሆን፣ አስቀድሞ የሱዳን ኢንተሪዬር ሚሲዮን (SIM) ጠዛ ላይ የተከፈተው ትምህርት ቤት ቢያንስ አንድ ሰዓት በእግር ያስኬድ ነበር፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሌላው ከእናታችን ያገኘነውና አሁንም የቀጠለው የማያቋርጥ ጸሎታቸው ነው። ስንቁም ሣንቲሙም ሲደርሰን ቆጥረን ጉዳያችንን እንወጣበታለን ወይም በልተን ጉልበታችንን አጠንክረን ትምህርታችንን እንገፋበታለን። ከእማማ የዘወትር ጸሎት የተነሣ የሆነልንን ግን የትኛውም የሳይንስ ፎርሙላ ሊያሰላው አይችልም። ሌላዉ ቀርቶ ከሰባቱ አምስታችን በትምህርቱ መስመር ገፍተን ለመጓዝ የቻልነዉ በእናታችን ጸሎትና ድጋፍ እንደሆነ እንመሰክራለን።

ወላጆቻችን ተፋትተው እናታችን ወደ ዘመዶቻቸው ወደ ቃጨቢራ ተመልሰው ይዘዋቸው ከሄዱት እህቴ ዘነበችና ወንድሜ ታደሰ ጋራ ‹ጎጆ› ወጥተው መኖር ጀመሩ፡፡ ጥቂት እንደቆዩ አንዲ አክስታቸው ያልተጠበቀ ምክር ሊለግሡአቸዉ መጡ። ምክሩም"እነዚህን ልጆች ወስደሽ በአባታቸው አፍንጫ ላይ ወርውረሽለት ነይ፤ በበቅሎ ተቀምጠሽ አሽከር አስከትለሽ የምትወጪበት የምትገቢበት፣ ብዙ ላሞች የምታልቢበት ቤት (ትዳር)፣ እኔ ላዘጋጅልሽ፤ ሲያይሽ ቀንቶ ለመታረቅ ሽማግሌ

ልኮ ለምኖ አስታርቁኝ ባይል ታያለሽ"[7] የሚል ነበር፡፡ እህቴ ዘነበች ነፍስ ስላወቀች ያኔ ያዳመጠችው የአከስታችን ምክር ውስጧን ረበሻት፤ በተለይም "ልጆቹን በአፍንጫው ወርውረሽለት . . ." ሲሉ የተናገሩት ቃል ወዲያው የሆነ እየመሰለኝ ለረዥም ጊዜ ሲዘገንነኝ ቆይቷል፤ ከዚያ በኋላ አክስቴን በጣም ጠላኋቸዉ፤ ትላለች። በጊዜው እናታችን "እኔ ልጆቼን በቀኝና በግራ ይዤ ከታለበውም ሆነ ከሚናጠው ቀንሼ ስሰጣቸው የማገኘውን ደስታ ምንም ነገር ሊተካው ስለማይችል ጨርሶ ላስበው አልችልም" የሚል ምላሽ ሲሰጧቸዉ አኩርፈዋቸዉ እንደ ተመለሱ ነግረውኛል።

## የቋንቋ ልዩነት አስኮበለለኝ

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ጡት ለማስጣል በሚል ሰበብ እናቴ ወደ ወላጆቻቸው አያቶቼ ቤት ተወስደው ነበር ያደጉት። እኔ የተወለድሁት በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ በሚሽግዳ ቀበሌ ልዩ ስሙ አዜ-ዶቦአ በተባለ ሥፍራ ሲሆን የሕዝቡ ቋንቋ ከምባትኛ ነው። የእናቴ ትውልድ ቦታ ደግሞ ቃጫቢራ የሚባል በአሁኑ አከላል የሐዲያ ዞን አካል ሲሆን ቋንቋው ሐዲይኛ ስለሆነ ባደረብኝ ሕመም ምክንያት ወደ ወላጆቼ ሲመልሱኝ ለረዥም ጊዜ መነጋገሪያዬ ይኸው ቋንቋ ሆኖ ሰው በከምባትኛ ሲያናግረኝ እኔ በሐዲይኛ እየመለስኩ የምጠየቀውንም የምመልሰው በዚሁ ቋንቋ ሆኖ ቆየ። ወላጆቼና በነርሱ ምክንያት ሁላችንም የቤተሰብ አባሎች የፕሮቴስታንት ክርስትና አባሎች ከሆንን በኋላ ለምግብም ሆነ ቡና ለመጠጣት ጸሎት አድርግ ስባል የተመቸኝ ጌታችን ያስተማረውን ጸሎት በቃል ሸምድጄ ነበር በአማርኛ የምጸልይላቸው የነበረው። ይህ ሁኔታ ለአባባ ከቶውንም አልተመቻቸውም ነበር! ቤታችን በሚመጣው እንግዳ ሁሉ ከምባትኛ በአለመናገሬ እየተገረሙም ይሁን እየተከፉ መተቸታቸው አባባን እያሳፈረ መጣ መሰለኝ በከምባትኛ እንድናገር

[7] ሐምሌ 11 ቀን 2005 ዓ.ም በነበረን ውይይት አስታውሰው ከአጫወቱን።





"ማስገደዱ እየጨመረ ሄደና አንድ ቀን ምሽት ላይ አባባ ከዋሉበት መጥተው "ከነገ ጀምሮ ከምባትኛ ከአልተናገርክ ከዚህ ቤት ትወጣለህ" የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጠኝ።

ከምባትኛውን አቀላጥፌ መናገር ባልችል ይሳቅብኛል የሚል ፍርሃት ውስጤን ሞልቶት ነው መሰለኝ ለዚህ ሐፍረት ከመጋለጥ ይልቅ ከቤት የመውጣቱን ምርጫ ያዝኩና ንጋት ላይ ሰው ተኝቶ በእንቅልፍ ላይ እንዳለ እኔ ከቤት እንዴት ሳልያዝ ወጥቼ ወዴትስ መሄድ እችላለሁ በሚል አሳብ ሳወጣና ሳወርድ አደርኩና አንድ አሳብ መጥቶልኝ ማምለጫ መንገዴን አዘጋጀሁ። ወፎች ጭ-ጭ-ጭ በሚል ድምጻቸው መንጋቱን ሲያውጁልኝ ልብሴን ለብሼ ድምጽ ሳላሰማ በሩን ከፍቼ ከቤት ወጣሁና ወደ ደቡብ በደቀያ ሜዳ አድርጌ ድርግታን፣ ሕልፈታን፣ ሲቄን አቋርጬ የአባቴ ታናሽ እህት አክስቴ ሎዳሜ ወደ ምትኖርበት ለወላይታ ድንበር ቅርብ ወደ ሆነው ዴዳ የሚባልበት ቦታ ረፋዱ ላይ ደረስኩ። ኃይለኛ ውሾች ስለነበሩአቸው ዘው ብዬ መግባት ስለማልችል ለሚያውቋቸው ሰዎች ጎረቤቶች ነግሬ ሄደው አክስቴን ጠሩልኝ። "ለምን መጣህ? ማን ላከህ?" እያለች ወጥታ ስትጠይቀኝ እቅጩን "ከምባትኛ ካልተናገርክ ከቤት ትወጣለህ" ስላሉኝ ወደዚህ ሸሸሁ ስላቸው ሁሉም ሣቁብኝ። ይሁን እንጂ በእንግድነቴ አልከፉኝም፤ ተመችቶኝ ሁለት ይሆን ሦስት ወር ቆየሁ።

በዚህን ጊዜ የአካባቢው ቋንቋ ሐዲይኛ ብቻ ሳይሆን ወላይትኛም ይነገር የነበረው መሳ ለመሳ ነበር፡፡ እኔም በወላይትኛ መነጋገር ጀምሬ ነበር፡፡ አንድ ቀን ከቤት ወጥቼ በአክስቴ ቤት በረዥሙ ጥጉን ይዘው ትንንሽ ቤት (ጐጆዎች) ነበረና በአንዱ አጠገብ ላልፍ ስሄድ አንዲት እናት አዋቂ ልጇን ጠርታ በወላይትኛ "የእሜቴ ወንድም ሞቶአል; ተብሎአልና ርቀህ አትሂድ" ስትል ሰምቼ ብቻ ጩኸቴን ለቀቅሁ። ድምፄን ሰምታ የወጣችው "አክስቴ" ሟን ነው የመታው እያለች ሠፈሩን ለማተራመስ

ስትወጣ እኔ እየጮሁ ወደ ወላጆቼ መንደድ ጀምሬ ነበርና ሮጠው ደርሰው ይዘውኝ ሲመለሱ የተባለውን ለአከስቴ በልቅሶ መኻከል እንዳለሁ ነገርኳት። እርሷም ነገሩን አጣርታ አብረን ልንሄድ ልብሷን መለወጥ ስትጀምር ለእኔ የሚበላ አዘዘችልኝ ግን ልበላው አልቻልኩም ነበር።

"የእሜቴ ወንድም ሞቷል" የተባለውም የአባቴ ታላቅ ወንድም ደልበቶ የተባለው እንደሆነ ተረጋገጠ። የአስም በሽታ ብዙ ጊዜ እያፈነው ይቸገር እንደነበረ ዘመድ አዝማድና ጐረቤት ሁሉ ያውቀው ነበር። አከስቴ ልብሷን ፈጠን ብላ ቀይራ ሁለታችን ተከታትለን መንገዱን ተያያዝነው። አንድ ቦታ ቆም ብላ ቆንጥሩን ትበጥስ ጀመር። እርሷ የእጇን መዳፍ የሞላ ቆንጥር አስተካከላ እንዳይበተንባት አድርጋ አሠረችው፡፡ ለምን እንደሆነ ስላልገባኝ አብሬአት ቆምኩ እንጂ ምን እንደምታደርግና ለምን ብዬ አልጠየቅሁም። ከእርሷ እንዳየሁት ከፊቴ ዘወር ስትል እኔም አንድ የቆንጥሩን ቅጠል በጠሰኩና እንዳታይብኝ እጄን ወደ ኋላ አድርጌ ተከተልኳት፡፡

ወደ ቤታችን አካባቢ ስንደርስ ወደ ደቀያ ሜዳ ገና ብቅ ስንል ቆንጥሩ ሥራውን ጀመረ። በቀኝ እጇ ይዛ ሁለቱን ጉንጮቿን ተራ በተራ ስትመታበት በቆንጥሩ የተተለተለው ፊቷ እስከ ደረቷ ደም በደም ሆነ። ቤት ደርሳ ከእጇ እስኪነጥቋት ድረስ ፊቷን ትነጭበት ነበር። የኔውማ ብቸኛ ቆንጥር ስፈራ ስቸር አንዴ ጉንጬን ስመታበት ወግቶ ያዘኝ፡፡ እንደምንም አባብዬ ነቅዬው እዚያው ጣልኩት። ደግነቱ ፊት መንጨት ከወንድ የሚጠበቅ የሃዘን መግለጫ ስርአት አልነበረም። እንዲያ ደምና እምባ እያነባች ተጉዘን የደረስነው ግን ለቀስተኛው ከቀብር ሲመለስ ነበር፡፡ አከስቴ ፊቷን ወደ መታጠብ ስትሄድ እኔ ደግሞ ሰዎችን እየዞርኩ እጅ መንሳት ጀመርኩ፡፡

የአባቴ አጐት አቶ ቀልቦሮ ሐረቼ "አባ" በመባል ይታወቃሉ (የቄስ ሻምሜቦና የቄስ አስፋዉ አባት ነበሩ)፡፡ የቤቱን ምሶሶ ተጠግቶ ባለው የሚታይ ቦታ በርጩማ ላይ ተቀምጠዋል፡፡ የአጣፉት ባለ ቀይ ጥለት ጋቢ ሆን ብለዉ ከነጭ ሽበታቸው

ጋር ለማመሳሰል የለበሱት ይመስላል። በጣም የተከበሩ እንግዳ ስለሆኑ አባባ አጠገባቸው ተቀምጠው ያጫውቱአቸው ነበር። ቀደም ሲል እኘኹ ሰው የአያቴን መሬት ለወንዶች ልጆቻቸው ማለትም ለአባቴና አጐቶቼ ለማካፈል ቤታችን መጥተው ነበር፡፡ ታዲያ ምን ያደርጋል መሬቱን አካፍለው የጨርሱ ምሽት ለራት ግብዣ የታረደላቸው እኔ ያሳደግሁትን ዳለቻ በግ ነበር፡፡ ከእንቅልፌ ስነቃና በጌን ከአጠገቤ ሳጣው እንዴት እንደጮኩሁ ትዝ ይለኛል፡፡

ከአከስቴ ጋራ ከኋላዋ እያለቀስኩ ስገባ አባባን "ለምን ሄዶ ነው" ብለው ጠይቀዋቸው ኖሮና ጉዳዩን ነግረዋቸው ለሰላምታ የተነሣሁ ጊዜ ከእርሳቸው መጀመር ስለነበረብኝ ሄጄ ወደ ጉልበታቸው ጐንበስ ስል አቅንተዉ ከሳሙኝ በኋላ "የእናትህ ቋንቋ ከአባትህ ቋንቋ ስለሚጣፍጥ ነው አልናገረውም የምትለው? ... በል ሁለተኛ ይህንን ወሬ እንዳልሰማ!" አሉኝ፡፡ እሺ ብዬ በትኅትና እጆቼን ከእጆቻቸዉ አስለቅቄ ነበር ለሌሎቹ እንግዶች ሰላምታ ማቅረብ የቻልኩት። በዚያን ጊዜ "አባ ተናገሩ" ማለት "እግዚአብሔር ተናገረ" ማለት እንደማለት ነበረ፡፡ የከምባታ ተረትና ምሣሌ **"ከዋጄም ጋዕሮሪ ሙተ ሐሚሊን ገፍ እቾም"** ማለትም "የፈራኋትን እስስት ከጐመን ጋር ቀቅዬ በላሁ" እንዲል እኔም ደፍሬ እንዳልናገር ጭንቅ ሆኖብኝ ነበር "እሺ" ያልኩት፡፡

በእኔ የልጅነትና የወጣትነት ዘመን በከምባታ ባሕል የልቅሶ ስነስርዓት ከባድ ነበር። ይሁን እንጂ እንደሟቹ የኑሮ ደረጃ ይለያያል፡፡ ሟቹ ጦረኛ፣ አዳኝና ታዋቂ ከሆነ በሐብቱም ፈርጠም ያለና በኅብረተሰቡ ዘንድ መልካም ስም ያተረፈ ከሆነ ፈረሰኞች በየአቅጣጫው እየዞሩ ዝናዉን እየተረኩ ሞቱን ያውጁለታል። ይህም እስከ ሳምንት ድረስ ሊወስድ ይችላል፡፡ የቀብሩ ዕለት በአካባቢው በአለው ሰፊ ሜዳ ወይም በማኅበረሰቡ ታዋቂ የሆነ ሰው ደጃፉ ሰፊ ስለሚሆን ፈረሰኛውም ሆነ እግረኛው ሆ እያለ ሟቹን በማሞገስ ሴቶችም ተሰልፈው እያለቀሱ የሚገቡትን ተቀብለው

ሦስት ወይም አራት ጊዜ እየተመላለሱ ካለቀሱ በኋላ ሄደው ይቀመጣሉ። "ትልቅ ሰው" ለተባለው ደግሞ "ሞራ" እየተባለ ጀግና ማለት ነው ከብ ሠርተው ወይም ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየቱመላለሱ የሰውዬውን ዝናና መልካም ሥራ እያወደሱ አውራጅና ተቀባይ ሆነው ያለቅሱለታል። እነዚያ ተመርጠው በፈረስ መሞቱን የሚያውጁት (ለሣኑ ይባላሉ) ደግሞ ወደ ማታ ጊዜ ከነፈረሶቻቸው በየበኩላቸው የት ድረስ እንደሄዱና ምን ብለው እንደ ተናገሩ ከፈረሳቸው ሳይወርዱ እንድህ ፣ እንዲህ አልኩ" እያሉ ይናገራሉ።

እንደዚህ የአንዱን ሞት እንዲያውጅ የተላከው ሰውም ሙሉ ቀን ሳይሆን በግማሽ ቀን ተመልሶ መጥቶ ውሎውንና ያለውን ሲናገር "ምነው በአጭር ተመለስክ? ብለው ሲጠይቁት "እርሱስ ከዚያ ርቆ መቼ ሄዶ ያውቃል!" በማለት ንቀቱን ገለጸ ተብሎ ይነገራል። እንዲህም ያለ ነገር ስለሚኖር ምርጫው በጥንቃቄ መደረግ አለበት። ነጋሪት ዳላቂዎችም ተመርጠው ለቅሶው ከተጀመረበት እስከ ተቀበረበት ድረስ ያላቅሳሉ። ከቀብር በኋላ ደግሞ መስትንግዶው ይጦፋል። ሠንጋዎች ታርደው ጠላው ጠጁና አረቄው እየታደለ በሟቹ ስም የተደገሰው ድግስ በየዓይነቱ ይበላል። ከዚህ በኋላ ቤተዘመዱ ሐዘኑን ይቀጥላል። የመጣውም እንግዳ እንደዝምድናው ቅርበትና እውቀት ጊዜውን እያሰበ ወደየመጣበት ውሎ አድሮ ይመለሳል። አንዳንዱ ለቅሶ እስከ ወርም ይቆያል። ከዚያ እንደሟቹ ታዋቂነት በቀናትና ሳምንታትም የሚያበቃ አለ። ቦአ ተብሎ ደግሞ እንደተዝካር ይደገሣል። በዕለቱ ሕዝብ ተሰብስቦ የሟቹ መታሰቢያ አድርጐ ያለው በእርድ የሌለውም እንደየአቅሙ መታሰቢያውን ይፈጽማል።

ይህ "ነበረ" ለማለት ያህል እንጂ በአብዛኛው የኢኮኖሚውና የሃይማኖት ተጽዕኖ እያስቀረው ሄዷል። አቶ ሄራሞ አናሞ ስለዚህ ነገር ሲያስረዱኝ "እናታችን ሞተው ተቀብረው የቦአ (ተዝካር) ጊዜ እንደደረሰ ታላቅ ወንድሜ አቶ ወንታሞ





ሲያስታውሰኝ የሚጠበቅብኝን እህሉንም ብሩንም ሰጥቼአቸው በቀረው በምንም ሳልሳተፍ ፊደል ለመማር ቀጠሮ ወደነበረኝ ስፍራ ልማር ሄድኩ"[8] ብለዋል። ያ ማለት ጊዜው በ1940 ዎቹ መጀመሪያ ላይ ስለነበረ ይህ ጽሑፍ የሚዘጋጀው በ2006 ዓ.ም ስለሆነ በ56 ዓመት ውስጥ የሚሆነውን ለውጥ አንባቢው መገመት ይችላል። የወንጌላውያን ብዛትና የወንጌሉ ማየል በነባሩ ባሕልና ልማድ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ አሌ የሚባል አይደለም። የ86 ዓመቱ አቶ ሚቆሬ ደግሞ በበኩላቸው የነበረውን ሁኔታ እያስታወሱ "ቀድሞም ያንን ፊት እየነጩና ደረት እየደቁ ቢያንስ ሦስት ጊዜ እየተመላለሱ ማልቀሱን እጠላው ነበር" ካሉ በኋላ "የወንጌል አማኝ ከሆንኩ በኋላ መጀመሪያ ከተላቀቅኋቸው ልማዶች አንዱ የለቅሶ ስሥርዓት ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ ለቅሶ ቤት ሰተት ብዬ ገብቼ ስቀመጥ ሰው ሁሉ "ምን ነክቶታል" ብሎ አጉተምትሞብኝ ነበር" ብለዋል[9]።

በእውነቱ ከቤተሰብና ከቤተዘመድ ልባዊ ሃዘን በስተቀር የነበረው የለቅሶ ባህል ራሱ ሞቶ አብቅቷል ባይባልም ዳግም ነፍስ በማይዘራበት ጣዕረ ሞት ተይዞአል ማለት ይቻላል። ለዚህም አስተዋፅዖ ያደረጉ በርካታ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊና አስተዳደራዊ ግብዓቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡- እንደ ጀግንነት መለኪያ የሚቆጠሩ የአካባቢ ወይም የጎሣ የነበሩ ግጭቶች ቀርተው፣ ሰላም መስፈኑ፣ ለመታያ ይወጡ የነበሩ ፈረሶች በመኖ/ግጦሽ መሬት ጥበት ምክንያት ማርባት አለመቻሉ፣ ፈረስና ፈረሰኛም እየታነቀ መሄዱ፣ ሰው ለኑሮዉ ከሚያደርገው ትግል አልፎ የአደባባይ ታይታው እየራቀው መሄዱ የለቅሰውን ልማድ አክስሞታል፡፡ የመሬቱ ጥበት እንኳን ለታይታ ስነሥርዓቶች የሚተርፍ ምርት ለማምረት በቀን ሦስት ጊዜም ለመቀለብ የሚያወላዳ አልነበረም፡፡

ለምሳሌ አባቴ የአባታቸውን ይዞታ መሬት አራቱ ዎንድሞች ሲካፈሉት የደረሳቸው

[8] አቶ ሄራሞ አናሞ ጥቅምት 25/2006 የሰጡኝ ቃለ ምልልስ
[9] አቶ ሚቆሬ ዴሌቦ ጥቅምት 25 ቀን 2006 ዓ.ም. በነበረን ቃለ ምልልስ

ድርሻ በቂና ሰፊ ነበር። ይሁን እንጂ ሁለተኛውና ሦስተኛው ትውልድ የሆነ ወንድ ልጅ ሁሉ ያንኑ የአባቱን ድርሻ መሬት እየተቀራመተው ሲተለተል የአንዱ ልጅ ድርሻ አንድ ጥማድ በሬ የማያውል ሆነ፡፡ ከዚያው ላይ ቤት ሲሠራበት" አጥር ሲታጠርበትና ወሰን ሲከለልበት እያደር እየኰሰመነ ይሄዳል፡፡ የግብርናው ዘርፍ የከብት እርባታንም ስለሚያጠቃልል ለግጦሽ የነበረው ሁሉ መሬት እንኳን ከብት መቻል ቀርቶ ለሰውም ቀለብ በቂ የማያፈራበት ደረጃ ወርዶአል። መሬቱም ራሱ አፈሩ እያለቀና እያረጀ እንደሄደ ግንዛቤው የሌለውማ ገበሬ እሱኑ መልሶ መላልሶ ሲጭር ሲቧጥጥና ሲቆፍር አፈሩ ወደ ገልነት እየተለወጠ የተሰጠውን ዘር እንደቀድሞው ማብቀል አልቻለም። አሁን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተጀመረው የማዳበሪያ አቅርቦት ጥቡቱን ባያሻሽልም አፈሩ እንዲያገግምና የተዘራው ዘር የተሻለ ፍሬ እንደሚሰጥ ተስፋው ከፍተኛ ነው።

ከዚሁ ከመሬት ነገር ሳንወጣ በከምባታ ልማድ ሴቶች አግብተው እንዲሄዱ እንጂ በተወለዱበት ቆይተው የወላጆቻቸውን ይዞታ መሬት እንደ ልጅ አይካፈሉም። ሴቷም ልካፈል ብላ አትጠይቅም። ብትጠይቅም እንኳን በአግባቡ መልስ አታገኝም። አባቱን የሚወርሰው ወንድ ልጅ እንደሆነና መሬትም የወንድ ልጅ እንደሆነ ነባር ልማድና እምነት አኑረውታል። አሁን የመሬቱ ድርሻ እንደ ቁራሽ ቂጣ የሆነበት ጊዜ ቀርቶ ከትውልዶች በፊትም በተሻለውና የመሬቱ ስፋት በሚያጓጓበትም ዘመን ሴቶች ወዲዚህ ጨዋታ አይታደሙም። ቀድሞ ልማዱ፣ አሁን ድህነቱ ሴቶችን ከመሬት ይዞታ ውጭ እንደ አደረጋቸው ልብ ይሏል። የሴቶችን ጉዳይ ካነሳሁ አይቀር ስለ ቀድሞው አሁንም በከፊል ስለሚታየዉ የጋብቻ ሁኔታ ጥቂት ላካፍላችሁ ወደድኩ፤ ለምን ቢባል የእኔም ሆነ የእኔ ዘመን ሰዎች የግል ሰብዕናና ማሕበራዊ ገጽታ የተገነባዉ ባብዛኛዉ ያሳደገን ቤተሰብ ካረገልን ወይንም ካረገብን ሁለንተናዊ ግብዓቶች ነውና!





# 6. ጋብቻ በከምባታ ባህል

ጌታ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር በደነገገዉ መሠረት አደራረጉ ይለያይ እንደ ሆነ እንጂ ሰዎች እየተጋቡ እየበዙ፣ እየተባዙም ምድርን እየሞሏት አሉ፤ ወደ ፊትም እስከ ምፅዓት ድረስ ይቀጥላል። በከምባታ ልማድ ጋብቻ በሦስት ዋና መንገዶች ይከናወናል። ተራ በተራ እንያቸዉ፡፡

## ማባበል፣ ማግባባት - ሔረንቻ ወይም ሔረሚ

ሁለቱን ታሳቢ ጥንዶች የሚያውቅ ዘመድ ከወንዱ ወይም ከሴቷ ጋራ አግባብ ያላቸው (በአብዛኛው ጊዜ ለዚህ ተግባር የሚታጩት ሴቶች ሲሆኑ አክስትና የወንድም ወይም የአጐት ሚስት) የምትሆንህ/ የምትሆንሽ በማለት ማግባባት ይጀምራሉ። በተለይ ወንዱ በሰማውና ባየው ልቡ ከተሳበና ፈቃደኛ ከሆነ አግባቢዎቹ ሴቷን ለማሳመን በርትተው ይሠሩና የርሷን መስማማት ካገኙ በኋላ ልጅቱ በምስጢር ከቤቷ እንድትወጣና በወንዱ ዘመድ ቤት በማትደፈርበት ሁኔታ እንድትቀመጥ ተደርጎ "ሁለቱ ስለተስማሙ ፈቃዳችሁን" ተብሎ ሽማግሌ ይላካል። የሚላከውም ሽማግሌ በተራው ወላጆቹን ለማግባባትና ለማሸነፍ ጥረት ያደርጋል፤ ከተሳካላቸውና ስምምነት ላይ ከደረሱ ማጫ የሚወሰድበት ቀን ተወስኖ በስምምነቱ ጐዳና ጋብቻው የሚፈጸምበትን እርምጃዎች ይወስዳሉ። በመጀመሪያ ቢያንገራግሩና ተደፈርን ለማለት ቢሞክሩም የማጫውን ዋጋ ለማብዛት ካልሆነ በቀር ብዙም ፋይዳ የለውም፡፡

ለሴቷ ልጅ ይኸኛው መንገድ በመረጃ ደረጃ የተሻለ ይመስላል። ጉዳዩን ወደ እርስዋ የሚያመጡት ዘመዶች ስለ ወንዱ ማንነት ስለ ወላጆቹና ስለ ወገኖቹ (ዘር ሐረጉ) ይነግሯታል። አልፎም በግል እንዲገናኙ አለዚያም በሩቅ በሰዎችም መካከልም ቢሆን ለይተው ያመላክቱአታል። እርሷም ቢሆን አስቀድሞ የማየትና የመስማማት

ዕድል ይኖረዋል። አንድ ጊዜ ማጫ ከወሰደ በኋላ ወደ ቤቱ ወስዶ ትዳራቸውን መመሥረት ይችላሉ። ለነገሩማ ሴቷ ናት እንጂ ወንዱማ ምንም ጊዜ አይቶ ነዉ የሚመርጠው።

## ጠለፋ ምዱ (ምዷ)

ከሁሉም አስቀያሚ" ክብር የሌለውና በማን አለብኝነት በወንዱ አምባገነንነት ስር የወደቀ የጋብቻ ዓይነት ነዉ፡፡ በጉልበት አፍኖ ከመድፈር የማይለይና በደመነፍሳዊ ግፊት ብቻ የሚፈጸም ኢሰብዓዊ ድርጊት ነዉ። የትዳር መመሥረቻው ፍቅር ሲሆን ጠለፋ ደግሞ ፍጹም ተቃራኒው እንደሆነ ግልጽ ነው። ዕደሜ ልክ አብሮ ለመኖር የሚታቀድ ጋብቻ በሞገደኝነት ተጀምሮ እንዴት እንደሚዘልቅ ግራ ያጋባል። የዚህ ዓላማባለቤትየሆነውወንድቢጤዎቹንሰብስቦከአሳደመበኋላልጅቱየምትወጣበትን መንገድ አጥንተው ወደ ገበያም ይሁን ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ አድፍጠው ጠብቀው ከቀናው ባለቤቷ የሚሆነው አስቀድሞ በመያዝ ይሁን በመጎተት እጁን ከአሳረፈባት በኋላ ተባባሪዎቹ ቢችሉ ተሸክመው ባይችሉ ጎትተዋት ወደ አቀዱበት ይወስዳሉ። እንዳትጮህ አፏን አፍነው በበትርም፣ በአለንጋም፣ በጥፊም፣ በጡጫም ደብድበው እያንገላቱ ይወስዷታል፡፡ ለዚያውም የሚታየው ውጫዊ መቁሰልና መንገላታት ነው እንጂ ውስጣዊ ቁስሏንና የሰብዕና ውርደቷን ማን ተረድቶት!!

ስለዚህ ጉዳይ እማማን እንዴት እንደነበረ ሰኔ 21 ቀን 2006 ዓ.ም. ስጠይቃቸዉ በአጭሩ እንዲህ ነበር ያሉኝ "ጠለፋ አዋራጅ በንቄትና በማን አለብኝነት የሚደረግ ቤተሰብን ከቤተሰብ፣ ጐሣን ከጐሣ የሚያጋጭ አስቀያሚ ድርጊት ነው"። በዚሁ አጋጣሚ ወንድሜ ወልዴ ደለለው የሚያስታውሰዉ ታሪክ አነሳልኝ፡፡ ይኼውም አንዱ ዘመዳችን እንዷን ጠልፎ ወስዶ እንደ ነበር፣ የልጅቱ ዘመዶች ፈረሶቻቸውን ጭነው የጦር መሣሪያ ይዘው ሠልፍ ወጥተውብን እንደ ነበር፣ ከመዋጋት ይልቅ ልጅቱን መመለስ እንደሚሻል ቤተዘመድ ከመከረ በኋላ ተጠልፋ በመጣችበት





ሁኔታ ሳይሆን በዘመዶቿ ታጅባ በድል እንደተመለሰች ነበር ወንድሜ ያጫወተኝ፡፡

ያለግለሰቡ ፈቃድና ስምምነት አንድን ሰው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ አስገድዶ መውሰድ በሌላው ዓለም ከባድ ወንጀል ነው። ሕጋዊ አካል ለምሳሌ ፖሊስ አንድን ሰው በሆነ ወንጀል ከጠረጠረ አስገድዶ መውሰድና ምርመራ ማካሄድ ከዚያም እንደ ግኝቱ ሊለቀውም ወይም አሥሮ ወደ ፍርድ ሊያቀርበው ይችላል። ለጋብቻ ብሎ መጥለፍ ግን ሕጋዊ ነው ማለት ሳይሆን በልማድ ፈረስ ሲጋለብ እዚህ የደረሰ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ የተዳከመም ቢሆን ያልጠፋ ስለሆነ ሕግ አውጪውም አካል ሆነ ሕግ አስከባሪው ከቀበሌ አንሥቶ እስከ ፌደራል ድረስ ይህ አስከፊና ኋላ ቀር ልማድ እንዲጠፋ ርብርብ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም።

## "ልጃችሁን ለልጃችን (ቤቱ ፅኔ ቤቲ ሃኔ)"

ሦስተኛውና በሁሉም ዘንድ ወግና ማዕረግ ያለው ወላጅ ሁሉ የሚጠብቀውና በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ብቻ ሳይሆን የሚጠብቀው ጋብቻ በሁለቱ ወላጆች ወይም ቤተሰቦች ስምምነት የሚመሠረተው ትዳር ነዉ፡፡ የ"ልጃችሁን ለልጃችን" ጋብቻም ቢሆን በቀድሞ ጊዜ አስቸጋሪ ጐን ነበረው። ይህ አስቸጋሪ ጐኑ ሁለቱ ወላጆች ጠይቀው ተጠይቀውና ተስማምተው የሚፈጽሙት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ወንዱ አስቀድሞ ማንና መቼ እንሚያገባ የማወቅ እድል፣ ሙብትም አለዉ፡፡ ሴቷ ግን አንዳችም ሳትሰማ ለገዛ ጉዳዩዋ ባይተዋር እንደሆነች በሠርጓ ዕለት በሚደረጉት ልማዶች ሳቢያ ነዉ ዱብ እንቁ እሷን ለመዳር መሆኑን የምትረዳዉ።

ከልማዶቹ አንዱ ኮሶ ማጠጣት ነዉ፡፡ ኮሶውን በማለዳ ተነስተዉ በጥብጠው ወደአለችበት የቤቱ ጥግ ድረስ ሄደው የሚያጠጧት እናቷ ወይም አክስቶቿ ናቸዉ፡፡ በዚህ ጊዜ ማንን እደምታገባ እንደምንና ለምን ምንም ፍንጭ የሌላት ከሆነች - ኮሶውን

"ጠጪ" ለእነሱ ብሥራት ቢሆንም ለእሷግን የመርዶ ያህል ያስደነግጣታል፡፡ በግዳጅና በይሉኝታ ጫና ያንን መራራ የኮሶ ጽዋዋን ከጨለጠች በኋላ ሽሽታም በማታመልጥ ሁኔታ ትጠበቃለች፡፡ እንዲህ በድንገት በሰዓታት ልዩነት ላላየችው ላላወቀችው ሰው ትዳራለች፡፡ለዚህ አብነት የሚሆንና ከልጅነት ጀምሮ በአእምሮዬ ተሰክቶ የሚኖር አንድ ምሳሌ አለ። ያኔ አባባ "በከምባትኛ ካልተናገርክ" ብለውኝ ወደ አከስቴ ቤት መኮብለሌን ከፍ ብዬ መግለጼ ይታወሳል። እዚያ ባደረግሁት ቆይታ በቤተሰቡ የአከስቴ እንጀራ ልጅ የምትሆን የደረሰች በጣም ውብ ልጃገረድ ነበረች። እዚያ ከቆየሁባቸው ዕለታት በአንዱ ማለዳ ያ ጉደኛ የተበጠበጠ ኮሶ ሲሰጣት በድንጋጤ ውሀ ሆና እጇን ዘርግታ መቀበል እስከሚያቅታት ድረስ ሰውነቷ ዛለ። በመቆጣትም በማደፋፈርም ሆይ ሆይ ተባለና የኮሶውን ዕቃ በሌሎች ዕርዳታ ተቀብላ በእምባዋ እያማገች የገባው ያህል ገብቶ የፈሰሰው ፈስሶ ዕቃው ተጋባ። ከዓይኖቿ ይወርድ የነበረው የእንባ እንክብል በዚያ በሚያምር ፊቷ ላይ እንደ ጎርፍ ወረደ፡፡ የሃዘን ጭቃ የተቀባች አስመሰላት፡፡ ሰዓቱ ሲያረፋፍድ በዙሪያዋ በነበሩት ሰዎች ውትወታና ማደፋፈሪያ ተመርኩዛ ሳትፈልገው ለሙሽርነት መዘጋጀት ጀመረች።

ከነገሩ ሁሉ ለዚህ ጸሐፊ ሲቆጨው የኖረውና አብዛኛውን ሰው ሲያጓጓ የነበረው ያንን የመሰለች ውብ ኮረዳ ለማን ይሆን የተሰጠችው የሚለው ጥያቄ ነበር። መገለጡ አይቀሬ ነበርና ሁሉን ያጓጓው አቶ ሙሽራ ከአጀቡ ጋር ብቅ ሲል የተቀመጠበት ፈረስ እንጂ እርሱ ለዓይንም የማይሞላ ነጠላ ሰዉ ሆኖ ተገኘ፡፡ የሚያርፍበት ዓይነት አልነበረም። ያ ሁሉ ጓጉቶ ሲያየው የጠበቀው ሕዝብ ለግብ ተመትታ እንደተሳተች ኳስ ዓይነት የቁጭት ድምጽ ባያሰማም የሙሽራውን አቋም ሲመለከት ስሜቱ ያነኑ ያህል እንደነበር አስታውሳለሁ። በኮሶው ምሬት ማለዳውን ጀምራ የእንባዋ ዘለላ ሳያቋርጥ ሙሽራ ተብላ ተሸፋፍና በመጣላት በቅሎ ተጭና እንዳለቀሰች ፊቷን አዙራ አሳልፎ የሰጣትን ቤተሰብ ትታ ከማታውቀው ሙሽራና





ሠርገኛ ጋራ ወደ አዲሱ ቤቷ ተወሰደች፡፡

ይኼ በእድሜ ዘመኔ ካየሁት የከፋውና በማንም ላይ ሊደርስ የማይገባው፣ ከጠለፋም የማይተናነስ የጋብቻ አጋጣሚ ነዉ፡፡ ሆኖም የወላጆች ማስተዋል ሲታከልበት በአብዛኛው በ"ልጃችሁን ለልጃችን" የተመሠረተ ትዳር የሰመረ ይሆናል፡፡ በሁለቱ ተጋቢዎች ሳቢያ የቤተሰብና የቤተሰብ ዝምድና ዳብሮ ተዋልዶና ተከባብሮ ይኖራል። ለዚህም አንዱ ምክንያቱ በቅድመ ጋብቻ የሚደረገው ጥንቃቄ ይመስለኛል፡፡

ለምሳሌ "ልጃችሁን ለልጃችን" የሚል ጥያቄ ሲመጣ "የማን ልጅ ነው?" ከሚለው ተነሥተው ያለው ዝምድና ምን እንደሆነ ይመረመራል፤ የቅርብ ዝምድና የሚኖር ከሆነ ይሆናል አይሆንም በማለት ቤተሰብ ተወያይቶ በማረጋገጥ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ መልስ በአግባቡ ይመልሳል። የሥጋ ዝምድና እንደሌለ ከተረጋገጠ በኋላ የትጭጭትም ሆነ የሠርጉ ቀን ቀጠሮ ተወስኖ ሁለቱም ቤተሰብ ዝግጅቱን ይቀጥላሉ። ጊዜው እየተቃረበ ሲሄድ የቅርብ ዘመድና ወዳጅ ሁሉ ጉዳዩ አድርጐ በሚያስፈልገው ሁሉ በድግሱ ዝግጅት ይሳተፋሉ። ሴቱ በሴቱ ወንዱም በወንዱ ሥራ ተባብረው በማያስወቅስ መልኩ ሙሽራውንና አጃቢዎቹን እንዲሁም የሠርጉን ዕድምተኞች ይቀበላሉ። ይህ እንግዲህ እንደየቤተሰቡ አቅምና እውቀት ሊበዛም ሊያንስም ይችላል። የሠርገኛው ሙሽራዋን ይዞ መመለሻ ጊዜ የሚወሰነው በቦታው ርቀትና እንደወራቱ የዝናብ ጊዜ ከሆነ የማዘግየት ሁኔታ ስለሚፈጥር ሠርገኛው እየተጠበቀ ግብዣው ይቀጥልና ሲበላ፣ ሲጠጣ፣ ሲዘፈን ይከረማል።

# ምዕራፍ ሦስት
# ወንጌል፣ ወንጌላውያንና ማሕበራዊ ለውጥ

## 7. የመጀመሪያዎቹ የወንጌል መልእክተኞች

አውራጃው ከምባታና ሐዲያ ነው። ይህ በመልክአ ምድሩ በደጋ ወይና ደጋና ቆላ የተባረከ ከመሆኑ ባለፈ በሰሜን ጉራጌ፣ በደቡብ ወላይታ፣ ከምዕራብ ከፋና በምሥራቅ አርሲ ያዋስኑታል። ከነዚህ አራት አቅጣጫዎች የትኛው ለወንጌል በር ሊሆን ይችላል ብሎ መጠየቅ ለመጀመሪያዎቹ የወንጌሉ መልእክተኞች ብቻ የሚተው ሣይሆን አሳቢ አእምሮ ሁሉ ስልታዊ አቅጣጫውን ማጤን ሰብዓዊ ግዴታ ነው።

ፈረንጆች "There is a method to madness" ለእብደትም ዘዴ አለው። የሚሉት አባባል አላቸው። ያ እንደመስቀሉ ደመራ እሳት በየቦታው ቦግ ብሎ የተቀጣጠለው የወንጌል እሳት ከበስተኋላው ዘዴና እቅድ እንደነበረው ቆም ብሎ በሰከነ መንፈስ ሲያዩ እየተገለጸ ይሄዳል። ይህንን አቶ ወንድዬ አሊ በጻፈው ገለጻ:-

> "ዶ/ር ላምቤና የቡድኑ አባላት ዛሬንና ዘላለምን በእጁ የያዘውን ሁሉን ቻይ ጌታ ተስፋ አርገው እግዚአብሔር ምርኮ አድርጎ በሚሰጣቸው አካባቢዎች ወንጌልን ለመዝራት የካቲት 28 ቀን 1920 ዓ.ም (March 7/1928) መድረሻቸውን ጅማ ለማድረግ ከአዲስ አበባ ተነሱ. . . " ካለ በኋላ:-

ሚስዮናዊያኑ ሥራቸውን ከከፋ ክፍለ አገር ለመጀመር እና ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ለመዝለቅ ያቀዱት ገና ከአገራቸው ሳይነሱ እንደነበር አስረድቶ በመቀጠልም።

> "ስድሳ አምስት በቅሎዎች፣ 20 አህያዎች፣ ዘጠኝ ፈረሶች፣ 25 ዕቃ ተሸካሚ ሠራተኞች፣ 22 ለጓሚዎች /የጋማ ከብቶችን የሚነዱ/ እና ሌሎችንም ሰዎች





> አስከትለው ጉዞአቸውን ወደ ጅማ መስመር አቀኑ:: መንገደኞቹ የተያያዙት የጅማን መስመር ስተው በስተ ምሥራቅ ደቡብ ባለው መንገድ ቀጥለው ሲጓዙ ርቀው ከተጓዙ በኋላ ነው የጅማን መንገድ እንደሳቱ የተረዱትና ከቀናት ጉዞ በኋላ ማረቆ እንደደረሱ›› ወንድዬ እንደሆነ ይገልጻል።[10]

ይህንን ወራሪ ኃይል የመሰለ ተጓዥ ቡድን ለጅማ አቅዶ ተነስቶ ማረቆ እንዲደርስ ምን? ማን? መራው ያሰኛል። በግምታዊ መልስ ከመዳከር ይልቅ ከአሜሪካ ሳይነሱ የጠነሰሱትን ሚስዮናውያን ከማረቆ ወደ ሆሳዕና ብሎም ወደ ወላይታና ሲዳማ የመራቸው ያ ተስፋ ያደረጉት ሁሉን ቻይ ጌታ እግዚአብሔር እንደሆነ ለማመን በነዚህ ሁሉ ቦታዎች የተጫረው የወንጌል እሳት ብሎም እስከዛሬ ዳብሮ ያለው ሥራና ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ያለው ወንጌልና ወንጌላውያን ይመሰክራሉ።

ፈቃዱ ጉርሜሳ በበኩሉ"የማዕከላዊ ደቡብ የወንጌል እንቅስቃሴ ማዕከላት የተጀመሩት በሱዳን ኢንተሪዮር ሚሲዮን ባልደረቦችና ከሚስዮኑ መምጣት በፊት ሆነ ከእነርሱ መምጣት በኋላ የወንጌልን እምነት ተቀብለው በሥራው በተሳተፉ አገር በቀል ሚስዮናውያን አማካይነት ነበር" ብሏል።[11] እነዚያ "አገረ በቀል" ወንጌላውያን በድርጅታዊ ምልመላና ደመወዝ የተቀጠሩ ሳይሆኑ ውስጣቸውን በሞላው የጌታ ፍቅር ተነሣሥተው በወንጌለ ምሥራች ያገኙትን ሰላምና ደስታ ለቤተሰብ፣ ለጎረቤት፣ ብሎም ለአገር ሁሉ ማድረስ ቆርጠው በመስዋዕትነት የተነሣሱ ነበር። በነዶ/ር ላምቤና ባልደረቦቻቸው የተጀመረው ረዥም ጉዞ ድንበር እየተሻገረ ባህልንና ቋንቋን ሁሉ እያካተተ ወደ "እስከ ዓለም ፍፃሜ" እየተጓዘ ነው።

ከአሥራ ሁለቱ ሽማግሌዎች ጋራ ጥቅምት 25 ቀን 2006 ዓ.ም ላደረግነው ውይይት

[10] ወንድዬ አሊ፤ በመከራ ውስጥ ያበበች ቤተ ክርስቲያን፣ ቅጽ አንድ ከ1920-1933 የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ 2ኛ እትም 2000ዓ/ም

[11] ፈቃዱ ጉርሜሣ ኩሣ፤ የወንጌል እምነት እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነየሱስ- ኢ.አ 1999 ዓ.ም.

አንዱ ታዳሚ የነበሩት አቶ አየለ አንዮ ነበሩ። እርሳቸው ውይይቱ አልቆ ምሳም ተበልቶ ሊያበቃ ሲል ደረሱና ምክንያታቸውን ሲገልጹ "ልጃቸውና ባለቤታቸዉ ሚስዮናውያን ሆነው ወደ ባንግላዴሽ ትላንትና ማታ በረሩ። እኔም ጸልዬ እንድሸኛቸው ስለጠየቁኝ አዲስ አበባ ሄጄ ሸኝቼአቸው አሁን ተመለስኩ ለእነርሱ ጸልዩላቸው" አሉ። የወንጌሉ መልእክት ልክን የሚያሳርፈው ሲያስተላልፉት ነው እንጂ ይዘውት ሲቀመጡ እንዳልሆነ ግልጽ ነው።።

የሱዳን ኢንተሪዬር ሚሲዮናውያን ቀናት የፈጀ ጉዞአቸውን ተጉዘው (በ1920 ዓ.ም) ሆሣዕና ደረሱ።። መጀመሪያ ዱባንቾ ቀጥሎም ላምቡዳን ከሞከሩ በኋላ ቦብቾ ለዘላቂ የሚሸኑ ጣቢያ በኮንትራት ወሰዱ። ይህም በቀላሉ የተገኘ ሳይሆን ከብዙ መደናቅፎች በኋላ የተሳካ ነበር።። አንዱና ከባድ የነበረው መልከኞች በሁለት ምክንያቶች የሠፈራ ቦታ ሲነሱአቸው ቆይተዋል። አንደኛው ምክንት የኦርቶዶክሱን እምነት በመደገፍ ሲሆን፣ ሁለተኛ ምክንያት የወንጌል እምነት የጭሰኛና የትንንሽ ሰዎች ሃይማኖት ነዉ ብለው ስለሚያምኑ እንኳን ለሚስዮኖቹ ማረፊያ መስጠት ቀርቶ የነበሩትም ለቅቀው ቢወጡ በወደዱ ነበር። በጊዜው የነበረውን የመልከኛን ሥርዓት ግፍ ሲገልጹ የ86ቱ ዓመት አንጋፋ አቶ ሎዲሶ ሎዴቦ እንዲህ ይላሉ፡- "መሬቱና የመሬቱ ውጤት ሳይበቃቸው ቀርቶ ሥጋችንን ቆርጠው ቢበሉም የሚያጠግባቸው አይመስልም ነበር።[12] በአንድ ወቅት የሣር ቤቴ ተቃጠለና ምትኩን በቆርቆሮ ለመሥራት ፈቃድ ለመጠየቅ አዲስ አበባ ድረስ ሄጄ ማመልከቻ ጽፌ የነጋድራስ ተሰማ ወኪል የነበረች ገነት ተሰማ ትባል ለነበረች ሴት ልጅ ወሰጄ አስገባሁ። ሳምንት ሙሉ ደጅ ሲያስጠኑኝ ቆይተው ፈቃዱን ሲሰጡኝ ‹መሬቱን በምትለቅበት ጊዜ ቆርቆሮውንም ምስማሩንም ነቅለህ ይዘህ ትወጣለህ› አሉኝ።። ‹እሺ እግዚአብሔር ያውቃል ብዬ› ፈርሜ መጣሁና ቤቴን ሠራሁ። ይሁን እንጂ ምስማሩንም ቆርቆሮውንም ሳልነቅል 1969 ዓ.ም. የመሬት አዋጅ መጥቶ እነርሱን

[12]አቶ ሚቆሬ ዲሌቦ ጥቅምት 25 ቀን 2006 ዓ.ም በሽማግሌዎች ፊት ከሰጡት ቃለ ምልልስ፣ ዱራሜ





ነቃቀለልኝ።።[13]

መልከኛዉ ወንጌልን የማይፈልግ ርስት የሌለውና ተርታዉ ሰዉ ወንጌልን መፈለጉ ከመንፈሳዊ ፍላጎት አልፎ ትልቅ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቅራኔ እንደ ፈጠረ የመስኩ ባለሙያዎች በተለያ መንገድ ገልጸውታል።። በዚያን መሬት ያለው ኃይልም ስላለው ከመሬቱ ሊፈነቅል፣ ኪራይ ሊጨምር፣ ግብር ሊያበዛ የመሬቱን ውጤት በአብዛኛው ለራሱ የማድረግ ኃይል መኖሩ ብቻ ሳይሆን እየተገበረ በወንጌል አማኙ ላይ ያሳደረው ጫና ተዘርዝሮ እንደማያልቅ በተለያየ መልኩ አባቶች ያስታውሱታል። ስተፋን ግሬንስቴድ ሲጽፍ፡- "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የመልከኛውና የባለርስቱ አካል እንደመሆኗ የገባርን ሥርዓት መቀበል ብቻ ሳይሆን ከተማን እንደምሽግ በመጠቀምና በማስገደድ ስለመጡ ነፃ አስተሳሰብ ላለው ሕዝብ መልካም የሆነ ትምህርት አዘል ምርጫ አልፈጠረችለትም" ሲል ዘግቧል።[14] የወንጌሉ ባለቤት ግን ከሰው ሁሉ ስትራቴጂ በላይ ስለሆነ የወንጌሉ አበቃቀል በአንድ ሥፍራ ወይም በአንድ አቅጣጫ ሳይሆን እንደ ደመራ እሳት በየአቅጣጫውና በየሥፍራው ቦግ ብሎ ሲታይ የአእምሮ አግራሞትን ተራራ ያሳክላል። በሰሜን በሆሣዕና ዙሪያ የወንጌሉ እሳት ሲለኮስም በደቡብ ከወላይታ ወደ ሰሜን በኩል ሾኔ ላይ ተንቦለቦለ። በመሐል በቃጫና በሚሽግዳም የወንጌሉ እሳት እየተያያዘ ሳለ በምዕራብ በአሸራ ማን ለኩሰው የሚያሰኝ የወንጌል እሳት ተጧጧፈ።

በሆሳዕና ዙሪያ የወንጌሉ አውታሮች የተባሉት አቶ ሽጉጤ ዳዳ፣ አቶ ሰብሮ ወሦሮና አቶ አባጎሌ ኑነሞ ሲሆኑ በደቡብ ቆላው አቶ ደዕሞ አበቦና ወንድማቸው አቶ ደዴቦ አበቦ፤ በመኻል ደጋው ደገሞ ባቦ ባቾሬ፣ አቶ ባፋ ሰላሙ፣ አቶ አጋፋሪ ሰላሙ፣ ከዚያ ወደ ደቡብ ምዕራብ ደግሞ አቶ አባይ ኤደም የወንጌሉን ብርሃን ያዩ

[13]ሎዲሶ ሎዴቦ በተመሳሰሳይ . . .

[14]Staffan Grenstedt: Ambaricho and Shonkola. The faculty of Theology, Uppsala University , 2000 Pg 65

እንደ ኦሎምፒክ ችቦ ይዘው የሮጡ ያቀበሉና ያደረሱ ሲሆን እሳቱም ተንቀልቅሎ እንዲነድ ቆስቋሾችና ማገዶውን በመጨመር የሚያቀጣጥሉ ነበሩ። "ከባዕድ ፊት ቆርሰህ ወደ ዘመድህ ዞረህ፣ ዋጥ" እንደሚለው አባባል የወንጌል ችቦ የደረሳቸው ሁሉ ያስተላለፉት በሁለት ዋና ዋና ዘዴዎች ነበር።

## በመጀመሪያ፡- ወንጌልን ለቅርቦቻቸዉ አደረሱ

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው አባባል የወንጌሉን የምሥራች የሰሙና የተቀበሉት ሁሉ በአብዛኛው ያሰሙት ለቅርብ ዘመድ፣ ጓደኛና ጎረቤት ነበር። ቃጫ ላይ የሰሙትን ወንጌል ወደ ሚሽግዳ ያወጁት በጋብቻ ወደ ተዛመዱት ወደ አቶ ሰደኖ አምቦሴ ቤትና ቤተሰብ ነበር። ይህንን ለዚህ ጸሐፊ የተረኩት አቶ ሄራሞ አናሞ ናቸው። ጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ.ም በመኖሪያ ቤታቸው ባደረግነው ቃለ ምልልስ የነበረውን ድባብ ሲገልጹ አባባ ሄራሞ እንዲህ አሉ፡-

> "ሰውን ሁሉ የቃልቻ ግብርና "የሞት ዛቻ" ማስፈራሪያ ሠልችቶት ነበር። ሌላው ደግሞ ለኦርቶዶክስ እየተባለ የሚጠየቀው ግብርና የአማራው ባለ ርስት በየጊዜው የሚጠይቀው የመሬት ግብርና የአሽከርነት ሥራ ሕዝቡን እንደ ቅንቅን ቢያራግፉት የማይለቅና መሄጃ ያሳጣ ነበር። እኔም ራሴ ለምሳሌ የእናታችንን "ቦአ" እንደ ተዝካር የምናወጣበት ጊዜ ስለነበረ ድርሻዬን ሊታላቅ ወንድሜ ለአቶ ወንታሞ እህልና ሌላውን የሚያስፈልገውን ሰጠሁ፡፡ ነገር ግን በውስጤ ለምን? የሚል ጥያቄ ባደረብኝ ወቅት ነበር ስለ ወንጌልና ስለ አማኞች የሰማሁ።፡[15]

## ሁለተኛም፡- በየገበያው ወንጌልን ዐወጁ

መቼም በዚያን ዘመን ሰው ወደ ገበያ የሚወጣው ሊሸጥና ሊገዛ ብቻ አልነበረም። ገበያ የማሕበራዊ ግንኙነትና መረጃ የመለዋወጫ መድረክ፣ እንዲሁም የመዝናኛም ሥፍራ ነበር፡፡ የመንግሥት አዋጅ፣ የሹም ልፈፋ ወይም የአዋቂ ትንግርት የሚነገረዉ ገበያ ላይ ነበር፡፡ በዚያን ዘመን በረኸኛም ዘንግ ደበሎውን ለምልክት አንጠልጥሎ፣ ድምጹን ከፍ አድርጎ "አዋጅ አዋጅ የደበሎ ቅዳጅ" ተብሎ ሲለፈፍ ሕዝቡ አዲስ ነገር መከሰቱን በቀላሉ ይረዳል፡፡ ግር ብሎ  ወደ ሚናገረው ሰው ይጠጋል፡፡ የሰማውን ለሌሎች ለማሰማት ደጋግሞ ያዳምጣል፡፡

ይህንን ዘዴ ወንጌላውያኑም ተጠቅመውበታል። ይህንን ያደርጉ የነበረው እንደሌላው አዋጅ ብለው ደበሎ ይዘው ሳይሆን በሚታይ ሥፍራ ቆመው "መና መጮጭ! መና መጩሬ" (ሰው ሆይ ስማ) በማለት በከምባትኛ /ሐዲይኛ የሕዝቡን ጆሮ ይስቡ ነበር። ይህንን ባህላዊ የመገናኛ ዘዴ ከተጠቀሙት መካከል እንደ አቶ ዳዕሞና እንደ አባይ ኤደሞ የመሳሰሉ ጎበዝና ደፋር የወንጌል አርበኞች ይጠቀሳሉ፡፡ አቶ ዳዕሞ ራሳቸው ወንጌልን በመጀመሪያ የሰሙት በሾኔ ገበያ ከወላይታ መጥተው ከሰበኩት ወንጌላውያን እንደነበረም አጽንተው በተደጋጋሚ ካስተማሩአቸው መልእክቶች ጋራ አያይዘው መስከረዋል።

## ሦስተኛ፡- ፊደል ማስቆጠርን እንደ ወንጌል ስርጭት ስልት ተጠቀሙበት

ሌላው ከወንጌል ጋር አብሮ የመጣው ፊደል የማወቅ ጥማት ነበር። የማንበብና የመጻፍ ፍላጎት የተለየ ረሃብ የለቀቀበት ሕዝብ ለወንጌሉ ከነበረው ጥማት ያላነሰ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። የነፍሱን እሥራት በወንጌል ሲፈታ የመሃይምነትን እስራት ደግሞ ፊደልን ተምሮ፣ ማንበብና መጻፍ በመቻል ለመገላገል ቆረጠ፡፡ አቶ ዮሐንስ መኪሶ በወጣትነታቸው ጌታ የሱስን ተቀብለው ፊደልን ተምረው ማንበብ ስለቻሉ ለአስተማሪነት ወደ ቤናራ ቀበሌ በ1936 ዓ.ም ገደማ ተላኩ። አባባ ሄራሞ ፊደል የቆጠሩበትን አጋጣሚ እንዲህ ተርከውልኛል፡-

> "በደቦ ሥራ አንድ ወዳጃችንን እየረዳን' ነበር። በደቦ ከተሳተፍነዉ ጓደኞቼ አብረን ስንሠራ ከሰዓት በኋላ የፊደል ትምህርት ስለሚሰጥ ቶሎ

[15]ሄራሞ አናሞ፣ ጥቅምት 25 ቀን 2006 ዓ.ም. በመኖሪያ ቤታቸው ባደረግነው ቃለ ምልልስ

> ቶሎ ሠርተን ወደዚያ እንሄዳለን፣ ሲሉ ሰማኋቸዉ:: "እኔም እሄዳለሁ" አልኋቸው። ሥራችንን አፋጥነን ጨረስንና "ሰው ምን ነካቸው እያለን ተነስተን ሄድን"አቶ ሶደኖ ቤት ስንደርስ ዮሐንስ እኔን እያየ "አንተ ለምን መጣህ" አለኝ። ፊደል ለመማር ነው የመጣሁት ብዬ ስመልስለት መጀመሪያ ኢየሱስን ተቀበልና ትማራለህ አለኝ እኔም እቀበላለሁ አልሁት። ወዲያው "የሚባለውን በል" አለኝና እጄን አንሥቼ ያለውን እያልኩ ጌታ የሱስን ተቀበልሁ። ከዚያ ስንወጣ ዑጋሞ የተባለው ጓደኛዬ "ዛሬ ናቅሁህ ምን ነካህና እንደዚህ በጣም ቸኰልክ" አለኝ። ከዚያ ወጥተን ስንሄድ ሌላውን ጓደኛችን ጉንቱራን አገኘነውና ስንነግረው እርሱም አመነ"።

አቶ አስፋው ባቾሬና አቶ ሙለነህ ባቾሬ ስለአባታቸው ሲነግሩኝ አባታቸው አቶ ባቾሬ ወንጌልን ቃሜ ካሉት አማቻቸው ሰምተው ተቀበሉና ትንሽ እንደሰነበቱ ታወቀባቸውና የአካባቢው ሕዝብ በብዛት ሽሬፋ ሜዳ ወጥቶ "ሃይማኖታችንን ትቷል፣ ስማችንን አጉድፏል፣ ከዛሬ ጀምሮ ከብቱ ከከብታችን፣ ልጆቹ ከልጆቻችን እንዳይገናኙ፣ እሳት እንዳይጭር ቢሞትም እንዳንቀብረው አግልለነዋል" ብለው ወሰኑባቸው:: እሳቸውም ከተቀመጡበት ተነሥተው "ለኔ ክርስቶስ ሞቶ ስለተነሳልኝ እኔ አልሞትም፤ እናንተ ስትሞቱም አልቀብራችሁም፤ እኔም አግልዬአችኋለሁ" ብለው ወደ ቤታቸው ተመለሱ:: ከዚያም ጎረቤታቸው የነበረው አቶ ቦራጎ የሚበለውን ሰው ጠርተው እንደሰማኸው እኔን አግልለውኛል፣ ለማንኛውም አንተም እንደ እኔ እመንና አንዳችን ለሌላችን እንደራረሳለን" ሲሉት እሺ ብሎ ጌታ ኢየሱስን አመነ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ በሳምንት ጊዜ ውስጥ በአቶ ቦራጎ ቤት ይኖር የነበረ ወንድሙ በድንገት ሲሞት ሁለቱ የእምነት ጣምራዎች የሟቹን አስከሬን በአልጋ ተሸክመው ወስደው መቃብር ቆፍረው ቀበሩት::"[16]

በእንዲህ ዓይነት የወንጌሉ ብርሃን ማሕበራዊዉን ድባብ ቀስ በቀስ ሲሸረሽረዉ

[16] ቃለምልልስ፣ሕዳር 10 እና 17 ቀን 2006 ዓ.ም።





በሰው ላይ የተዘራዉ የፍርሃት መንፈስ በቀስታ እየተወገደ የእምነት ጥንካሬ ሥር እየሰደደ መጣ:: ነብዩ ኢሳይያስ የጻፈው የጌታ ሥራዎች አንኳር የሚባለው የምንባብ ክፍል ከላይ የተጠቀሰው አሳብ ፍንትው አድርጎ ይገልጸዋል።

> "የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ ልኮኛል። የተወደደችውን የእግዚአብሔርን ዓመት አምላካችንም የሚበቀልበት ቀን እናገር ዘንድ የሚያለቅሱትንም ሁሉ አጽናና ዘንድ እግዚአብሔር ለክብሩ የተከላቸው የጽድቅ ዛፎች እንዲባሉ ለጽዮን አልቃሾች አደርግላቸው ዘንድ በአመድ ፋንታ አክሊልን፣ በልቅሶም ፋንታ የደስታን ዘይት በሐዘንም መንፈስ ፋንታ የምስጋናን መጎናጸፊያ ዘይት፣ እሰጣቸው ዘንድ ልኮኛል"(ኢሳ 61÷21-23)::

መልእክቱ ለእሥራኤል ሕዝብ ትንቢት ነበር፤ ለከምባታና ሐዲያ ሕዝብ ግን የምሥራች ሆነው። ነፍስና ሥጋው ተጨንቆ፣ ተወጥሮ የነበረ ሕዝብ በወንጌል መፈታት ሲመጣለት፣ ጨለማው ሲገፈፍለትና በሞት ፈንታ ሕይወት ሲታወጅለት፣ እፎይታና ዕረፍት ሆነለት:: እውነትም የምሥራች!

## 8. ወንጌል ያስከተለዉ ማኅበራዊ ለውጥ

ከወንጌል ጋራ አብሮ የመጣው ማኅበራዊ ለውጥና ትሩፋቱ የትየለሌ ነው። በቀድሞው ዘመናት መልካሙ ሁሉ እየተዘረፈበት፣ ተስፋው ተወስዶበት፣ ባለርስት እንደ ቁራኛ (Cancer) የመጠመጠው ሕዝብ የወንጌል ብርሃን ሲበራለት የማሕበራዊ ሕይወት ዘይቤውም ተለወጠ:: ወንጌል የማይነካዉ የሕይወት ዘርፍ ምንም እንደሌለ የተገነዘበው ወዲያው ነበር። ከነዚህም ትሩፋቶች መነገር ካለባቸው

ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸዉ:-

**መማር**

ይህ ሲባል የአሁኑ አንባቢ አእምሮ ወደ መደበኛ ትምህርት ሊዘልል ይችላል። ይሁን እንጂ ምንም ባልነበረበት የተገኘውን ማጣጣምና ማወቅ የሌላውንም ተስፋ ያዳብራል። ያኔ መደበኛ ትምህርት ተብሎ የሚታሰብ እንኳን ባይሆንም ከመጣው ፊደል እውቀት ማንበብና መጻፈ ተወለዱ። በመሠረቱ ማንበብና መጻፍ ታልሞ የነበረው መጽሐፍ ቅዱስንና ወንጌላትን ለማንበብና ለመረዳት ለማስተማርም ቢሆን በዚህ ብቻ አልተገደበም። ይህን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ወቅት አሰፋው ባቾሬ የ86 ዓመት አዛውንት ነበሩ። ከ75 ዓመት በፊት ለመማር ምን እንዳነሳሳቸው ሲገልጹ አንድ የሚያውቁት "ማንበብና መጻፍ የቻለ ሰው አንድ የግዢና ሽያጭ ውል አዋውሎ ሲያስፈርም ሦስት ማርትሬዛ ብር ሲከፈለው አየሁና እኔም ብማር እንዲህ ላገኝበት እችል ነበር በሚል ቁጭት አጎቶቼ ጋ ቃጫ ሄጄ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ፊደሉን ጨርሼ ማንበብ ቻልኩ።" ወዲያውኑ መጻፍ ጀመርኩ"[7]፤ በማለት አስረድተውኛል። የዚህን ዓይነቱን መነሣሣት (Motivation) በገንዘብና ለገንዘብ ብቻ ሳይሆን ራሱ ማንበቡና መጻፍ መቻሉ በሰውም ፊት ቆሞ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ ማስረዳትና ሌላውን ማስተማር ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው ፍላጎት ነበር።

ይህንን የሚያህል የትምህርት ጉጉት ባደረበት ሕዝብ ላይ ነው የሱዳን ኢንተሪዮር ሚስዮን ባንድ እጅ የወንጌልን ብርሃን ችቦ ይዞ በሌላው እጅ "ማንበብ ይበቃሃል" የሚል የትምህርት ፖሊሲ ነድፎ የነበረዉ:: የአገሬዉ ሰዉ ከ4ኛ ክፍል በላይ እንዳይማር ገደብ ማበጀቱ "ራቁቱን ለተወለደ ደበሎ መቼ አነሰው" ዓይነት አስተሳሰብ መሆኑ ነዉ:: የሚሲዮኑ ፖሊሲ በጊዜዉ ብዙ ወጣቶችን ብቻ ያስከፋ ብቻ ሳይሆን ወደ ሌሎች ቤተእምነቶች እንዲፈልሱ ምክንያት የፈጠረ እንቅፋት

[7] አሰፋው ባቾሬ ፤ ሕዳር 10 ቀን 2006 ዓ.ም. በቤታቸው የሰጡኝ ቃለ ምልልስ





ነበር::

## በሥራ መትጋት

ጳውሎስ በ2ኛ ተሰሎንቄ ም 3፥10 ላይ "ሊሠራ የማይወድ አይብላ" ያለው ምዕመኑን ሁሉ ለሥራ ያተጋ ትምህርት ነበር። የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሥራዬ ብለዉ አማኞች ጠንክረዉ ሠርተዉ ኑሯቸውን እንዲያሸንፉ፣ ቤተሰባቸውን እንዳያስርቡ ይከታተሉ ነበር:: የአማኙ ጓሮው በተለያዩ አትክልት ማልማቱን፣ ማሣውን በትክክል ማረሱን፣ ዛፍ መተከሉን እያዩ ጥሩ የሠራውን እንደ ምሳሌ በየስብሰባው በስም እየጠቀሱ እውቅና ይሰጡታል:: የሰነፈውንም እንደዚሁ ምን ማድረግ እንዳለበትና የጌታን ስም እንዳያሰድብ ያስተምሩታል። ስንፍናዉን ማራገፍ ያቃተውን በጉባኤ ይገስጹታል:: በዚህ ረገድ:- እኔ ባደግሁባት ጸሎት ቤት ተሰብስበዉ ይህን መረጃ የሰጡኝ አባቶች ትዝታቸውን እንዲህ አጋርተውኛል።

> "አንድ አባለጀቦ የሚባሉ በእድሜአቸዉ ጠና ያሉ ለስንፍና የተመቹ፣ ሥራ የማይወዱ ሰዉ ነበሩ አሉ:: በአንዱ ሰባት ጉባዔ (ለመሊያአን) ሁኔታቸውን ያወቁት ሰዎች ተነሥተው "ሚስትህና ልጆችህ በቤት እየተራቡ እዚህ መሰብሰብ አትችልም" በማለት በጉባኤ ፊት ገስጸው፣ ከስብሰባዉ ሸኙዋቸው።
>
> ከሦስት ዓመት በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች "ኑና እዩ" የሚል መልእክት ላኩባቸዉ - የሠሩትን ለማስጎብኘት:: በጥሪዉ መሠረት የተላኩ ሰዎች የግምገማ ሪፖርታቸውን አቀረቡ:: ባጭሩ:- በከምባቲኛ
>
> ***"ከበሬ እህኖ በአ ቢጋን ዘኪዕኑ ሁጇተንቴዕ" ማለትም "ለአሁን አይደርስም እንጂ ለበኋላስ ተሰርቷል"***

"የማይሠራ አይብላ" ካለው ከጳውሎስ አባባል ጋራ ሙሉ ለሙሉ የተስማማው የአውራጃው ምዕመን በጠቅላላው የሥራ ውጤት በዓይን የሚታይና በእጅ የሚዳሰስ ጠላትን የሚያስቆጣ ወዳጅን ደስ የሚያሰኝ ሆነ። መሬቱና የአየሩ ጠባይ የሚቀበለው ዓይነት ተክል ሁሉ ብቅ ብቅ ማለት ብቻ ሳይሆን የተመልካችን ሁለንተና የሚመስጥ ሆነ። ሙዙ፣ ብርቱካኑ፣ አቮካዶውና ማንጎው ሸንኮራው በእሽቅድምድም ምድሪቱን ሞላው። ጥሩ ቤት መሥራት፣ ቀዬውን ማሳመር፣ ፀአዳ ልብስ መልበስና የመሳሰሉት የወንጌላውያን ምልክቶች ሆኑ። ቢሆንም በጉልተኛው ይደረግ የነበረው ተጽዕኖ አሌ የሚባል አልነበረም። ሰውም ዕውቀቱንም ዘሩንም ሆነ ችግሩን ለማካፈል በእጅጉ የተዘጋጀ ነበር፤ እንደ ሽማግሌዎቹ ትውስታ።

### ፍርሃት ቀረ

የመልከኛው "እሥርሃለሁ፣ እፈነቅልሃለሁ" ወዘተ፤ የቃልቻውና የጠንቋዩ "እገድልሃለሁ፤ እወርስሃለሁ። እንደዚሁም የኦርቶዶክሱ "እገዝትሃለሁ" በማለት ሕዝቡን አሥሮት የነበረው ማስፈራሪያ ቢሆንም ሥጋን እንጂ ነፍስን ስላልሆነ የወዲያኛው ዓለም ሕይወት ዘለዓለማዊ ስለሆነ ለዚህ ጊዜያዊ ለሆነው ሕይወት መጨነቅ ሥፍራ አጣ። ያ ማለት ሥርዓት ጠፋ ማለት እንዳይመስል፤ ባለሥልጣን ማክበር በወንጌሉ ትምህርት የተካተተ መጽሐፍ ቅዱሳዊም ስለሆነ ለሥርዓት አልባነት ሥፍራ አልተሰጠውም። የማንበብና የመጻፍ ችሎታም ለመንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን የፍትሐብሔሩንና የወንጀለኛውንም ሕግ አንብበው የተረዱ፣ ላልተረዱትም መቆም የቻሉ ሰዎች ብቅ ብቅ ማለት የጀመሩት ከወንጌል በኋላ ነበር።

ወንጌል ለከምባታና ሃዲያ ሕዝብ እነዚህን ትሩፋቶች ቢያመጣም ቅሉ ለአወንታዊ ባህላዊ እሴቶችና ልማዶች አስፈላጊው ጥንቃቄ ስላልተደረገ ለደጋግ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሐብቶች መጥፋት ምክንያት መሆኑንም ማንሳት ተገቢ ነው።





### ባሕላዊ እሴቶች ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ፦

እነዚያው የወንጌልን ችቦ አብርተው ባሕር ተሻግረው የመጡት ሚስዮናውያን በእውቀትም ይሁን በስሕተት ባሕሉ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል። ለዚህም ዋናውና ትልቁ ምክንያት የሚመስለው ተቀባዩ ባሕል በሙሉ ከዛር፣ ቃልቻና የጣዖት አምልኮ ጋራ የተያያዘ ነው በሚል ግምትም ይሁን እምነት ነበር ለማለት ይቻላል። ለምሳሌ መዝሙሮች ለመዘመር ከበሮና የመሳሰሉትን መሣሪያዎች መጠቀም አይቻልም ነበር። ምክንያቱ ደግሞ ቀደም ሲል ጣዖት አምላኪዎች ስለተጠቀሙበት ያለ አንዳች ጥያቄ ተወግዷል። ማጨብጨብና እልል ማለትም ሁሉ የማይሞከር ነበር። ማንኛውም ዓይነት ውዝዋዜ ከአጋንንት ጋራ እየተያያዘ በጸሎት ቤቶች የማይደፈርና በጥብቅ የተከለከሉ ነበሩ።

ይሁን እንጂ ሚሲዮናዊያን ይዘዋቸው የመጡት ፒያኖ፣ አኮርዲዮን አርጋንና ጊታርም የመሳሰሉ የሙዚቃ መሣሪያዎች ለመዘመሪያ እጅግ ተፈላጊ ነበሩ፤ አሁንማ በተሻሻለ መልኩ ጥቅም ላይ እየዋሉ ነዉ። በአሁኑ ጊዜ ከበሮ ከሞት እንደተነሣ ያህል በአምልኮ ሥፍራዎች ይገለገሉበት ጀምረዋል። ይህ ጸሐፊ ወጣት በነበረ ጊዜ ለብቻም ሆነ በቡድን ሲዘመር ቀጥ ብሎ ቆሞ ነበር እንጂ አንዳችም እንቅስቃሴ (ውዝዋዜ) ማድረግ የማይታሰብ ነበር። የአሁኖቹ ወጣት መዘምራን ደግሞ መድረክ የማይበቃቸውና "ግር" የሚያሰኙ እየሆኑ መሄዳቸውም ለማስታወስ ያህል መጥቀሱ አስፈላጊ ነው። ጋጠ ወጥነት እንዳይበዛ ከአሁኑ ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል።

ሌላው እንደጠዘ የቀረው በአልኮል ነክ መጠጥ ዙሪያ የነበረው ልማድ ነው። የመጠጥን ጉዳት አሳንሦ ለመናገር ለማቅለልም ሳይሆን ባህሉን ማውደሙ ነው። የዚህ ጸሐፊ ቁጭት የመጠጡ መቅረት ሳይሆን መጠጡን ለመጥመቅ ይገለገሉባቸው የነበሩ መሣሪያዎች ጭምር መጥፋታቸው ነው። አሁን የባሕል ሙዚዬም እንክፈት ቢባል እነዚህ መሣሪያዎች ሊካተቱ በማይችሉበት መጠን ወድመዋል ማለት

ይቻላል። ወንግሮ የሚባል ከእንጨት (ግንድ) ተቦርቡሮ የሚሠራ ትልቅ እንደጋን የሚያገለግል ነበር። አሁን የለም። የጦር መሣሪያዎች ጦር ትልቅና ትንሽ ጋሻ ሁሉ ጠፍቷል። ይህ እንኳን ከጊዜው መለወጥ እና በመሣሪያዎቹ መሻሻልና መለወጥ ምክንያት አያስፈልጉም ሊባል ይቻላል። ይሁን እንጂ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ለባሕል ሙዚየምና ታሪክ ሲማስተላለፍ የሚነገርለት ያለው ይሆን ነበር።

ስለዚህ የወንጌሉ እምነት በነባሩ ባህል ላይ አሉታዊ ጫና እንዳሳደረበት እና አንዳንዶቹም ወደ ማይመለሱበት ደረጃ ደርሰው ትውልድ መጥቶ ትውልድ ሲተካ ነባሩ ባህል ፈጽሞ ወደ ማይታወቅበትና ወደ ማይታወስበት ጽልመት ውስጥ እንዳይገባና ለታሪክ ማስታወሻነቱ ቢቀመጥ ለትምህርት ይሆናል።

## ትኩስ ድንች

አንድ ነገር ሳይዘገይ ተፋጥኖ መተላለፍ እንዳለበት ለመግለጽ ፈረንጆች "Hot Potato/ትኩስ ድንች" ይሉታል። እንደሚታወቀው ከፈላ ውሀ ውስጥ እንደወጣ ድንቹን በእጅ ይዞ ለመቆየት ዕምቅ ትኩሳቱ አያስችልምና ቶሎ ማሳረፍ ወይም ማቀበል ይጠይቃል። እንደዚሁ ወንጌል የሚያስፈልጋቸውና ዕደሉን የሚጠባበቁት ብዙ ስለሆኑ በአንድ ሰው እጅ መቆየት የለበትም።

የወንጌሉን ትኩሳት ያገኙት ቄስ ሻሜቦ ቀልቦሮ ጌታን እንዳገኙ ወደ አርሲ ሄደው ወንጌልን ለማስተማር ከወጡት የመጀመሪያዎቹ ወንጌላውያን አንዱ ነበሩ። በኋላ ቄስ ሆነው በወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ የሱስ የተሾሙት ወንጌላዊ ሻሜቦ ተወልደው ያደጉት በከምባታና ሐዲያ አውራጃ በሸሸራ ቀበሌ ነበር። ስለ እኚህ ሰው ተሰማ ዘውዴ የሰማውን ምስክርነት እንዲህ ብሎ ዘግቦአል።

> "አቶ አርጎ ፊቼ የተባለው ሰው ቄስ ሻሜቦ ሲሰብኩ ሰምቶ" በመጀመሪያ ደነገጥሁ። ሰውነቴም ሞቀ፤ ክርስቶስንም ለመከተል ወሰንሁ፤ ከዚያም በኋላ ከኔ ጋር እንዲያድር ወንጌላዊውን ጠየቅሁና እሺ አለኝ፤ ቤት ስንደርስ





> መልእክቱን ድገምልኝ ብዬ ስጠይቀው "በደስታ" ብሎ እራት እስኪደርስ ድረስ ነገረኝ"[18]

እሸቱ አባተም በወላይታም ሆነ በከምባታና ሐዲያ የመጀመሪያዎቹ አማኞች ወንጌልን ያደረሱት በተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ እንዳልነበረ ሲገልጽ "አደጋ አልባ ሁኔታ ውስጥ አልነበረም ብሏል[19]። በኋላ የኢጣሊያኑ ወረራ ሚስዮኖቹን ከአገር እንዳስወጣ ሁሉ አገር በቀሉን ወንጌላውያንንም እንዳሰቃየ እሙን ነው። ይሁን እንጂ በወንጌላውያኑ ላይ መከራን ማብዛት ለወንጌሉ መስፋፋት እንደ ማዳበሪያ ሆነና የኢጣሊያኑ ጭካኔ በበዛ መጠን እንደሚሲዮናውያኑ ካገር ሳይወጡ ተሰድደው በሄዱበት ሁሉ እሳቱ እየተጫረ የአማኞችን ቁጥር እጅግ አብዝቶት እንደ ነበረ ከድህረ ጣሊያን ወረራ በኋላ ለተመለሱት ሚስዮናውያን አግራሞትን ጨምሮላቸዋል። ወንድዬ አሊ የመጀመሪያዎቹ ወንጌላውያንን ሥራና የወንጌሉን ሂደት ሲገልጽ፡-

በደቡብ ኢትዮጵያ ሰፊ ምድር የተዘራችው የሰናፍጭ ቅንጣት የራሷን መልክ ይዛ ታየች። አዲሲቷ ቤተ ክርስቲያንና የበኩር ልጆችዋ የጨለማው ገዢ በሰለጠነበት ምድር ያቀጣጠሉት ችቦ ደማቅ ብርሃን መስጠት ጀመረ። በመጀመሪያ ለክርስቶስ የተሰጠ ሕይወታቸው፣ ቀጥሎም ትምህርታቸውና ኑሮአቸው ሚሲዮን ሳያጠላበት ብቻውን እንዲቆም ጊዜው ግድ አለ።[20]

"የመጀመሪያው ፍቅር" ግድ ብሎአቸው ቤታቸውን፣ ቀዬአቸውንና ዘመድ አዝማዱን እየተው ነበር የወጡት። ይህ ጸሐፊ ሻሸመኔ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ በነበረ ጊዜ 1946 ዓ.ም ከከምባታ ሐዲያ ወደዚያ ተልከው የነበሩ ወንጌላውያን አቶ ያዕቆብ ባፋ፣ አቶ ሽፈራው አረኮንና አቶ አየለ ለቴቦ ከሻሸመኔ ዙሪያ እስከ ወንዶ ገነት ድረስ በእግራቸው እየተዘዋወሩ ያስተምሩ እንደ ነበረ ምስክር ነው።

[18] Tesemma Zewde: The Seed Bore Fruit, FMA Publishing 2o1o, pg 49
[19] እሸቱ አባተ 1980 ገጽ 33
[20] ወንድዬ አሊ፤ በመከራ ያበበች ቤተ ክርስቲያን፤ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቅፃ 1

ሁለት ጊዜ ያህል ወደ ወንዶ ገነት ይዘውኝ ሄደው በተለይ ሽፈራውና አየለ ካስተማሩ በኋላ ጠንቋዮች ጨሌአቸውን ጀበናቸውን፣ ሌሎችንም የጥንቆላ ዕቃቸውን እያወጡ ሲሰብሩና ሲያቃጥሉ እጃቸውን ወደ ላይ እያነሱ ጌታን ሲቀበሉ የዓይን ምስክር ለመሆን ዕድል አግኝቼ ነበር። ከወላይታ አቶ ገሎሬ፣ አቶ ቡናሮ፣ አቶ ባዛ የሚባሉ በጌታ ማሳ የተሰማሩ ገበሬዎች ነበሩ፡፡ በሻሸመኔ ዙሪያ እየተዘዋወሩ በሚያስተምሩበት አመታት ድንገት ወደ ቤታቸዉ ስሄድ የሚያጋጥመኝ መስተንግዶ የየበቆሎ ቆሎና የቀጣጠነ ቡና ነበር፡፡ ብዙዎችን ባለጸጋ እያደረጉ በድህነት እየኖሩ ወንጌልን ለማገልገል መቁረጣቸዉ እስከ አሁንም ያስገርመኛል፡፡

በዚያው ጊዜ ነበር የሁለት ልጆች አባት የሆነዉ ጋሼ ኬዳሞ ሜቻቶ ከዲላ ወደ ሻሸመኔ - ኩየራ መጥቶ ከአቶ ኢዮኤል ፉጌ ጋራ ወደ ዲላ የተጓዙት፡፡ እነዚህ አንጋፋ ወንጌላውያን ከየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸዉ በወር አሥር ብር ለቀለብ ተቆርጦላቸዉ እንደነበርና ያቺም በየምክንያቱ እንደ ማትደርሳቸዉ ጋሽ ኬዳሞ እንዲህ ያስታውሰዋል፡፡

> “የአሥር ብሩ ደመወዛችን ሁል ጊዜ ተስተካክሎ አይመጣልንም ነበር። ካለ በኋላ “አንድ ጊዜ ለአሥራ አምስት ወራት አሥሩም ብር እልም ብሎ ቀርቶ ነበር። ለዕረፍት ወደ አገር ቤት ሄጄ ሳለሁ ከሽማግሌዎች ለአንዱ ገንዘቡ ለአሥራ አምስት ወራት እኮ አልደረሰንም ብዬ ስነግረው በመደነቅ ሰማኝ፡፡ እንዴት/ለምን ካለ በኋላ ሁለታችንም ዞር ብለን ስናይ እየተቀበለ እንዲልክልን ተወክሎ የነበረዉ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ በቅርብ ርቀት ሆኖ አዳምጦን ኖሮ ላብ ሲያጥለቀልቀዉ አየን፡፡ ይህንን ነገር ከሁለታችን በቀር ወደ ማንም ጆሮ እንዳይደርስ አደራ ብዬ ነግሬዉ ጉዳዩ በዚያው ተቀብሮ ቀረ። ወደ ባሌ የተላኩት አቶ ዮሐንስ አንሼቦና አቶ በቀለ ወራቆ ተመሳሳይ ችግር ተጋፍጠዉ ነበር”።





## መነቃቂያ ኮንፍራንስ፡-

ትልልቅ የመነቃቂያ ጉባኤ (ኮንፈረንስ) በማዘጋጀት የምትቀድመዉ የወላይታ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ነች፡፡ ወላይታን ተከትላ የከምባታና ሐዲያ ቤተክርስቲያን በ1944 ዓ.ም በቡብቾ ማእከል ዓመታዊ መንፈሳዊ ኮንፈረንስ ማድረግ ጀመረች። በዚህ ስብሰባ ለመገኘት በያመቱ ከአውራጃዋ አራቱም ማዕዘን በብዙ ሺሆች የሚቆጠር ምዕመን ሲተምም እንደ እኔ በልጅነት እድሜዉ ለማየት የታደለ ሰዉ ትዝታዉ ዘላለሙን አይለቀውም፡፡

አዘጋጆቹም ሆነ ሊሳተፉ የሚመጡት ምዕመናን በደስታ፣ በሰላምና በአንድነት መንፈስ ሞልቶት መገለጫው ሳቅ፣ መተቃቀፍ፣ መሳሳምና መነፋፈቅ ነበር። ታዳሚው ይዞ የሚመጣው የራሱን ለሳምንት የሚበቃ ስንቅ፤ መኝታውንና ያለው የሚጓጓዝበትን ፈረስ፣ በቅሎና ስንቁን የሚጭንበት አህያ ነበር።


ሌሎች ሁለት ዓይነት ሰዎች ወደ ስብሰባው የሚመጡት 1ኛ/ከአካባቢው በትምህርትና በሥራ ወደ አዲስ አበባና ሌሎችም ከተሞች የተሰማሩ ጊዜውን አመቻችተው የሚሳተፉ 2ኛ/ በስብሰባው በተናጋሪነት በዘማሪነትና ምስክርነት ሊሰጡ የሚጠሩ “እንግዶች” ነበሩ፡፡ ከስብከቱና ከመዝሙሩ ሌላ በዚህ ስብሰባ የሚከናወኑ ሁለት አበይት ጉዳዮች አሉ። እነርሱም ለወንጌል አገልግሎት ራሳቸውን እንዲሰጡ የሚደረገው ጥሪ እና ለወንጌል ሥራ የሚሰጠው መባና ምፅዋት ነው።

በተለይም ደስ የሚለው በስብሰባው መጨረሻ ሰው ጭኖበትና ተቀምጦበት የመጣውን የጋማ ከብት (አህያ፣ ፈረስም ሆነ በቅሎ) ለወንጌሉ ሥራ እዚያው ሰጥቶ በእግሩ የመልስ ጉዞውን ሲያያዘው ማየት ነው። አቶ ኬዳሞ “አሥር የምንሆን ወጣቶች ጥሪውን ተቀብለን የወጣነው በዚያ በ1944 ዓ.ም. ስብሰባ ነበር።” ብሏል። /ሕዳር 22 ቀን ባደረግነው ቃለ ምልልስ/። ይህ ጸሐፊም እግዚአብሔር

ፈቅዶ ከ1968-1978 ዓ.ም ድረስ በሦስቱም ቦታዎች ማለትም ወላይታ በሶዶ፣ በዱራሜ ጠዛና በቦብቾ ዓመታዊ ስበሰባዎች በያንዳንዱ ቦታ ሁለትና ሦስት ጊዜያት በተናጋሪነት የማገልገል ዕድል ገጥሞታል።

## ሁለቱ ባሪያ ፈንጋዮች ያሳደሩት በጎ ተፅዕኖ

የወላይታው ዳና መጃና የከምባታና ሐዲያው አባጎሌ ኑነሞ አንድ የሚያደርጋቸዉ ጌታን ከማግኘታቸው በፊት የነበራቸው የሥራ መስክ ነበር። ሁለቱም ባሪያ ፈንጋዮች ነበሩ። በተለያየም ጊዜ ቢሆን ሁለቱም ጌታን ተቀበሉና የቀደመውንና የታወቁበትን የባሪያ ፍንገላ እርግፍ አድርገው ጥለው አዲስ የሕይወት መንገድ ተያያዙት። ሳውል በደማስቆ መንገድ ጌታ ተገናኝቶት ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሲወሰድ ስለቀደመው ሥራው ያውቁ ስለነበረ ደቀ መዛሙርቱ የተቀበሉት በፍርሃትና በጥርጣሬ ነበር (ሐዋ 9)፡፡ በተጨማሪም የሁለቱም አካላዊ ቁመና ግዝፈት ለመፈራታቸዉ አስተዋፅዖ እንደነበረዉ የሚያውቋቸዉ ይመሰክራሉ፡፡



አባ ጎሌ ኑነሞ



ዳና መጃ መደሮ

በእርግጥ አባጎሌ ከዳና መጃም ይገዝፋሉ፡፡ ስለሆነም ወንጌልን ከተቀበሉ በኋላም ምእመኑ ወዲያው በተዘረጋ እጅ ያቅፋቸዉ ዘንድ ፈራ ተባ ይል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አዲስ ለተቀበሉት እምነት ታማኝነታቸውን በራሳቸዉ ለማስመስከር በተጉ መጠን





ታዋቂነታቸው እየጎላ ጥርጣሬውም ሆነ ፍርሃቱ በመታመንና በመወደድ ተቀይሮ እንደ ጴጥሮስ የገሃነም ደጆች የማይችሏትን የጌታን ቤተ ክርስቲያን መምራቱን ተያያዙት። ስለ ዳኛ መጃ ወንድዬ ሲጽፍ፡-

> "ከዚህ በኋላ አይበገሬው ኩሩው፡- ባሪያ ፈንጋይ፣ ሹም መጃ መደሮ በጌታ በኢየሱስ ፍቅር ተማርከው የክርስቶስ ባሪያ ሊሆኑ ወደ ክርስቲያኖች ኅብረት ተቀላቀሉ. . ." ካለ በኋላ፡-
>
> ". . . በቤተ ክርስቲያን መሪነታቸውም የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበርን ለማቋቋምና የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሠረት ከጣሉት ሰዎች አንዱ ለመሆን በቅተዋል። ስለ ቤተ ክርስቲያን ለመሟገትና የሃይማኖት ነፃነትን ለማስጠበቅ ከእነ ቄስ ባድማ ያለው ጋር በመሆን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ፊት ለመቅረብ የበቁም አረጋዊ ናቸው" -ሲል ገልፆአቸዋል።[21]

ሁለቱም ዳና መጃ (የወላይታን)፣ አባጎሌ (የከምባታና ሃዲያን) ቤተክርስቲያናት ለተከታታይ 30 አመታት ያህል የመሩ አባቶች ነበሩ፡፡ ዳና መጃ ከአባጎሌ የሚለዩበት አንድ ትልቅ ነገር አብዛኛዎቹ ልጆቻቸው ፈለጋቸውን ተከትለዉ እንደ አባታቸው ሁሉ ቤተክስቲያንን እንደ ጸጋቸዉ መጠን ማገልገላቸዉ ነዉ፡፡ በተለይም መርኪና መጃ ከወጣትነት እስከ መቃብራቸዉ አፋፍ ድረስ ቤተክርስቲያንን ማገልገላቸዉ ይታወቃል፡፡

በአንጻሩ ደግሞ አባጎሌን የሚያህል ታላቅ አገልጋይ ፈለጋቸውን ተከትሎ በወንጌል ማሣው ላይ አብሯቸዉ ቀንበር ለመሸከም ራሱን የሰጠ ልጅ የላቸውም፡፡ ምስጢሩ የእግዚአብሔር ነዉ፡፡ ይህም የማታ ማታ ብቸኛ አድርጓቸዉ ነበር፡፡ ሆኖም ወደ ኋላ ሳይጎትታቸውና ለሥጋቸው ዕረፍትና ምቾት ሳይሹ እጅግ ብዙ መንፈሳዊ ልጆችን አትርፈው የነርሱን ደስታ ደስታቸው አድርገው ሲኖሩና ሲያገለግሉ ዕድሜአቸውን

[21] ወንድዬ አሊ፤ በመከራ ውስጥ ያበበች ቤተ ክርስቲያን ገጽ 221 እና 223



አባ ጎሌ ኑነሞ



ዳና መጃ መደሮ

ፈጅተው ወደ ጌታቸው ተሰብስበዋል። Staffan Grenstedit ስለ አባጐሌ የወንጌል ሥራ ሲጽፍ በኢጣሊያኑ ወረራ ምክንያት አመቺ ሁኔታም ባይኖር "አገር በቀል ብርቱ የወንጌል ሰባኪና የቀድሞው ባሪያ ፈንጋይ አባጐሌ ሰውን ለማሳመን ኃያል መሣሪያ ሆነዋል። እንደ እርሳቸውም ላለ ታላቅና ታዋቂ ሰው የኢጣሊያውያኑ ማስፈራሪያም ሆነ የቃልቻዎች ከፉ መንፈስ ሊበግራቸው አልቻለም" ::[22]

በስምንት ዓመቴ ለትምህርት ወደ ዱባንቾ ተልኬ እንደነበረ በሌላው ክፍል ተጠቅሷል። ዱባንቾ የአባጎሌ መኖሪያቸው ነበር። ከሄዱበት ሲመለሱ ወይም ሲሄዱ ወደ ት/ቤቱ ብቅ ብለው "እንዴት ናችሁ? ትበረታላችሁ?" ብለው ራሳችንን አሻሽተው ይሄዱ ነበር:: አንድ ቅዳሜ ቀን የአባቴ ወዳጅና አባ ጎሌ ወደ ትምህርት ቤት መጡ። ሁሉንም ሰላም ካሉ በኋላ እኔን በእጃቸው ጠቁመው "ና!" የሚል ምልክት ሰጡኝ:: ስቀርባቸው ከኔ ጋራ አንድ ቦታ ሄደን እንመጣለን አሉኝ:: ያለምንም ማንገራገር ተከተልኳቸዉ። መድረሻቸው ሹርሞ የሚባል መንደር፣ ዓላማቸውም የመንደሩን ሰው ሰብስበው ስለየሱስ ማስተማር ነበር:: የኔ ሥራ ደግሞ በቅሎአቸውን መያዝ ነበር። ተልእኳቸውን ሲጨርሱ በመጣንበት አኳኋን ተመለስን። ኑሮአቸው ይህን ይመስል ነበር። "የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁ" (ዮሐ. 6÷38) እንዳለው ጌታቸው የላካቸውን (የጠራቸውን ፈቃድ ማድረግ የአባጎሌ የረዥም አገልግሎት መገለጫ ነበር:: የአባበጎሌን ሕይወት እንደ መጽሐፍ እያነበበ፣ ተግባራቸውን እያዩ ማደግ ቢቻልም በአንዳንዱ መድረክ ከእርሳቸው ጋራ መቆም እንደርሳቸው ያገዝፋል።

እነዚህን ሁለት ግዙፋን (Giants) መልምሎ እስከ ሕልፈተ ሕይወታቸው የተገለገለ ጌታ እውነትም ታላቅ ነው። ሰውን በገንዘብ ገዝተው ለገንዘብ ሸጠው በኃጢአት ባርነት ይኖሩ የነበሩትን ባሪያ ፈንጋዮች በደሙ ዋጅቶ ነፃ አውጥቶአቸው የባርነትን

[22]Ambaricho and Shonkola, Pg 6)





ሳይሆን የነፃነትን (የአርነትን) ባንዲራ እከሌ ከእከሌ ሳይሉ በእጃቸው እንደ ያዙ ዘመናቸውን ጨርሰዋል:: ክብር ሁሉ ለእርሱ ይሁን!!

ቀጥሎ ደግሞ የመጀመሪያዎቹ የወንጌል አማኞች በአካባቢዉ አገላለጽ "የሱስ መናዎች" በእምነታቸዉ ምክንያት በግላቸውና በቤተሰባቸዉ ከደረሰባቸዉ ስደት ሌላ እንደ ክርስቲያናዊ ማሕበረሰብ በጅምላ ያስተናገዱትን ስደት አንዷን ዘለላ ጠቅሼ ወደ ጉዞዬ እመለሳለሁ::

## 9. ስደቱና የፈጠረው ትርምስ

"ኢየሱስ መናዎችን" (የኢየሱስ ሰዎችን) ለማሳደድና ለማሠር ከሐንገጫ ተልከው የመጡት ፖሊሶች የመጀመሪያ አዳራቸውን አዜ/ደቦአ - አቶ ኤርጊቾ ቤት ካደረጉ በኋላ አቶ ፎቼ ቤት ለሁለተኛው ቀን አዳር ተመሩ። የኛ ቤትና የአቶ ፎቼ ቤት ፊት ለፊት ሲሆን ደቀያ የተባለው በቁመቱ ያለ አንዳች ችግር አይሮፕላን ያሣርፋል ብዬ የምገምተው ሜዳ አለ። የጨጫን ተራራ ከጀርባው የተደገፈ የሚመስል የአቶ ፎቼ ቤት በርቀትም ቢሆን ይታያል። በቤት ውስጥ እሳት ሲነድ ጪሱ ከሣር ቤት ቡልቅ ብሎ ሲወጣ በጉልህ ይስተዋላል።

ፖሊሶች መጥተው እዚያ ሊያድሩ እንደገቡ ወሬው ፈጥኖ ተዛመተ፤ እኛም ሰምተናል። አባባ በዕለቱ ሆሣዕና ሄደው ስለነበረ በቤታችን እናታችንና እኛ ልጆቹ ብቻ ነበርን። ባይጎላም በእማማ ውስጥ ፍርሃት እንደነበረ አስባለሁ። ቀኑ መሽቶ ከብቱ ሁሉ ከግጦሽ ተመልሶ የቤታችን በሩ ተዘግቷል። እንደተለመደው የነደደው እሳት ብርሃኑንም ሙቀቱንም ከማደሉ በላይ እራት እየበሰለበት ነው። እኛም ዙሪያውን ከበን እንደ ወትሮአችን ተቀምጠናል:: እራቱ ይበላ አይበላ አላስታውስም፤ ግን የተደጋጋመ ተኩስ በድንገት ተሰማ። በቤታችን የኮሽታም ድምፅ አልነበረም፤ ጋጣው ውስጥ ታስረው ከነበሩት ከብቶች እንቅስቃሴና ማመንዠግ

በተቀር። እማማ የጓሮውን በር ከፍተው ለመቃኘት ሲወጡ ተከትዬ እኔም ወጣሁና በአጥሩ ላይ ወደ ተኩሱ አቅጣጫ ሳማትር በጨረቃው ምሽት በጨሜ ተራራ ጥጉን ይተኮስ የነበረው ጥይት ከብዛቱ የተነሣ በልጅ አእምሮ ከሰማይ እንደሚወረወር ኮከብ ያበራ ነበር። ምሽቱ እንደወትሮው ጤነኛ እንዳልሆነ የተረዳው ከቤታችን ቀጥሎ ይኖር የነበረ አጐቴ አደሞ በጓሮ እየተጣደፈ መጣና የአባባን በቅሎና ዋጋ ሊያወጡ የሚችሉ ዕቃዎችን ማሸሽ እንዳለብን ለእማማ በተሰበረ ድምጽ አስረዳና አንዱን ሣጥን እርሱ አነስተኛውን እኔ ተሸክመን ራቅ ብሎ ወደ አለው ዘመዳችን ቤት በጨለማ ወንዝ ተሻግረን ወስደን ሸሸግን።

ወዲያው ተመለስንና በቅሎዋን ይዘን የጨሜን ተራራ ከቤታችን በስተደቡብ በኩል ወጥተን እኔና ያው አጎቴ ቃጨ-ቢራ አልፈን ገባቦ በሚባል ቦታ ወዳለችው የእናቴ እህት ቤት አደረስን። ከብቶቻችንንም ወደ ቃጨ ቢራ በለሊት እናቴና ሌሎች ሰዎች ነዱአቸው። ወደኋላ የቀሩትን ጥጆች ጅቡ አላስሄድ በማለቱ ወደ የሚያውቁት ሰዎች ባዶ ቤት ከፍተው እንዳስገቡና የሠፈሩ ጎረምሶች ለዘረፋ ነድተው አንዱንና ያማረውን ጥጃ ለማረድ መርጠው ሲወያዩ የሰማ የአካባቢው ሰው "እስቲ ንክች የዳለሎን ንብረት አርዳችሁ እዚህ ሰፈር እንኖራለን አትበሉ" ብሎ እንዳስጣላቸው እማማ አስታውሰው አጫውተውኛል።

ከትንሽ ጊዜ የተኩስ እሩምታ በኋላም ጸጥታ ሰፈነና የተፈጠረው ግርግር አብቅቶ እንዳይታደር የለምና ታደረና ሌሊቱን የተሸረበው ኢድማ ሁሉ ጧት ይፋ መሆን ጀመረ። ሌሊቱን በነበረው ተኩስ ከመጡት ፖሊሶች አንዱ ተገድሎና የቀኛዝማች ሻንቆ መልእክተኞች ወደ አንገጫ፣ ዱራሜና ሾኔ ሌሊቱን ሄደው "ኢየሱስ መናዎች ሸፍተዋል" ባሉት መልእክት የመጣው የፖሊስ ኃይል የጦር አገር አስመስሎት ነበር። በዚያው ሌሊት በቤተ ክርስቲያን ካደሩት ሽማግሌዎች አቶ ሻዕመሎን፣ አቶ ሹኩዕሎ፣ አቶ አጭሶና አቶ ለፌቦ የተባሉትን አማኞች ይዘዋቸው አድረዋል።

"የቀሩት ከሁለት ወር እስራት በኋላ 75.00 (ሰባ አምስት) ብር እየከፈሉ ሲለቀቁ አቶ ፎቼ አናሞ፣ አቶ ፉዕኑሮ አናሞና አጎቴ አቶ መንታሞ ዋቤቶ የግድያ ክስ ተመስርቶባቸው በጊዜው የጠቅላይ ግዛቱ ዋና ከተማ ወደ ሆነችው ወደ አሰላ ተላኩ።[23] በዚያ ቀውጢ ወቅት እንኳን ሰው ከብቱም ተንገላታ፣ አየሩም ታወከ። በልጅነት አእምሮዬ የማስታውሰውና ከቶም የማይረሣኝ ሁከት በጀመረ ማግሥት ረፋዱ ላይ አቶ ገዴቦና አቶ ሐንቄቦ የሚባሉ 2 የቀኛዝማች ሻንቆ አሽከሮች እያንዳንዳቸው ጥምር ጦር ይዘው እየሰበቁና ኡኡ ብለው እየጮኹ ደቀያ ሜዳ ላይ ወጥተው ሕዝቡን ለማነሣሣት ሙከራ አድርገው ነበር። ነገር ግን ሰምቶ የወጣላቸው ወይም የተባበራቸው ሰው አልነበረም። ይህንን በወቅቱ የከብት እረኛ የነበረው የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ከአእምሮ ውስጥ ተቀርጾ የቀረ ማስታወሻ ነው።

በዚያ ግርግር ምክንያት ብዙዎች ታሠሩ፣ ተንገላቱ፣ ንብረት ወደመ፣ ነፍሳት ጠፉ። የአንድ አካባቢ ሰዎች አንዱ አሳዳጅ ሌላው ተሰዳጅ፣ አንዱ ወንጃይ ሌላው ተወንጃይ፣ አንዱ ከሳሽ ሌላው ምስክር በመሆን ይህንን ሁሉ ሁከትና ግርግር በራሳቸውና በኅብረተሰቡ ላይ ፈጠሩ። በዚያ ሁሉ ውስጥ ግን ቦታ አጥታ፣ ድምጿ ሳይሰማና መኖሯም ያልታየላት "እውነት" የተባለች ነገር ነበረች። በጊዜው ተካደች፣ ያለሆነችውን ሆነች ተብላ ተቃራኒዋ የሆነችው ሐሰት ግን ነገሠች፣ በራች፣ አምታታች፣ አጋጨች፣ አጋደለችም። በጊዜው ለግብረ አበሮችዋ መሰለች እንጂ እውነት የማትጠፋ፣ የማትሞት፣ ሐሰትም ልትበራም ሆነ ልታበራ የማትችል አስመስላ የሰውን ልጅ እያምታታችና ግራ እያጋባች ወደ ጽልመት እየመራች የዓለምን ሕዝብ ለጥፋት እየዳረገች ትኖራለች።

አንድ ትዝታ ልጨምር፤ በዚያዉ ሰሞን አባባ ከእምነት ባልደረባቸዉ ከአቶ ዳዕሞ አበበ ጋር ሆነዉ ከሆሳዕና ሲመለሱ ወደ ሐንጋሜ ከተማ ጎራ ብለዉ ከወረዳዉ ገዥዉ ጋር ተገናኙ፡፡ በፖሊሶች ታጅበዉ የነበሩት ወረዳ ገዥ «ትፈለጋላችሁ»

[23] ወንድዬ አሊ፤ የእከሌ ሴለት ወገግታ፤ ቅጽ 2 የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ታሪክ፤ ማያዝያ 1992 ዓ.ም. ገጽ 305

በማለት ፖሊስ ጣቢያ እንዲቆዩ ለአጀቧቸዉ ፖሊሶች ትዕዛዝ ሰጡ፤ እነ አባባም ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰደዉ ገና በአጥር ግቢዉ ውስጥ እንዳሉ ወረዳ ገዥዉ በርከት ካሉ ፖሊሶች ጋር ሲመጡ አዩአቸዉ:: አመጣጣቸዉ ለሰላም እንዳልሆነ የተረዱት ጓደኛሞች ከፖሊስ ጣቢያዉ አጥር ላይ አንዳንድ እንጨት ነቅለዉ ያዙ:: ወረዳ ገዥውንም «ሃሳብህ ገብቶናል! ሱሪያችን በአንገታችን ይወልቃል እንጂ ሜፋችንን አትነካንም! ወንድ ከሆንክ ና ሞክረን!» ሲሉት «እነዚህ ሰይጣኖች . . .» ብሎ ወደ መጣበት ተመለሰ:: እነሱም ከግቢዉ ወጥተዉ ወደ ቤታቸዉ ሄዱ:: ይህንን ያጫወቱኝ አባባ ዳዕሞ ናቸዉ::

ያ ወቅት ከአለፈ በኋላ ሰውን ለጸጸትና ለቁጭት ዳራጊ ወዳጅ መሳይ ጠላት ናት። ሐሰትና እውነት ሁለቱ እንደማይስማሙ ጣውንቶች ናቸው። ይወነጃጀላሉ፣ በከፋት ለከፋትና ለጥፋት ይፈላለጋሉ። ጣውንትነትን የሚገልጽ በከምባታና ሐዲያ የተለመደ አባባል አለ። ጣውንቷ ሞታ ሊቀብሯት በአጭር ቃሬዛ ተሸከመዋት ሲሄዱ ሌላዋ ጣውንት በሰዎች መሃል እየሄደች የአስከሬኑን አንገት ቃሬዛው ስላጠረና በተሸካሚዎቹ ንቅናቄ ወዲያ ወዲህ ሲወዛወዝ አይታ (ኤጂ በኢ እሴንታ አሰኖሴጋ ጡጅዬ) (ኤራዕል እሴም እሶ እሥ ሞዕሴሄ) ይህን አባባል በአማርኛ ተመሳሳይ የሚመስል "እንኳንስ ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ" ዓይነት ነው።

ከላይ እንደተገለጸው በአንዳች እውነት ሳይደገፍና ሙሉ በሙሉ በሐሰት ተጠንስሶ በከፋት የተፈጠረው ሁከትና ግርግር ለሰው ሕይወት መጥፊያ፣ ለንብረት ውድመት፣ ለሰላም መደፍረስ እንጂ ምን አተረፈ ተብሎ /ቢጠየቅ (ጠያቂው ከተገኘ) መልሱ ከንቱ ነው። ከሣሾቹ፣ የሐሰት ምስክሮቹ የዘረፉዉ ሁሉ ተባባሪዎች (በትርምሱ) የት ደረሱ? ምን አተረፉ? ማንን ጠቀሙ? ቢባል በጊዜ ጥብቅና ሁሉም ከሡሩ፣ ተሸነፉና ሐሰት ጸጸትን ትታላቸው አለፉ። ይህ እንግዲህ ወደ ሕሊናቸው ተመልሰው ከሆነ ማለት ነው። እንደጠፋ ይጥፋ ማለት "two mistakes don't make one right"





ሁለት ስሕተት አንድ እውነት አይሠራም/አያደርግም እንደሚሉት ፈረንጆች ስለሆነ ፋይዳ የለውም። እውነት የሕሊና በራቸውን ስታንኳኳ ሰምተው ቢከፍቱላት ብርሃን የእውነት ተባባሪ ስለሆነ ነፃ ያወጣቸዋል። ሌሎችን የመከራ ገፈት ቀማሾች እንዳደረጉ እነርሱም ከማለት ይልቅ "ጌታ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ" (ሉቃስ 23÷42) እንዳለው ወንበዴ ዕድል ቢያገኙ።

እውነትን ረግጠው ቆመውበት ራሳቸውን ለሐሰት ያስገዙ እነዚያ አባቶች በሐሰት ክስ፣ በሐሰት ምስክር የሐሰት ፍርድ በማስፈጸም የማኅበረሰቡን ሕሊና ያቀለመና ሰብዓዊ እውነታውን በማጣመም ከፍትህ የራቀ ፍርድ በማስፈረድ የክርስቲያናዊ ማኅበረሰብ እሴቶችን እንዲዘቅጥ አድርገውታል። በአሁኑ ጊዜ እንኳን እነርሱና ልጆቻቸውም በአብዛኛው ሞተዋል። የፈጸሙትን የከፋ ሥራ ታሪክ ቢያስታውሰው እንጂ እነዚያ ከሳሾች፣ ምስክሮችና ዳኞች የገዛ ሕይወታቸውን ብሎም ታሪካቸውን የሐሰት ካባ በማልበስ አቅልመውታል። ያለውና የሚመጣው ትውልድ ይህንን ታሪክ ቀብሮት እንዳይተው ነገር ግን መማሪያ ርእስ አድርጎ ሐሰትን ሳይሆን እውነትን ተጣብቆ ትውልድ እንዳይጠፋ መጣር አለበት። ትላንት እንዴት ነበር? በምን ምክንያት? እንዴት? የማይል ትውልድ ለራሱም ለሚተኩትም አይበጅምና::